አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ በበና ፀማይ ወረዳ

በ
ዘላለም ፋንቱ

በኢትዮጵያ ስነ-ፅሑፍና ፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ለማሟላት የቀረበ

በሰብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ
የኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
ኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

መስከረም 2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ በበና ፀማይ ወረዳ

በ
ዘላለም ፋንቱ

በኢትዮጵያ ስነ-ፅሑፍና ፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ለማሟላት የቀረበ

አማካሪ
አቶ ቱምድሮስ ገብሬ

በሰብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ
የኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
ኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

መስከረም 2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ

የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ በበና ፀማይ ወረዳ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

በሰብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ቴዎድሮስ ገብሬ	
አማካሪ	ፊርማ
ሰለሞን ሙሄት መዓ	
የውስጥ ፈታኝ	ፊርማ
የውጭ ፈታኝ	ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ቋ.ሙ.ቁ.
ቤተ መጻሕፍት
ILS
LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

ምስጋና

- መምህራ እና አማካሪዬ አቶ ቱምድሮስ ገብሬ ከጥናቱ ሂደት አንስቶ ውድ ጊዜያቸውን በመሰዋት፤ የጥናት ፅሁፌን በማረም፤ በማስተካከል እና አቅጣጫ በመጠቆም ረገድ ላደረጉልኝ ከፍተኛ ትብብር እጅግ አብዝቼ አመሰግናለሁ።
- የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድኅረምረቃ ትምህርት ቤት ጥናቱን እንዳካሂድ በገንዘብ ረገድ እገዛ ስላደረገልኝ አመሰግናለሁ።
- አቶ ጌታነህ ግርማ በመስክ ቆይታዬ ወቅት ማረፊያ ቦታ ከማዘጋጀት አንስቶ ጥናቱን በማካሄድበት ግዜ ላደረጉልኝ ከፍተኛ እገዛ እጅግ አመሰግናለሁ።
- በጥናቱ ወቅት በዋና መረጃ አቀባይነት ያገለገሉኝን አቶ ጋያ ፊዮ፤ አቶ በላቸው ሉማር፤ አቶ ዶይዶ ኪሎ፤ ወ/ሮ ሶፋ ዶቢያር፤ ወ/ሮ ወንገላ ሰጎ፤ አቶ ፍቃዱ ጋሴ እና አቶ ሰጎ አዮን፤ እንዲሁም በአስተርጓሚነት የተባበሩኝን አቶ ተስፋዬ ኢሾ እና አቶ ማሙሸን በጣም አመሰግናለሁ።
- ወዳጆቼ ታደሰ ሺበሺ፤ መዓዛ ገብሩ፤ ሙሉቀን ንጋቱ፤ ለታሪክ ተሾመ እና የኔአሳብ የሰራህ መፅሃፍ በማዋስ፤ በሃሳብ፤ በሞራል እና በማቴሪያል በኩል ላደረጋችሁልኝ ቀና ትብብር አመሰግናለሁ።

ማውጫ

ገጽ

ምስጋና ..... ሀ

አጠቃሎ ..... ለ

1. መግቢያ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 2

1.3 የምርምር ጥያቄዎች 2

1.4 የጥናቱ ዓላማዎች 3

1.5 የመረጃ መሰብሰቢያ እና መተንተኛ መንገዶች 3

1.6 የጥናቱ ወሰን 5

1.7 የጥናቱ ውጤት ጠቀሜታ 5

1.8 በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች 6

2. ክለሳ ድርሳን 8

2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት 8

2.2 የንድፈ ሃሳብ ቅኝት 22

2.2.1 ሞት፣ ለቅሶ፣ ክብረ-በዓል እና ክዋኔ 22

2.2.2 ክዋኔ እና የክዋኔ አላባውያን 30

3. ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ዳራ 35

3.1 የአካባቢው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ 35

3.2 የበና ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ እና አሠፋፈር 37

3.3 የበና ብሔረሰብ ባህላዊ አስተዳደር 38

3.4 የበና ብሔረሰብ ባህላዊ እሴቶች፣ በዓላት እና ክብረ በዓላት 40

4. የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ በበና ብሔረሰብ 43

4.1 የቅድመ ሞት ዝግጅት 43

4.1.1 ሞት መቅረቡን ማረጋገጫ ብልሃቶች 44

4.1.2 ኑዛዜ 47

4.1.3 ለለቅሶው ማስፈጃ እና ለለቀስተኛ ማስተናገጃ የሚደረጉ ዝግጅቶች 50

4.1.3 ለለቅሶው ማስዒጃ እና ለለቀስተኛ ማስተናገጃ የሚደረጉ ዝግጅቶች 50
4.2 ጊዜ ሞት 53
4.2.1 ድህረ-ሞት የሚደረጉ ስነ-ስርዓቶች 54
4.2.2 ጉዞ ወደ ቀብር 61
4.2.3 በቀብር ወቅት የሚደረጉ ስነ-ስርዓቶች 63
4.3. የድህረ ቀብር ክዋኔዎች 69
4.4. የቀጠሮ ለቅሶ 72
5. ማጠቃለያ እና ይሁንታ 74
5.1. ማጠቃለያ 74
5.2. ይሁንታ 76
ዋቢ ጽሑፎች 78
አባሪዎች
አባሪ አንድ፡ የመረጃ አቀባዮች ኘሮፋይል
አባሪ ሁለት፡ ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ መንደርደሪያ ጥያቄዎች
አባሪ ሶስት፡ የዞኑ ወዳዎች አጠቃላይ መረጃ
አባሪ አራት፡ የወረዳዎች እና የቀበሌዎች ካርታ

አጠቃለሎ

ይህ የጥናት ፅሁፍ ዋና ትኩረቱን ያደረገው በበና ብሔረሰብ ዘንድ የሚደረገውን የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔን በማሳየት ላይ ነው። ጥናቱ ሁለት ዓበይት ዓላማዎችን የያዘ ነው። እነዚሁም በበና ብሔረሰብ ዘንድ የሚደረገው የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ ምን እንደሚመስል ማሳየት እና ከእያንዳንዱ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ ጀርባ ያለውን ትርጉም መግለፅ ናቸው። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ከፅሑፍ መጠይቅ (*Questionnaire*) በስተቀር ሁሉም የመረጃ መሰብሰብያ መንገዶች እንደ አስፈላጊነቱ አገልግሎት ላይ ውለዋል። እነዚህንም የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶችን ከተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ጋር በማጣመር አስፈላጊ የተባሉ መረጃዎችን ለመያዝ ተችሏል። ይህ ሁሉ ይሆን ዘንድም ተፈጥሯዊ መቼትን ዳር ቆሞ መመልከት አስፈላጊ ነበር። በዚህም መሰረት ብሔረሰቡ የተለያዩ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔዎችን በሚች ማንነት እና ምንነት ላይ በመመስረት እንደሚያካሂድ ታውቋል። ሞት መቅረቡን ለማረጋገጥም አዋቂ ቤት መሄድ እና ጠጅ ጥሎ ውጤቱን መጠበቅ አስፈላጊ ነው። በሌላ በኩልም ለሚች፣ ለሚች ቤተሰብ እና ለለቀስተኛ የሚደረጉ የተለያዩ ዝግጅቶች እንዳሉ ለመመልከት ተችሏል። በእያንዳንዱ ክዋኔ መልዕክት የሚተላለፍ ሲሆን የመልዕክቱ ይዘትም የተለያየ ሆኖተገኝቷል። እነዚህ መልዕክቶችም የብሔረሰቡን አመጣጥ፣ አሰፋፈር፣ አኗኗር፣ እና ርዕዮተዓለምን የሚያሳዩ እና የሚያመለክቱ እንደሆኑ ተስተውሏል። የብሔረሰቡ የተለያዩ ክፍሎች እና በተለያየ የማህበራዊ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች ምን ዓይነት የለቅሶ እና የቀብር ስነ-ስርዓት እንደሚፈፀምላቸው በጥናቱ ላይ ተመልክቷል። የቀሪዎቹም የስራ ክፍፍል እና ድርሻ በየታ፣ በማህበራዊ ደረጃ፣ በፅድሜ እና በህይወት ተሞክሮ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ በጥናት ሂደቱ ለማወቅተችሏል።

1. መግቢያ

የሃዘን ምክንያቱ በርካታ ነው። ሰው ሲከዳ ያዝናል፤ ሲጠቃ ያዝናል፤ ከወገኑ ሲለይ ያዝናል፤ ወዘተ.። መለየት፣ በተለይም በሞት መለየት በብዙ ባሕሎች ውስጥ ከባድ የሚባል የስሜት ቀውስን ይፈጥራል። ይሄ የተቃወሰ ስሜት ግን በአመዛኙ እንዲሁ አይለቀቅም። በባህል ይለዝባል፤ ይገራል፤ ሥርዓት ይይዛል። አንዱ ማኅበረሰብ ከሌላው ማኅበረሰብ ልዩነት ከሚፈጥርባቸው ዓበይት ፍክሎራዊ ክዋኔዎች መኃል አንዱ ሃዘኑን የሚገልጽበት ሥርዓት ነው። ይህ ጥናት የበናን ብሔረሰብ በማትኮር፣ ሠው ከወገኖቹ በሞት ሲለይ ማኅበሩ እንዴት ባለሁኔታ ሃዘኑን እንደሚገልጽ ለመመርመር ይሞክራል።

1.1 የጥናቱ ዳራ

ግለሰቦች የሚኖሩበት ማኅበረሰብ ባሕል ተገዢዎች ናቸው። ወደዚህ ዓለም ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ ያሳደጋቸውን ባህል እየለመዱና እየተማሩ ነው "ሰው" የሚሆኑት። በመሆኑም እንደተቀሩት ባሕላዊ ጉዳዮች ሁሉ፣ የሃዘን መግለጫ መንገዶች--የለቅሶ ሥነ ሥርዓቶች ከማኅበረሠቡ የአኗኗር ፈሊጥ፣ አመለካከትና ፍልስፍና የሚቀዱ ክዋኔዎች ናቸው።

አንድ ማህበረሰብ በሚያከናውነው የለቅሶ ሥነ ሥርዓት አማካይነት ስለ ሕይወት፣ ስለሞት፣ ስለሟች እና በህይወት ስላለ ሰው ያለውን ግንዛቤ እና አመለካከት መረዳት ይቻላል። በለቅሶው ሥነ ሥርዓት ወቅት አባላቱ የሚያከናውኗቸው የለቅሶ፣ የቀብር እና የማፅናኛ ሥርዓቶች፣ እንዲሁም ለለቅሶው ድምቀት እና ስምረት ሲባል የሚፈፅሟቸው ልዩ ልዩ ድርጊቶች የማኅበረሰቡ ዓይነተኛ መገለጫ ሆነው ይገኛሉ። በለቅሶው ወቅት የሚቀርቡት ልዩ ልዩ የስነ-ቃል ዓይነቶች፣ ክዋኔዎች፣የለቅሶ ማድመቂያ ልዩ ልዩ መሳሪያዎች (ቁሳቁሶች) እና ልዩ ልዩ ዓይነት እንቅስቃሴዎች (ረገዳ፣ ደረት መጣል፣ ፊት መቧጠጥ...) ለዚህ ዓይነተኛ ማሳያ ናቸው። እነዚህንም ዝርዝር የባህል ጉዳዮች በመመልከት ስለ ማህበረሰቡ እና ስለ ባህሉ አንድ አጠቃላይ የሆነ ነገር መናገር እና መግለፅ ይቻላል። ይህም የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ አንዱ የማህበረሰቡ እና የባህሉ ምንነት እና ማንነት ማሳያ መሆኑን የሚያስረግጥልን ነው።

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህንን ጥናት ለማድረግ መነሻ የሆኑኝ ሦስት ዓበይት ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው ምክንያት፤ በተለያየ ወቅት በመገናኛ ብዙኃንም ይሁን በልዩ ልዩ መድረኮች በሚካሄዱ ውይይቶች ላይ የደቡብ ክልልን አስመልክቶ የተለያዩ ነጥቦች ይነሳሉ። ከእነዚህ ነጥቦች መሃከልም ሠርክ በዋነኝነት የሚጠቀሱት የክልሉ ሰምሰም እና አረንጓዴ መሆን እንዲሁም በተለያዩ ባህሎች እና ትውፊቶች የበለፀገ መሆን ናቸው። ከእነዚህ ሁለት ነጥቦች መሃከልም በተለይ የክልሉ በባህል እና በትውፊት መበለፀግ ዘወትር የሚገለፅ ጉዳይ ነው። በተለይም በክልሉ፤ በደቡብ አሞ ዞን ውስጥ በርካታ የባህል እና የትውፊት ዓይነቶች መኖራቸው እና በዚህም ሳቢያ የቱሪስት ፍሰቱ ከፍተኛ እና ፈጣን መሆኑ በሰፊው ይነገራል። ከሚጠቀሱት የባህል ዓይነቶች መሃከልም የከብት ዝላይ፤ የኢቫንጋዲ ጭፈራ እና ዶንጋ (የቦዲ ማህበረሰብ የዱላ መከታ) ዋነኛዎቹ ናቸው። እናም ዘወትር እነዚህ እና እነዚህን መሠል ጉዳዮች ሲነሱ ስነ-ስርዓታቸው የደመቀ ኧና ክዋኔያቸው ዘርፈ ብዙ መሆኑ አብሮ ይወሳል። ለመሆኑ በእነዚህ ማህበረሰቦች አካባቢ የለቅሶ ስነ-ስርዓቱስ ምን ይምስላል? ክዋኔውስ እንዴት ያለ ነው? የሚለውን ጉዳይ ዘወትር አነሳ ነበር። ይህ ጉዳይ ደግሞ ብዙ ጊዜ ሲነሳ ባለመስማቱ ለጥናት ዋና መነሻ ምክንያት ሆኖኛል።

ሁለተኛ፤ እነዚህ ማህበረሰቦች በክዋኔ እና ከበራ ረገድ ዘወትር ተጠቃሽ ናቸው። ለመሆኑ በለቅሶ ስነ-ስርዓት ወቅትስ ያለው ክዋኔ እና ከበራ ምን ይመስላል? ከሚለው ጥያቄ ባሻገር በክዋኔው እና በከበራው ውስጥ ያለው መልዕክት እና ትርጉም ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ በሁለተኛ ደረጃ ለዚህ ጥናት መደረግ እንደ መነሻ የሚጠቀስ ነጥብ ነው። ሦስተኛው ምክንያት በእነዚህ ስነ-ስርዓቶች እና ክዋኔዎች አማካይነት ብሔረሰቡ ስለቀሪው ዓለም፤ ስለሞት፤ ስለሚች፤ ያለው አመለካከት እና ግንዛቤ ምን ይመስላል? እንዴትስ ይገለፃል? የሚለውንም ጥያቄ ከሌሎቹ ጋር አብሮ ለመመልከት በመሻት ነው። በእነዚህ ሦስት ዓበይት ምክንያቶች ሳቢያ ጥናቱን ለማድረግ ተነሳስቻለሁኝ።

1.3 የምርምር ጥያቄዎች

ለዚህ ጥናት መነሻ ከሆኑት እና በዚህም ጥናት ላይ ትኩረት ተደርጎባቸው መልስ ሊሠጥባቸው ከሚገቡ ጥያቄዎች መሃከል ሁለት ዓበይት የምርምር ጥያቄዎች ሲኖሩ በእነዚህ

ስር የሚመጡ ሦስት ንዑሳን የምርምር ጥያቄዎች አሉ። በበና ፀማይ ወረዳ ውስጥ የሚገኘው የበና ብሔረሰብ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ ሂደት ቅደም ተከተል ምን ይመስላል? በእያንዳንዱ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ ውስጥ ያለው ትርጉም ምንድን ነው? የሚሉት ጥያቄዎች የጥናቱ ዓበይት የምርምር ጥያቄዎች ናቸው። ከእነዚህ ስር የሚመጡት ደግሞ በበና ብሔረሰብ ዘንድ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ በተለየ መልኩ የሚደረግላቸው ሠዎች አሉ ወይ? በበና ብሔረሰብ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ ወቅት የማህበረሰቡ የስራ ድርሻ ክፍፍል ምን ይመስላል? እንዲሁም በበና ብሔረሰብ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔው ለምን ያህል ጊዜ ይቆያል? ምክንያቱስ? የተሠኙ ንዑሳን የምርምር ጥያቄዎች ናቸው። እነዚህን ሁለት ዓበይት እና ሦስት ንዑሳን የምርምር ጥያቄዎችን በተቻለ መጠን በጥናቱ ውስጥ ለመመለስ ተሞክሯል።

1.4 የጥናቱ ዓላማዎች

ጥናቱ ሁለት ዓበይት ዓላማዎች እና ሶስት ንዑሳን አላማዎች አሉት። የጥናቱ ዓበይት ዓላማዎች በበና ፀማይ ወረዳ በበና ብሔረሰብ ዘንድ ያለው የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ ምን እንደሚመስል ማሳየትና በእያንዳንዱ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ ውስጥ ያለውን ትርጉም መግለፅ ናቸው። ንዑሳን ዓላማዎቹ ደግሞ የበና ብሔረሰብ በክዋኔው አማካይነት ስለ ቀሪው አለም ያለውን አመለካከት መግለፅ፤ የብሔረሰቡ የህዘን ስሜት እና ክዋኔው ያላቸውን መስተጋብር ማመልከት እና የህዘን ስሜታቸውን በምን መልኩ እንደሚወጡ እና በዚህም ማህበራዊና ስነ-ልቡናዊ ጫናቸውን በምን መልኩ እንደሚያቀሉ ማስተዋወቅ ናቸው።

1.5 የመረጃ መሰብሰቢያ እና መተንተኛ መንገዶች

የአንድን ማህበረሰብ ባህል በቅጡ ለመረዳት እና ለማጥናት የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መጠቀም የግድ ነው። ለዚህም ሲባል ዋና ዋና ከሚባሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች መሃከል ከጽሑፍ መጠይቅ በስተቀር በተቻለ መጠን በተቀሩት መንገዶች ተገልግያለሁ። እነዚሁም ቃለ-መጠይቅ፤ ምልከታ እና የቡድን ተኮር ውይይት ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች በመረጃ ሰጪነት አገልግለዋል። በዚህ ጥናት ወቅት መስክ መውጣት አስፈላጊ እና ግዴታም ጭምር ነበር። ይሁን እንጂ ከመስክ ስራ በፊት አስፈላጊ የሚባሉ የቅድመ መስክ ዝግጅቶች አሉ። እነዚህም የመስክ ስራን የተቃና እና የተሳካ እንዲሆን የማስቻል አቅማቸው ከፍ ያለ ነው። ጎልድስቱይን (1964፤ 36-46) እንደሚለውም ከመስክ በፊት መሰራት ያለባቸው በርካታ ጉዳዮች

አሉ። እነዚህም በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችን መመልከት፤ ከዚህ በፊት በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የሚመሳሰል ጥናት ከሰሩ ሰዎች ጋር መገናኘት እና መወያየት፤ ከአካባቢው ሠዎች እና መሪዎች ጋር ተገናኝቶ ስለ ጥናቱ ማሳወቅ እና መረጃ መሰብሰብ እንደዚሁም ለስራው አስፈላጊ የሆኑትን መሳሪያዎች ማዘጋጀት ናቸው።

እኔም ጎልድስቴይን ያሰፈራቸውን ነጥቦች ከሞላ ጎደል በማሟላት ጥናቱን አካሂጃለሁ። ወደ መስክ ከመውጣቱ በፊት በእኔ ርዕስ ዙሪያ የተሰሩ የተለያዩ ጥናቶችን በመመልከት አስፈላጊና ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ። ይህ ደግሞ ለጥናቱ ጥሩ ጅምር ሰጥቶኛል። ከመስክ በፊትም የቤተ-መጻህፍትን ስራ በሚገባ ሰርቼ ብዙ ጠቃሚ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ። የቤተ-መጻህፍት ስራን ከጨረስኩ በኋላ እና ወደ መስክ ከመውጣቱ በፊት እዚህ ከተማ የሚገኙ የአካባቢውን ተወላጆች እና አካባቢው ዙሪያ ላይ የተለያየ ጥናት ያካሄዱ ሰዎችን በማግኘት ስለአካባቢው እና ስለብሔረሰቡ አጠቃላይ የሆነ መረጃ ሰበሰብኩ። ከዚህ በኋላ ነው ወደ መስክ ስራ ያመራሁት።

ከላይ የተጠቀሱትን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እያደጋገፍኩና እያስማማሁ ለመጠቀም ሞክሬያለሁ። እነዚህንም ዘዴዎች ለማሳካት እና ለማሟላት የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ተጠቅሜያለሁ። ክዋኔውን በማስታወሻ ደብተር ከመያዝ ጀምሮ በፎቶ ግራፍ ለማንሳት፤ በመቅረጸ ድምጽ እና በቪዲዮ ካሜራ ለመቅረጽ ሞክሬያለሁ። በምልከታ ወቅትም የብሔረሰቡ አባል ባለመሆኔ ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ *(non-participatory observation)* ለማካሄድ ተገድጃለሁ። ይሁን እንጂ ተፈጥሯዊውን አውድ በመጠቀም መረጃ በቅጡ ለመያዝ ሞክሬያለሁ። ከማህበረሰቡ ጋር በመቀራረብ እና በመግባባትም ተዓማኒነት እና ተቀባይነት ያላቸውን መረጃ አቀባዮችን በመጠቀም አጥጋቢ ሊባል የሚችል መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ።

ለዚህ ጥናት ማስኬጃነት ያገለግል ዘንድ ሃያ አንድ ሰዎችን ቃለ-መጠይቅ አድርጊያለሁ። እነዚህን ሃያ አንድ ሰዎች የመረጥኩትም የታላሚ ናሙና *(purposive sampling)* በመጠቀም ሲሆን፤ ሰባቱ ዋና መረጃ አቀባይ፤ ሁለቱ አስተርጓሚም ጭምር ሲሆኑ አስራ ሁለቱ ደግሞ ከተለያዩ የማህበረሰብ ደረጃዎች የተመረጡ ናቸው። እነዚህ ሃያ አንድ

ሰዎች ከማጠናው ጥናት ጋር ቁርኝት ያላቸውና ስለብሔረሰቡም ሆነ ስለ ባህላዊው ክዋኔ በቂ እውቀት ያላቸው፤ በአካባቢው ሰዎች ዘንድ የተከበሩና የሃገር ሽማግሌዎችም ጭምር ናቸው። እነዚህንም ከጥናቱ ዓላማ ጋር የሚመቹ እና የሚመለከታቸው በመሆኑ የታላሚ ናሙና ዘዴን በመጠቀም የተለያዩ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ። እነዚህንም ዘዴዎች በመጠቀም የተገኙትን መረጃዎች ክዋኔን ማእከል ያደረገ *(performance centered approach)* ዘዴን በመጠቀም እተነትናለሁ። ይህንንም መሠረት በማድረግ ትኩረቱ የለቅሶው ስነ-ስርዓት ላይ ያሉትን ክዋኔዎች፤ አውድ፤ ከዋኝ፤ መልእክት፤ አቀራረብ፤ ወዘተ... ምን እንደሚመስሉ እየተነተንኩ አሳያለሁ።

1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ወሰኑን ያደረገው በበና ፀማይ ወረዳ በበና ብሔረሰብ ዘንድ የሚደረገውን የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔን በማሳየት ላይ ነው። በበና ብሔረሰብ ዘንድ ለተለያዩ የማህበረሰቡ ክፍሎች የሚደረጉትን የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔዎች ምን እንደሚመስሉ አመለክታለሁ። ለዚህም ይሆን ዘንድ የአንድ ጎልማሳን የቀብር ስነ-ስርዓት እንደማሳያነት እየተጠቀምኩ የሌሎቹን የማህበረሰቡን ክፍሎች የለቅሶ ስነ-ስርዓት በየክዋኔው መሀል እያያያዝኩ አቀርባለሁ። ስለዚህም ወሰኔ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔያቸው ላይ ብቻ ይሆናል። ክዋኔውም ቢሆን ስነ-ቃሉን የሚያጠቃልል አይሆንም። የቋንቋ ችግር እና አለመግባባት በመኖሩ ሳቢያ ስነ-ቃሉ ላይ ትኩረት አላደርግም። ይልቁንስ ከዋኔውን በተገቢው ሁኔታ እየተመለከትሁ እቃኝዋለሁ።

1.7 የጥናቱ ውጤት ጠቀሜታ

"የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ በበና ፀማይ ወረዳ" በሚል ርዕስ የተዘጋጀው ይህ ጥናት ውጤቱ ዘርፈ ብዙ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብዬ እገምታለሁ። ከእነዚህ ጠቀሜታዎች መካከልም ብሔረሰቡ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔን እንዴት ያካሂዳል የሚለውን ያሳያል። ብሔረሰቡን ከማስተዋወቅ በዘለለም እያንዳንዱ ክዋኔ ያለው ትርጉም ምን እንደሆነ ያሳያል። በተራዛሚውም በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች የሚያካሂዷቸው ባህላዊ ክንዋኔዎች

ትርጉመ ቢስ እንዳልሆኑ እና እያንዳንዱ ቅንጣት ነገር በቅጡ መታየት እና መተንተን እንዳለበት ግንዛቤ ያስጨብጣል ተብሎ ይታሰባል።

1.8 በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

በዚህ ጥናት ወቅት የተለያዩ ችግሮች ገጥመውኛል። ከእነዚህም መካከል ዋነኛው ጥናቱ ትኩረቱን ያደረገው በለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ ላይ እንደመሆኑ ትክክለኛ ለቅሶ ማግኘት ነበረብኝ። ይሁን እንጂ ትክክለኛ ለቅሶ ለማግኘት በጣም ተቸግሬ ነበር። ለዚህ ደግሞ እንደምክንያት የሚጠቀሰው የብሔረሰቡ ባህል ነው። በብሔረሰቡ ዘንድ ባላባት የሞተ እንደሆነ ሳይቀበር እስከ ሁለትና ሶስት አመታት ድረስ ሊቀመጥ ይችላል። ይህ ክዋኔውን ወዲያው ለማግኘት አንዱ ችግር ነበር። ሌላው ደግሞ በብሔረሰቡ ዘንድ ያለው የሞት ቁጥር መቀነስና የውልደት ቁጥር መጨመር ነበር። ይህንን መረጃ ያገኘሁት ከዞኑ የማዕከላዊ እስታትስቲክስ ቢሮ ሲሆን ለማረጋገጥ ወደ ወረዳው ሄጄ የብሔረሰቡን አባላት አናግሬ ነበር። አቶ ቃሮ ቡኔ የተባሉት አዛውንት፣ *"እዚህ አካባቢ እኮ ለቂሰ ታሎ ታሎ የለም። በብዙ ጊዜ አንድ ነው የሚንሰማ... አሚስት ሰባት በአንድ አመት ግዜ ከሞተ ሰው አምላክ ተቆጣ ብለን ባላባት ጋር ሄደን ይቅርታ እንዲደረጊልን እና ሞቱም እንዲወጣ ኢንለምናለን እንጂ ታሎ ታሎ ለቂሰ የለም።"* ብለው ገልጸውልኛል። በዚህም ሳቢያ ዋና ለቅሶ አስኪገኝ ድረስ ከአንድ ወር ላላነሰ ጊዜ ለመጠበቅ ተገድጀ ነበር።

ሌላው ጎልቶ የታየው ችግር በቃለ-መጠይቅ፣ በቪዲዮ ቀረጻ እና በፎቶ ግራፍ ማንሳት ወቅት እጠየቅ የነበረው የገንዘብ መጠን ነው። በ17/08/2003 ዓ.ም ለቅሶ ተገኝቶ ወደ ለቅሶ ቤት ሄድኩ። ቢሆንም አንዳችም ፎቶ ሆነ ቪዲዮ እንዳልቀርጽ ተከለከልኩ። ከትንሽ ንግግር በኋላ የሟች ታናሽ ወንድም መጥቶ የውጪ ሀገር ገንዘብ ከሰጠሁት ችግር እንደሌለ ነገር ግን በእኛ ሀገር ገንዘብ ከአንድ ሺህ ብር በታች እንደማይቀበለኝ ገለጸልኝ። ሌላ ለቅሶ ለመፈለግና ለመጠበቅ ግዜ ስለማይበቃኝ ተከራክሬ 740 ብር ከፍዬ እንድቀርጽ ተፈቅዶልኛል። ከዚህም ሌላ ቃለ-መጠይቅ የማደርግላቸው ሰዎች በየጊዜው ይጠይቁኝ የነበረው ገንዘብ ትልቅ ችግር ፈጥሮብኝ ነበር። የለቅሶው ቦታ በተቀየረና ግዜ በረዘመ ቁጥር ገንዘብ ጨምር እየተባልኩ ስራዬን እንዳቆም እገደድም ነበር። በኋላም በተቻለ መጠን ከ20-70 ብር በተለያየ ጊዜ እየጨመርኩ ስራዬን ቀጥያለሁኝ። ለዚህ እንደ ዓቢይ ምክንያት ተደርጎ

የሚወሰደውም በየጊዜው ወደ አካባቢው የሚመጡት የውጪ ሀገር ጎብኚዎች ከፍተኛ ገንዘብ ስለሚሰጧቸው እንደሆነ የአካባቢው አስጎብኚ ማህበር አባል የሆነው አቶ ማሙሽ ገልጸልኛል።

2. ክለሳ ድርሳን

2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህኛው የጥናት ጽሁፍ ክፍል ውስጥ የለቅሶ እና የቀብር ስነስርአት ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ የተለያዩ ጽሁፎች ተቃኝተዋል። አቀራረባቸውም በተዘጋጁበት ዘመን ቅደም ተከተል መሠረት ነው። በመጀመሪያ የምንመለከተው ርእሰ ጉዳዮቹን አንስተው የተሰሩ የመመረቂያ ጽሁፎችን ነው። በመቀጠልም በተለያዩ መጻሕፍት ላይ የተገኙ ጽሁፎች ይቀርባሉ። የዚህ ቅኝት ዋና አላማም ርእሰ ጉዳዮቹ እንዴት እንደተዘጋጁ፤ የትኩረት አቅጣጫቸው ምን እንደሚመስል እና ከዚህ የጥናት ጽሁፍ ጋር ያላቸው ተመሳስሎ እና ልዩነት ምን እንደሆነ ማመልከት ነው። በተለይ የትኩረት አቅጣጫቸው ምን ላይ ያተኮር እንደነበር በማሳየት ከዚህ ጥናት በኋላም ርእሰ ጉዳዩ በተለየ መልኩ እንዲቃኝ አቅጣጫ ለመጠቆም ነው።

በመጀመሪያ የምንመለከተው ሐረገወይን ድፋባቸው የተባለችው አጥኚ ያቀረበችውን ፅሁፍ ነው። ሐገረወይን በ1974 "የክስታንኛ የለቅሶ ግጥሞች" በሚል ርዕስ ጥናቷን አካሂዳለች። ጥናቷ ትኩረቱን ያደረገው የክስታኔ ማህበረሰብን የለቅሶ ሁኔታ በማስተዋወቅና የመ.ሽ ግጥሞችንም ይዘት በመተንተን ላይ ነው። አጥኚዋ በመጀመሪያ የብሔረሰቡን ታሪካዊ ዳራ እና አመጣጡን እንዲሁም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ገፅታውን አሳይታለች። ከዚህ በመቀጠልም የብሄረሰቡ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ምን እንደሚመስል ገልፃለች። በዚህ ክፍል ሥር በስርዓቱ ውስጥ ወንዶችና ሴቶች ያላቸውን የተለያየ ሚና የገለፀች ሲሆን የቀብር ስነ-ስርዓቱ እንደ ሟቹ የትውልድ ቦታ እና ደረጃ፣ ያታና መ.ያ እንዲሁም በእድሜ ደረጃ እንደሚለያይ ገልፃለች። ከዚህ በኋላም የመ.ሽ ግጥሞቹን በያታ፣ በዕድሜ፣ በመ.ያ በመመደብ የይዘት ትንተና አካሂዳባቸዋለች።

አጥኚዋ በጥናት ጽሁፏ ውስጥ አንዳንድ ትኩረት ያልሰጠቻቸው ነጥቦች አሉ። ከእነዚህም መሃከል የመረጃ አሠባሠብ ዘዴ.ጂን በግልፅ ያልጠቀሰች ሲሆን በተጨማሪም ምንም አይነት ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ አልሰጠችም። በተጨማሪም በትንታኔዋ የቀብር ስነ-ስርዓቱ እንደ ሟቹ መ.ያ የሚለያይ መሆኑን በደፈናው ብትጠቁምም፣ የትኛው መ.ያ ምን ዓይነት ስነ-ስርዓት እንደሚከናወንለት አላሳየችም።

ሌላኛው ከዚህ ርዕስ ጋር በተያያዘ የተሠራው ጥናት አየለ መሎሬ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ነው። ይህ በ1986 ዓ.ም የተዘጋጀው ጥናት "የሀዲያ ህብረተሰብ የለቅሶ ስነ-ስርዓት" የሚል ርዕስ የያዘ ነው። አጥኚው በጥናቱ ፅሁፍ ላይ ሁለት ዓበይት ጉዳዮችን አንስቶ ተመልክቷል። አንደኛው የለቅሶ ስነ-ስርዓት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የለቅሶ ግጥሞች ናቸው። የለቅሶ ስነ-ስርዓትን በተመለከተበት ክፍል የቅድመ ቀብር የለቅሶ ስነ-ስርዓት ምን እንደሚመስል፤ ሕፃናትን፣ወጣቶችን እና ሙሽሮችን በዋቢነት እየጠቀሰ ተመልክቷል። በተጨማሪም ለአዛውንቶች፣ ለስጋደዊ ህመምተኞች፣ ለጤነኞች እና ለጀግኖች የሚደረጉ የቅድመ ቀብር የለቅሶ ስነ-ስርዓቶችን እና ከቀብሩ በኋላ ደግሞ በፅለተ ሰልስትና በፅለተ አርባ እንደዚሁም የመቃብር ላይ ተግባሮችና የሽመት ርክክቡ ምን እንደሚመስል ስነ-ስርዓቱን ተመልክቷል። በሁለተኛው ዓበይ ጉዳዩ ላይ ደግሞ ዘረ ብርቱዎች፣ በውጊያ ላይ ጀግንነት ያሳዩ፣ አድነው የገደሉ ጀግኖች፣ ሃብታም የሆኑ ሠዎች፣እንደዚሁም ጨቋኞች ሲሞቱ የሚገጠምላቸውን ግጥሞች አሳይቷል።

በጥናቱ ውስጥ ለእያንዳንዱ ርዕሠ ጉዳይ አንዳንድ ግጥሞችን ብቻ በማምጣት ከፊት ለፊት የሚታየውን የግጥሞቹን ሀሳብ እና ይዘታቸውን ብቻ ነው የገለፀው። እነዚህ ገለፃዎች አጥኚው በአላማው ላይ ያስቀመጠውን የህብረተሰቡን ማህበራዊ ጉዳዮች በግጥሞቹ አማካይነት ለመመርመር ዓቅም የሚጎድላቸው ይመስለኛል። ስለዚህም ዓላማው ጥሩ ቢሆንም በጥናቱ ሂደት ወቅት ግን ግቡን አልመታም።

አጥኚው ለጥናቱ ማስኬጃ እና መቀንበቢያ የሚሆን አንዳችም ብያኔም ሆነ የንድፈ ሃሳብ አቅጣጫ አላሰፈረም። የመቀንበቢያ ንድፈ ሀሳብ አለማበጀቱም የርዕሠ ጉዳይ መስፋት እንዲያጋጥም ምክንያት ሆኗል። የመረጃ አሠባሰብ ዘዴዎቹን ስንመለከትም በተለይ አጋጣሚዎችን እየተጠቀመ እንደሰበሰበ እንደዚሁም ቃለ-መጠይቅ እና ምልከታ ማካሄዱን ገልጿል። ይሁን እንጂ ምልከታው ከተካሄደ የቆየ እና ረዘም ያለ ጊዜ ስለሆነው አንዳንድ የሚረሡ ነጥቦች መኖራቸውን መገመት አያዳግትም። ይህም በጥናቱ ላይ አንዳች ጉድለት ማስከተሉ አይቀሬ ነው።

በመቀጠል የምንመለከተው ወርቁ ማንደፍሮ የተባለው አጥኚ በ1987 ዓ.ም ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበውን የጥናት ፅሁፍ ነው። የጥናት ፅሁፉ ርዕስ "በሊቦ ከምከም ወረዳ የለቅሶ ስነ-ስርዓትና የሙሾ ግጥሞች" የተሠኘ ነው። ይህ ጥናት ትኩረቱን

ያደረገው በሊቦ ከምከም ወረዳ አንድ ሰው ነፍሱ ከስጋው ከተለየችበት ጊዜ አንስቶ እስኪቀበር ድረስ ያለውን የለቅሶ ሥነ-ሥርዓት ነው። በተጨማሪም የሙሾ ግጥሞችን ከባህላዊ እና ኃይማኖታዊ ክዋኔዎች አንጻር ለመመልከት ሞክሯል። የዚህ ጥናት ዓቢይ ትኩረት የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ ነው። በቅድሚያ በዕለተ ሞትና ድኅረ ሞት የሚከናወኑ ስርዓቶች ምን እንደሚመስሉ ለማሳየት የሚሞክረው ይሄ ጽሑፍ ስነ-ስርዓቱ እንደየሚቹ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሀይማኖታዊ ሁኔታና ደረጃ እንደሚለያይ ያስረዳል። ከጥናቱ አላማዎች መሀከልም "ህብረተሰቡ በግጥሞቹ አማካኝነት የራሱን ማህበራዊ እሴት ወይም አሻራውን እንዴት ያሳያል? የሚለውን ለማሳየት" የሚል ይገኛል። ይሁን እንጂ በጥናቱ ዕሁፍ ላይ እንደታየው አጥኚው ክዋኔውን እና ግጥሞቹን በመመልከት ቀለል ያለ የይዘት ትንተና ነው ያካሄደው። የህብረተሰቡ ማህበራዊ እሴት እና አሻራ ይህንን ይመስላል እያለ የገለፀውና የዘረዘረው ነገር የለም።

በመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ረገድ ጠንካራ ጎኖቹ በዛ ያሉ ቢሆኑም እንኳን ክፈተት ከማሳየት አላመለጠም። ከእነዚህ ክፍተቶቹ መካከል በብዛት ለመረጃዎቹ ራሱን በዓቢይ የመረጃ ምንጭነት መውሰዱ ነው። ይህም በዕሁፉ ውስጥ በጣም በመብዛቱ ሳቢያ የጥናቱን ሚዛናዊነት እና ተአማኒነት ሊያዛባው ይችላል። ሌላው በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ለጥናት ባይፈቀድለትም የማህበረሰቡ አባል በመሆኑ እያገለገለ በመምሰል ጥናቱን እንዳካሄደ ገልጿል። ይህ "ስለላ" ከጥናት (አጥኚ) የስነ-ምግባር ደንቦች ውጪ መሆን ነው። ከዚህም ሌላ በጣም በርከት ያሉ ግጥሞችን በአባሪ ውስጥ ያሰፈረ ሲሆን በጥናቱ ውስጥ ያሉትን ግጥሞች ግን በምን ምክንያት ወይም መስፈርት መርጦ እንደተገለገለባቸው በጥናቱ አልገለፀም። የጥናቱን ወሰን ባለመግለፁ እና ባለመወሰኑም ብዙ ክፍሎችን በመዘርዝር መልኩ እንዲነካካ አስገድዶታል።

ሌላው ለቅኝት የተመረጠው ሥራ አህመድ መሀመድ በ1989 ዓ.ም ያቀረበው የዲግሪ ማሚያ ዕሁፍ ነው። አህመድ "በአሪ ብሔረሰብ የቢዩ ባላባታዊ ቤተሰብ እና የለቅሶ ስርዓቱ" በሚል ርዕስ ጥናቱን ያካሄደ ሲሆን የጥናቱን ዋና ትኩረትም ያደረገው በአካባቢው ያሉ እና በተለያዩ ጊዜያት ስልጣን ላይ የወጡ ባላባቶች ሲሞቱ በለቅሶው ወቅት የሚካሄደው የንግስና ስርዓት እና "የጎድሚዎች" ሚና፣ የህዝቡንና የባላባቱን ትስስር እንዲሁም ባላባት ለመሆን የሚያስፈልጉ መመዘኛዎች ላይ ነው። በማያያዝም በባላባታዊ ቤተሰቡ የለቅሶ

ስርዓት ላይ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ምን እንደሆኑ፤ አይነትና ጠቀሜታቸው እንዲሁም በግልጋሎት ላይ ከሚውሉበት አጋጣሚ አንፃር ምን እንደሚመስሉ ተመልክቷል። የቀበሩ እና የለቅሶው ሂደትም ከሌላው የብሔረሰቡ አባላት ጋር የሚለይባቸውን ነጥቦች አንስቶ አስተዋውቋል።

አላስፈላጊ ወጪ እና ድርጊቶች ያላቸው፤ ኢኮኖሚን እና አካላዊ ጤንነትን የተመለከቱ ጉዳዮችን "ተዉ!" ከማለት ይልቅ ጉዳቱን እያሳዩ አራሳቸው እንዲተዉት ትምህርት መስጠት አስፈላጊ መሆኑን እና ዓላማውም ይህ እንደሆነ አስምሮበታል። ይሁን እንጂ እነዚህን ነገሮች ከባህሉ አንጻር ውስጥ ገብቶ የተመለከታቸው ይሁን ዳር ቆሞ የታዘባቸው የገለጸው ነገር የለም። አጥኚው የጥናቱ ጠቀሜታ "ጎጂ ባህሎች" እንዲተዉ ትምህርት መስጠትና ሁሉም የማህበረሰቡ አባል እኩል መሆኑን የማሳየት ነው ይላል። "ጎጂ ባህሎች" ብሎ የፈረጃቸዉን እና እንዲተዉ የፈለጋቸው ጉዳዮችን ከማን አንጻር እንደተመለከታቸው አልገለጸም። የባህል አጥኚ እንዲህ የማለትና ውሳኔ የመስጠት ሀላፊነት ያለበት አይመስለኝም።

አጥኚው በተወሰነ መልኩ ክፍተት ያሳየበትና እንደ ጉድለት የተመለከትኩበት ነጥብ በመረጃ አሰባሰብ ዘዴው ላይ ነው። አህመድ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴውን በብዛት ያደረገው ቃለ መጠይቅ እና የሰነድ (የፅሁፍ) ምንጭ ነው። ክዋኔን ያለ ምልከታ ማጥናት እጅግ በጣም ከባድ እና አስቸጋሪ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። አህመድ ጥናቱን በተለይ የአካባቢውን አረጋውያንን በማነጋገር፣ ጥናታዊ ፅሁፎችን በማገላበጥ እና ከልምድና ግንዛቤ በመነሳት እንደሰራው ገልጿል። ከዚህ በፊት በወርቁ ላይ ያየነው እራስን ዋና ምንጭ የማድረግ ችግር በዚህም ላይ ተስተውሏል። በጥናት ወቅት ራስን ውጭ አድርጉ በልዩ አይን መመልከት ተገቢና አስፈላጊ ነው። ከዚህ ሌላ እንደ ጠንካራ ጎን አድርጌ የወሰድኩት "ባላባት" የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ብያኔውን፣ አገልግሎቱንና ኃላፊነቱን ከማህበረሰቡ አንፃር እየተመለከተ ተንትኗል። ይሁን እንጂ አንድም ክዋኔን የተመለከተ ንድፈ-ሃሳባዊ ዳራ እና አካዳሚያዊ የሆነ የብያኔም ሆነ የማስተዋወቂያ ፅሁፍ አላሰፈረም። በመጨረሻም አጥኚው ለፅሁፉ በሰጠው መደምደሚያ ላይ የጥናቱን ግኝቶች፣ አንዳንድ ጥቆማዎችን እና ይሁንታዎችን አካቶበታል።

"በጎፋ ብሔረሰብ ባህላዊ ለቅሶ (ዬሆ) ግጥሞች ክዋኔና ስነ-ግጥማዊ ገጽታ" በሚል ርእስ ሌላው የተሰራው ጥናት በዘላለም ኢዮብ በ1995 ዓ.ም ነው። ዘላለም በዚህ ስራው ላይ ትኩረቱን ያደረገው በጎፋ ብሔረሰብ ያለውን የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔን መመልከት እና በለቅሶው አጋጣሚ የሚባሉትን ግጥሞች ስነ-ግጥማዊ ገፅታ ማመልከት ነው። በዚህም ውስጥ በለቅሶው ወቅት የለቀስተኞች ባህላዊ አቀማመጥ እና የአቋቋም ስርዓታቸው ምን እንደሚመስል፤ የእዝን ሁኔታው እንዴት ያለ እንደሆነ፤ እንደዚሁም ለህፃናት፤ ለወጣቶች፤ ለጎልማሶች እና ለአዛውንት የሚደረጉት ባህላዊ የአለቃቀስ ስነ-ስርዓቶች ምን እንደሚመስሉ ገልጿል። ከዚህም ሌላ የለቅሶው ቅድመ ዝግጅት ስነ-ስርዓትና የመቃብር አዘገጃጀት እንዲሁም የቀብር ስነ-ስርዓቱ ምን እንደሚመስል አሳይቷል። ከዚህም በኋላ "ሚሻዬሆ" እና "ባለዬሆ" የተባሉትን ከቀብር በፊት ያሉትን የለቅሶ ሂደቶች እና "ዶቻዬሆ" የሚባለውን ከቀብር በኋላ ያለውን የለቅሶ ክዋኔን ገልጿል። በመቀጠልም የጎፋ ብሔረሰብ የለቅሶ ግጥሞችን የቃላት ምርጫ እና ምስል ፈጠራን ተመልክቷል። በመጨረሻም ልጆች ሲሞቱ፤ ወጣቶች ሲሞቱ፤ አዋቂዎች ሲሞቱ እና አዛውንቶች ሲሞቱ የሚገጠሙትን የለቅሶ ግጥሞች ከአጫጭር መግለጫዎቻቸው ጋር አሳይቷል።

አጥኚው በመግቢያው ላይ አጠቃላይ የሆነ ገለፃ እና ክዋኔ ለሚለው ቃል የተሰጡ ብያኔዎችን አስፍሯል። የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎቹን ስንመለከት አካባቢውን ለይቶ በማወቅ እንደመረጠ፤ በኋላም በየአካባቢው አሉ የተባሉትን ሽማግሌዎችን እና መምህራንን በተለያየ መንገድ ቃለ መጠይቅ እንዳደረገ፤ እንዲሁም የአካባቢው ተወላጅ በመሆኑ ከራሱ የሚያውቀውን እንዳካተተ ገልጿል። ይሁን እንጂ እዚህ ላይ እንደ ክፍተት ያስተዋልኩት የአካባቢው ተወላጅ እንደመሆኑ ተሳታፊ ምልከታ *(Participatory observation)* ማካሄድ ነበረበት። ክዋኔን ያለ ምልከታ በሚገባ መልኩ መገንዘብና መግለፅ አስቸጋሪ ይመስለኛል።

በግጥሞቹ ዙሪያ ባቀረበው ጽሁፍ ውስጥ ደግሞ አጥኚው በመጀመሪያ የስነ ግጥምን ምንነት እና አበይት ባህሪያቱን አጠር ባለ ሁኔታ አስተዋውቋል። ይሁን እንጂ ያስተዋወቀበት መንገድ እና የሰበሰባቸውን ግጥሞች የተመለከተበት እና የተነተነበት መንገድ ተያያዥነት የሌላቸው ናቸው። ምክንያቱም የግጥም ባህሪያቱን በመጠኑም ቢሆን ከገለፀ በኋላ ግጥሞቹ ላይ ግን ከላይ (ከፊት ለፊት) የሚታየውን የይዘት ትንተና ብቻ ነው ያካሄደባቸው። ከዚህም ሌላ በአባሪው መሃከል በጥናቱ ውስጥ የተጠቀመባቸውን ግጥሞች በምን መስፈርት

መርጦ እንደተመለከታቸውና ገለፃ እንዳነሄደባቸው አላመለከተም። ሌላው በጥናቱ ውስጥ የወጥነት ችግር የሚስተዋልበት ነጥብ በመረጃ አሰባሰብ ዘዴው ላይ ያልተጠቀሰ ነገር ግን በአባሪው ላይ የሰፈሩ በርካታ ፎቶግራፎች ይገኛሉ። ዓላማውና ግኝቶቹም ተያያዥነት የሚጎላቸው ናቸው። አላማ አድርጎ የተነሳው ነገር በመጨረሻ ግኝቱ ላይ ግቡን ሲመታ አልተመለከትኩም። ጥናቱም በንድፈ-ሃሳባዊ ዳራ የተደገፈ ነው ለማለት ያስቸግራል።

አስቴር አንጀሉ በ1997 ዓ.ም የሠራችው ጥናት ሌላው በለቅሶ ርዕሠ ጉዳይ ላይ የተዘጋጀ ነው። ጥናቱ "የጋሞ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት" የተሠኘ ርዕስ ተሰጥቶታል። ጥናቱ ትኩረቱን ያደረገው በጋሞ ብሔረሰብ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ላይ ነው። በዚህም ጥናት ላይ ከቀብር በፊት፤ በቀብር ጊዜ እና ከቀብር በኋላ የሚከናወኑ ስርዓቶች ምን መልክ እንዳላቸው ተገልጿል። ሌላኛው ትኩረቱ የጋሞ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት እና የግጥሞቹ ይዘታዊ ትንተና ላይ ነው። አጥኚዋ በጥናት ፅሁፏ ውስጥ እነዚህን የለቅሶ ግጥሞች ከፅድሜ አንባር፤ ወጣት፤ጎልማሳ፤እና አዛውንት ሠዎች ሲሞቱ የሚከናወኑ የለቅሶ ስነ-ስርዓቶችን እና የግጥሞቹን ይዘታዊ ትንተና ያሳየች ሲሆን የተቀረውን በቤተሠብ ደረጃ፤ ከሙያ አንፃር የሚገጠሙ ግጥሞች እንደዚሁም ማህበራዊ (ኢኮኖሚያዊ) ደረጃን የሚገልፁ ግጥሞች በሚሉ ክፍሎች መድባቸዋለች።

ከአላማዎቿ መሀከል በተለይ ሁለቱ ከጥናቱ ጋር የተገናኙ ናቸው። አንደኛው የሙሾ ግጥሞችን ሠብስቦና በይዘት በመፈረጅ ተንትኖ ማቅረብ የሚል ሲሆን ሁለተኛው "የጋሞ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ያለውን የባህል ተዛምዶና ልዩነቱን ለይቶ ማሳየት" የሚሉ ናቸው። በጥናት ፅሁፏ ውስጥ እንደተመለከትኩት የሙሾ ግጥሞቹን በይዘት ረገድ በመፈረጅ ተንትና አቅርባለች። የለቅሶውን ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ያለውን ተዛምዶና ልዩነት ግን በቂ ሊባል በሚችል ሁኔታ አላቀረበችውም። ከሁለት ማህበረሰቦች ጋር በጣም በቀጭን የመገናኛ መስመር እና አጠር ባለ ሁኔታ ብቻ ነው አገናኝታ ያቀረበችው። ትንተናዋንና ምልከትዋን ከዓላማዋ ግዘፈት ጋር የሚመጣጠን ሆኖ አላገኘሁትም። ሌላው ለግጥም ክፍሏ በተቻለ መጠን ብያኔዎችን እና የግጥም ዋነኛ ባህሪያትን በመግለፅ የሰበሰበቻቸውን ግጥሞች ከእነዚህ ባህሪያት አንፃር እየተመለከተች አቅርባለች። ነገር ግን ጥናቱ ክዋኔንም ያካተተ በመሆኑ ስለ ክዋኔ ያነሳችው አንዳችም ብያኔ የለም።

ፈለገ ህይወት ዘገዩ "በባንጃ ሽኩዳድ ወረዳ የቀብር ሥነ-ሥርዓትና የለቅሶ ግጥሞች ስብስብ ይዘት ትንተና" በሚል ርእስ በ1997 ዓ.ም. የጥናት ጽሁፏን አቅርባለች። ፈለገ ህይወት በዚህ ጥናቷ ላይ ስለ ባንጃ ሽኩዳድ ወረዳ አጭር ታሪካዊ ዳራ በማስቀመጥ ፅሁፏን ትጀምራለች። በመቀጠልም የባንጃ ሽኩዳድ ወረዳ የቀብር ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም፣ ከቀብር በፊት ያለው ስነ-ስርዓት፣ የቀብር ስነ-ስርዓት እና ከቀብር በኋላ ያለው ስነ-ስርዓት ምን እንደሚመስል ገልፃለች። በመቀጠልም በለቅሶው ስነ-ስርዓት ጊዜ የእድሮች እና የማህበራት ሚና፤ ለሟች የሚደረጉ ኃይማኖታዊ ስርዓቶች (ቁርባን) ወይም "አርባ"፣ የቀጠሮ፣ የመርዶ ለቅሶ የሚባሉትን ስነ-ስርዓቶች እየዘረዘረች ገልፃለች። ይህንን ስራ ከሌሎቹ ለየት የሚያደርገው አጥኚዋ በለቅሶ ስነ-ስርዓት ወቅት የእድሮችን እና የማህበራትን ሚና በመመልከቷ ነው። ይህ ጉዳይ በተለይ ከማህበራዊ የህይወት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ነጥቦችን ሊጠቁም ይችላል። ባካሄድኩት ምልከታ ይህንን ጉዳይ የተመለከተ ሌላ ጥናት እስከ አሁን ድረስ አላጋጠመኝም።

አጥኚዋ በጥናቷ ላይ ስለ ክዋኔ ምንነት አንድ ብያኔ ብቻ ያስቀመጠች ሲሆን ስለ ስነ-ቃል የተወሠነ ነገር ብቻ በማለት አልፋለች። እዚህ ላይ በተለይ ስለግጥም ሰፋ ያለ ነገር ማለት ነበረባት። ምክንያቱም ጥናቷ ትኩረቱን የሚያደርገው በግጥሞቹ የይዘት ትንተና ላይ በመሆኑ። ነገር ግን ስለ ግጥምም ሆነ ስለ ይዘት ትንተና ምንነት እና እንዴትነት ምንም አልገለፀችም። የጥናቷን ዘዴዎች ስንመለከት፣ ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ ውይይት፣ የሰነድ (የፅሁፍ) ምርመራ አድርጌያለሁ ብላ በመቀጠል "እንደ ይዘታቸው ተቀራራቢነት እና ልዩነት በመመደብ እና በመከፋፈል" የተወሰኑትን ግጥሞች መርጣ እንደተነተነች ገልፃለች። ይሁን እንጂ በጥናቷ ውስጥ ያሉት ግጥሞች የተመረጡት በይዘት ሳይሆን በያታ መመደቢያነት ነው። በዚህም በጥናቷ ላይ የወጥነት ችግር ታይቷል።

ተሾመ መሉጌታ በ1998 ዓ.ም ያቀረበው የዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ ሌላው የለቅሶ ስነ-ስርዓት ላይ ትኩረቱን አድርጐ የተሠራ ጥናት ነው። ጥናቱ "በቤንሻንጉል ጉመዝ በድባጢ ወረዳ የለቅሶ ስነ-ስርዓት" የሚል ርዕስ ያለው ነው። ጥናቱ ትኩረቱን ያደረገው የጉመዝ ብሔረሰብ የለቅሶ ስነ-ስርዓትና የቀብር ጉድጓድ አዘገጃጀት ላይ ነው። ተሾመ በጥናት ፅሁፉ ውስጥ ወጣት ሲሞት፣ አዛውንት ሲሞት፣ ሰው ገዳይ ሲሞት፣ አውሬ የገደለ ሲሞት፣

በጥይት የተመታ ሲሞት የሚደረገውን የለቅሶ ስነስርዓት እና የሚደረደሩትን የሙሾ ግጥሞች እየዘረዘረ አሳይቷል። ከዚህም ሌላ ተገቦር (የሞት ጠላ) ስለሚባለው ስነ-ስርዓት ገልጿል።

በዚህ ጥናት ላይ የታየው ክፍተት በመረጃ አሠባሠብ ዘዴው ላይ ነው። የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ ናቸው ብሎ ምልከታን፤ ቃለ መጠይቅን እና ከተለያዩ መጣጥፎች እና ዕሁፎች ላይ የተገኙ መረጃዎችን በምንጭነት እንደ ተጠቀመ ገልጿል። ይሁን እንጂ በቀጣዩ የጽሁፍ ክፍል ውስጥ እንደገለፀው በአካባቢው የለቅሶ ስነ-ስርዓት እንዳላገኘና እንዳልተጠቀመ ገልጿል። በዚህም ሳቢያ ክዋኔው ላይ ሳይገኙ ምልከታን ተጠቅሜያለሁ ማለት በመረጃ አሰባሰብ ዘዴው ላይ አንዳች ያልጠራ ነገር እንዳለ ይጠቁማል። "ምልከታ" የሚለውንም ለመረጃ አሠባሠብ ዘዴዎች ፍጆታ ብቻ የተጠቀመበት ሆኖ አግኝቼዋለሁ። የጥናቱ ዓላማዎች ተብለው ከተዘረዘሩት መሀከል "ለብዙ ዘመን የኖረው የለቅሶ ስርዓት እየተለወጠ፤ እየጠፋ እና እየተረሳ ስለመጣ...." የሚል ነጥብ አለ። ስነ-ስርዓቱ ለምን እንደዚህ እየሆነ እንደመጣ እና ለውጡ በምን ምክንያት እንደተከሰተ በጥናቱ ውስጥ አልተገለፀም። ሌላው በጥናት ዕሁፉ ውስጥ የአንዱን ርዕሰ ጉዳይ ከአንዱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር የማቀላቀል ነገር ይስተዋላል። "የጥናቱ ወሰን" በማለት ወሰነ ጥናቱን እና አንዳንድ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎቹንም አብሮ እየቀላቀለ አቅርቧል።

በሌላው ክፍል ስር ደግሞ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝቱን አቅርቧል። በዚህ ክፍል ስር አራት ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት አላቸው ያላቸውን ጥናቶች ወስዶ ትኩረታቸውን፤ ጠንካራ እና ደካማ ጎናቸውን እንዲሁም ከእርሱ ጥናት ጋር ያላቸውን አንድነት እና ልዩነት እየዘረዘረ አቅርቧል። ከዚህ ሌላ የሙሾ ግጥም ስነ-ቃላዊ ባህሪያት በሚለው ክፍሉ ስር የስነ-ቃልን ባህርይ፤ ተከዋኝ መሆኑን እና ተለዋዋጭ መሆኑን እንደዚሁም ስለ አጋጣሚ /occasion/ እና ክዋኔ መግለጫ እና ማስተዋወቂያ ሠጥቷል። ከዚህም ሌላ ስለ ባህል አጠር ያለ መግለጫ ሠጥቶ አልፏል። ይህም እንደ ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ የተወሰደ እና በተዘዋዋሪም ቢሆን ቅንብቡን ለይቶ አውቆ እንደተጠቀመበት ያሳያል። በማጠቃለያው ላይ ደግሞ ሰዎች ማለትም የባህሉ ተከታዮች "ጎጅ ባህሎች" የሚባሉትን አውቆ እንዲተዋቸው እና እንዲለያቸው ይገልጻል። ከዚህ በፊት እንዳነሳነው ሁሉ "ጎጅ ባህል" ብሎ የመፈረጅ እና እንዲተዉ የማድረግ አላማ ከባህል አጥኚ የሚጠበቅ አይመስለኝም።

ሞገስ ሚካኤል በ2002 ዓ.ም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት "በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ስነ-ስርዓት፣ በስርዓቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፋከራና ክዋኔው" የሚል ርዕስ ያለው ነው። ይህ ጥናት ትኩረቱን ያደረገው በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ስነ-ስርዓት፣ በስነ-ስርዓቱ ላይ በሚከናወኑ ቀረርቶዎችና ፋከራዎች ላይ ነው። በዚህም ላይ የቅድመ ሞት ዝግጅት በማለት በዚህ ስር የሚመጡትን የነብዚ ስርዓት አፈፃፀምን እና ለዋናው ለቅሶና ለለቀስተኛው ማስተናገጃ የሚደረጉ ዝግጅቶችን እየዘረዘረና እየገለፀ አሳይቷል። ጊዜ ሞት በሚለው ክፍል ውስጥ ደግሞ በምሽት የሚካሄዱ ስነ-ስርዓቶች፣ በንጋት የሚካሄዱ ስነ-ስርዓቶች (እንደ ግንዘት) እና በአስከሬን ጉዞ ወቅት የሚከናወኑ ስነ-ስርዓቶች በማለት በእነዚህ ስር የሚመጡትን እና የሚታዩትን ስነ-ስርዓቶች በዝርዝር ገልጿል። በመጨረሻም ከቀብር በኋላ የሚከናወኑ ስነ-ስርዓቶችን አመልክቷል።

በጥናቱ ሂደት አጋጠመኝ ላላቸው ችግሮች መፍትሔዎችን ያስቀመጠ ሲሆን ለችግሩ ሰበብ ናቸው ያላቸው ምክንያቶች እንዲቀረፉም ይሁንታውን አስቀምጧል። የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ባደረገበት ክፍል ስር 15 የዲግሪ ማሟያ ፅሁፎችን እና 3 የሴሚናር ፅሁፎችን ተመልክቷል። እነዚህንም "የለቅሶ ሰርዓቶችን እና መሸኘን ያጠኑ"፣ "የለቅሶ ስርዓትን፣ ቀረርቶን እና ፋከራን ያጠኑ"፣ "የለቅሶ ስርዓትን ብቻ ያጠኑ"፣ እና "ቀረርቶን እና ፋከራን ብቻ ያጠኑ" በሚል ርዕስ ከፋፍሎ ቃኝቷቸዋል። በተለይም ከቲዮሪ፣ ከጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ እና ከትኩረት አንፃር ተመልክቷቸዋል። ከቀብር ስነ-ስርዓት፣ ከቀረርቶ፣ ከፋከራ እና ከክዋኔ ጋር የተያያዙ ንድፈ ሃሳባዊ ዳራዎችንም ቃኝቷል። በዚህም ስር ክዋኔ፣ የመከወኛ ምክንያት፣ ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ አውድ፣ ተጨባጭ አውድ፣ ማህበራዊ አውድ፣ ድርሰት፣ የክዋኔ ጠቋሚዎች እና የመከወኛ ቁሶች የሚባሉትን ፅንሰ ሃሳቦች ዘርዝሯል። በመጨረሻም በጊዜ ሂደት በክዋኔው ላይ የታዩትን ለውጦችን በማስታወስ ማጠቃለያ እና ይሁንታውን አስፍሯል።

በመቀጠል የምንመለከታቸው ፅሁፎች በ *"Ethnological society Bulletin"* ውስጥ የወጡ ናቸው። በትግራይ፣በአማራ ክልል በሸዋ ዞን እንደዚሁም በሀረር ክልል በተለያዩ አካባቢዎች የሚደረጉ የቀብር እና የለቅሶ ስነ-ስርዓቶች ምን እንደሚመስሉ የሚገልፁ ናቸው። በመጀመሪያ የምንመለከተው አብዱላ አብዱረህማን ያቀረበውን ፅሁፍ ነው። አብዱላ *"Harriri funeral custom"* በሚል ርዕስ ያቀረበው ፅሁፍ በሀረሪ ክልል በገላን እና አርባን አካባቢ

የሚደረገውን የቀብር እና የለቅሶ ስነ-ስርዓት በሁለት ክፍል መድቦ ያትታል። በዚህ ፅሁፉ ውስጥም አንድ ሰው ልክ መሞቱ እንደታወቀ ጀምሮ ያለውን ክዋኔ ይገልፃል። የመርዶ አነጋገሩ በየታ ላይ የተመረኮዘ ሲሆን ወንድ ከሞተ ሴት፣ሴት ከሞተች ደግሞ ወንድ መርዶ እየዞረ ያረዳል። በተጠቀሱት አካባቢዎች "አፎቻ" የሚባል እንደ ዕድር ያለ ማህበር መኖሩን ይገልፃል። የዚህ ማህበር አባል ያልሆነ ሰው ቀባሪ እንደሚያጣም ያትታል። ከዚህ በኋላ የለቅሶ እና የቀብር ስነ-ስርዓቱን የተመረጡ የአፎቻ ማህበር አባላት ያካሂዱታል።

በእነዚህ አካባቢዎች ሬሳ ጉድጓድ ውስጥ ሲገባ በቀኝ ጎኑ ተኝቶ ወደ ሰሜን አቅጣጫ እንዲዞር እንደሚደረግ ጠቁሟል። በሰሜን አቅጣጫ መዞሩም ወደ መካ ፊቱን ማዞሩን የሚጠቁም እንደሆነ አብዱላ በፅሁፉ ያትታል። የለቅሶና የቀብር ስነ-ስርዓቶቹም በየታ እና በማህበራዊ ደረጃ ላይ የተመሰረቱ እንደሆኑ ይጠቁማል። የስነ-ስርዓቱ ድምቀት እና ቆይታም እንደሟች የዕድሜ፣የማህበራዊ ደረጃ እና የማህበራዊ ህይወት ተሞክሮ የተለያየ እንደሆነ ይገልፃል። በአጠቃላይ አብደላ በዚህ ፅሁፉ ውስጥ አንድ ሟች ከሞተበት ጊዜ አንስቶ ያሉትን የተለያዩ ስነ-ስርዓቶችን ጠቁሟል። ይሁን እንጂ በእስልምና ዕምነት ተከታዮች ዘንድ ብቻ የሚካሄደውን ስነ-ስርዓት ነው የገለፀው። በሌላ በኩል ስነ-ስርዓቶቹን ከማስተዋወቅ እና ከመዘርዘር በዘለለ ጠለቅ ያለ ምልከታ አላካሄደባቸውም። ከዚህ በላይም በባህሉ ውስጥ ጉልህ ሚና ያላቸውን የየታ እና የማህበራዊ ሕይወት ደረጃን የተመለከቱ ስነ-ስርዓቶችን በቅጡ ሳይገልጽ እና ሳይተረጉም አልፏቸዋል። በባህሉ ውስጥ የየታ እና የማህበራዊ ሕይወት ደረጃ ያላቸው ቦታ እና አቀባበል፣ልዩነቱ ምንን መሠረት ያደረገ እንደሆነ ቢገልፅ መልካም ነበር። ይሁን እንጂ በተቻለ መጠን የአካባቢውን የቀብር እና የለቅሶ ስነ-ስርዓት ጠቅለል ባለ ሁኔታ ለማስተዋወቅ ሞክሯል።

ነጋ ተሠማ የተባለው ፀሃፊም *"The Death customs in the province of Tigre"* በሚል ርዕስ ፅሁፉን አቅርቧል። ነጋ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ በትግራይ አካባቢ የሚደረገውን የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ ከመጀመሪያው አንስቶ ገልጿል። ሟች ከተዳከመበት ጊዜ አንስቶ የሚደረገውን ስነ-ስርዓትም አሳይቷል። የአካባቢው የኑዛዜ አሠጣጥ እና አቀባበል፣መርዶ አረዳድ፣አገናነዝ እና የለቅሶ ቅድመ ዝግጅቶች ምን እንደሚመስሉ እየዘረዘረ ገልጿል። አንዳንዶቹ ላይም ጠለቅ ያለ ምልከታ እና ትንተና አካሂዶባቸዋል። የተራ ሰው እና የካህናት አገናነዝ፣ የመነኮሳት፣የባህታውያን እና የዲያቆናት የአገናነዝ እና የአቀባበር ሁኔታ ምን

እንደሚመስል እና ለምን እንደሆነ አጠር ያለ መግለጫ ሰጥቷል። ከሠባት አመት በታች ለሆነ እና ራሱን ላጠፋ ሰው ሞት እንደሌላው ሰው መደበኛ ክዋኔ እንደማይደረግለት ጠቁሟል። በባህሉ ውስጥ ራስን ማጥፋት ምን ማለት እንደሆነ እና ለምን ክዋኔቢስ እንደሆነ እንደዚሁም ሰባት ዓመት ለምን እንደተመረጠ እና ትርጉሙ ምን እንደሆነ በጥናቱ ውስጥ የገለፀው ነገር የለም። በቀብር ስነ-ስርዓት ጊዜ ወንዶች ንቁ ተሳትፎ እና እንቅስቃሴ እንዳላቸው ይገልፃል። ፀሀፊው የፆታ እና የስርዓተ-ፆታን ጉዳይ አንስቶ ከባህሉ አንፃር አንዳች ነገር ቢል የተሻለ ይሆን ነበር። ሬሳው ወደ ቀብር ቦታ መንገድ ሲጀምርም ሰዎች ለሟቹ እንዳላቸው ቅርበት፣ማህበራዊ ደረጃቸው እና ማህበራዊ ተሳትፏቸው በሰልፍ አጀበው ይሸኙታል። በመንገድ ላይም ሰባት ጊዜ እንደሚያርፍ ተገልጿል። ሰባት የሚለው ነጥብ ከእዚህ ጋር ለሁለተኛ ጊዜ ተገልጿል። ስለዚህ ቁጥሩ በባህሉ ዘንድ የተለየ ትርጉም እና ፋይዳ አለው ማለት ነው። አጥኚው ይህንን ጉዳይ በትኩረት መመልከት ነበረበት። ሰባት ለምን እንደተመረጠ እና በባህሉ አልያም በሃይማኖቱ ዘንድ ስላለው ትርጉም የተባለ ነገር የለም። ከቀብሩ በኋላም የተከስ፣የደወል እና የለቅሶ ድምፅ እንደሚሰማ ጠቁሟል።

በጥናቱ ውስጥ ከዋናው ለቅሶ ጋር በተያያዘ ስለ ሁለተኛ ለቅሶ ምንነት ተገልጿል። በዚህ ጊዜም የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎች በማጀቢያነት አገልግሎት እንደሚሰጡ ተጠቁሟል። እስከ 40 ቀን፣6 ወር እና አንድ ዓመት ድረስ ሃዘንተኞች ሃዘናቸውን መግለጫ የተለያዩ ድርጊቶችን እንደሚያካሂዱ ገልጿል። ነጋ ስነ-ስርዓቱን እና ክዋኔውን በተቻለ መጠን ለማሳየት እና ለመተንተን ሞክሯል። አንዳንድ ነጥቦች ላይ ጠለቅ ያለ ምልከታ ያካሄደ ሲሆን አንዳንዶቹን ግን በመጥቀስ እና በመዘርዘር ብቻ አልፏቸዋል። ከእነዚህ መሃከል የቀሳውስት፣የመነኮሳት እና የካህናት አገናኝ እና አቀባበር የተለያየ መሆኑን የገለፀ ቢሆንም ምክንያቱን እና ትርጉሙን በተገቢ ሁኔታ አላስቀመጠም። ይህም ለምን? እና እንዴት? የሚሉትን ጥያቄዎች ያስነሳበታል። እነዚህ ክዋኔዎች የሟችን እና የቀሪን የሕይወት እና የከሕይወት በኋላ እምነት እና ትርጉም የመግለፅ አቅማቸው ከፍተኛ የሆነ እና የስራ እና የኃላፊነት ደረጃቸውንም የመጠቆም ሀይል ያለው ይመስለኛል።

የሸዋ አማራን የሃዘን ስነ-ስርዓትን በተመለከተ ፅሁፉን ያቀረበው ደግሞ ፋሲካ በለጠ ነው። ፋሲካ *"The Death customs Among the Amharas of Šäwa"* በሚል ያቀረበው ይህ ፅሁፍ በአጠቃላይ በአምስት ዓበይት ክፍሎች ተመድቧል። የመጀመሪያው *"The making of the*

last will" የሚል ርዕስ አለው። በዚህ ክፍል ውስጥ ኑዛዜ መቼ እንደሚደረግ፣እነማን ባሉበት ለማን እንደሚደረግ ይገልፃል። ኑዛዜ በተመረጠው አካባቢ ባህል ውስጥ ያለውን አመለካከት እና ተቀባይነት ይዘረዝራል። ከዚህም በተጨማሪ ኑዛዜ በሚተላለፍበት ወቅት የተቀባዮቹ ሁኔታ እና ስነ-ስርዓቱ ምን እንደሚመስል ገልጿል። ቀጣዩ "Breaking the News" የሚለው ክፍል ነው። በዚህኛው ክፍል ውስጥ ፀሃፊው የሟች ሕይወት ማለፍ ለቅርብ ሰዎች እና ለቤተሰቦች፣ለወዳጆች፣ለጎረቤቶች እና ለአካባቢው ሰዎች እንዴት ባለሁኔታ እንደሚነገር እና እንደሚጠሩ ያትታል። *"The Service for the Dead"* በሚለው ቀጣይ ክፍል ውስጥ ደግሞ የግንዘት እና የአከፋፈን ስነ-ስርዓቱ በእነማን፣መቼ፣እንዴት እና ለምን እንደሚደረግ እየዘረዘረ ገልጿል፣፣ ገናገሮች በምን መስፈርት እንደሚመረጡ እና ለተለያዩ ሰዎች የሚደረገው የተለያየ ዓይነት ግንዘት ምን እንደሚመስል አሳይቷል።

"The Funeral Procession" እና *"At the Grave"* በሚሉት ቀጣይ ሁለት ክፍሎች ውስጥ ደግሞ የቀብር ስነ-ስርዓቱ ከመጀመሪያው አንስቶ እስከ ግብዓተ መሬቱ ፍፃሜ ድረስ ምን እንደሚመስል በዝርዝር አሳይቷል። እነማን ስነ-ስርዓቱን እንደሚያካሂዱ፣ጉድጓዱ እንዴት እንደሚቆፈር እና በየክዋኔው መሃል የሚደረጉ የተለያዩ ስነ-ስርዓቶች ምን እንደሚመስሉ ገልጿል። በመጨረሻው እና *"The Mourning Customs"* በተሠኘው ክፍል ውስጥ ደግሞ ያሉትን ክዋኔዎች እንደገና በሶስት ንዑሳን ክፍሎች ዘርዝሮ ያቀርባቸዋል። በአካባቢው ባካሄደው ቅኝት እና በሰበሰበው መረጃ መሠረት ክዋኔዎቹን ማልቀስ፣ዲኮሬሽን እና አልባሳት ብሎ መድቧቸዋል። ማልቀስ በግል እና በቡድን እንደሚደረግ እና አስለቃሽም እንዳለ አያይዞ ገልጿል። ዲኮሬሽን ደግሞ ፀጉርን መላጨት፣ፂምን አለመቆረጥ፣ፀጉር መንጨት፣ፊት መቧጠጥን እንደሚያጠቃልል ያስነብባል። የአለባበስ ሁኔታ እና የቀለም ምርጫ ደግሞ አልባሳት በሚለው ውስጥ ተመድበዋል። በለቅሶ ስነ-ስርዓቱ ውስጥ እነዚህ ሶስት ጉዳዮች ጎልተው እንደሚታዩም አስምሮበታል። ፋሲካ በአጠቃላይ ምልከታውን በኃይማኖት እና በአካባቢው ለይቶ ያካሄደ ሲሆን መረጃዎችንም ከትላልቅ ሰዎች እየጠየቀ እና እየፈለገ እንዳጠናቀረው ገልጿል።

የመጨረሻው አንዳርጋቸው ተስፋዬ ያቀረበው *"The Funeral Customs of the Kottu of Harar"* የተሰኘው ፅሁፍ ነው። አንዳርጋቸው በፅሁፉ አንድ ሰው እንደሞተ ወዲያው የሚካሄደው ክዋኔ ግንዘት እንደሆነ እና ግንዘቱም ምን እንደሚመስል ይገልፃል። ሬሳው

ሲገነዝ በስተቀኝ በኩል እንዲተኛ ተደርጎ ሁለቱ እጆቹ ከራስጌው ስር ሆነው እግሩ ከጉልበቱ እንደሚታጠፍ ይገልፃል። ይህ የሆነበት ምክንያት ከባህል፣ከእምነት፣ከፆታ እና ከማህበራዊ ደረጃ አንፃር ምን እንደሆነ ግን አልገለፀም። በመቀጠል የማርዳት፣ምግብ እና መጠጥ የማዘጋጀት እና የጉዞ ቀብር ዝግጅት ይደረጋል። ሬሳውን የሚያጥበው በፆታ እና በእድሜ ረገድ የተወሰነ እና የተመረጠ ነው። እዚህ ጋርም ቢሆን የፆታን ጉዳይ አጥብቆ በመያዝ ከሀይማኖቱና ከባህሉ አንፃር አንዳች ነገር ማለት ነበረበት። የፆታ አንድነት እና ልዩነት በባህሉና በእምነቱ ዘንድ ያለው ትርጉም ምን እንደሆነ አልተገለፀም። ይህም አንዳች የትርጉም ጉድለት ማስከተሉ አይቀሬ ነው። የእርድ ስነ-ስርዓት ከተደረገ በኋላ ወንዶች ብቻ ሊቀብሩ ይሄዳሉ ሴቶች ደግሞ እንዳይፈሩ እና መካን እንዳይሆኑ በሚል እሳቤ እንደማይቀብሩ እና ቤት እንደሚቀመጡ ይገልፃል። መካን መሆን ከመቅበር ጋር ያለውን ግንኙነት እና የማህበረሰቡን አመለካከት ከባህሉ እና ከእምነቱ ረገድ ቢጠቁም እና ቢገልጽ መልካም ነበር።

ከቀብሩ በኋላም ወንዶች የተዘጋጀውን ምግብ እና መጠጥ ከቀመሱ በኋላ ማስተዛዘን እና ኃይማኖታዊ ፀሎቶችን ማድረግ ይጀምራሉ። አመሻሽ ላይ ሁሉም ወደየቤቱ ሲሄድ ወንዶች ብቻ በሚች ቤት እንዲያድሩ ይሆናል። ይህ የፆታ ልዮነት በምን ምክንያት እንደሚመጣም አያይዞ ቢገልጽ መልካም ይሆን ነበር። በዚህ ሁኔታ ሃዘን እስኪበርድ ድረስ ለተቸገሩ ሰዎች ምግብ እየተሰጠ እና ለሚች እየተፀየለ ይቆያል። አንዳርጋቸው በዚህ ፅሁፉ በተለይ የፆታን ጉዳይ በሰፊው ሁኔታ መግለፅ እና መተርጎም ነበረበት። በፅሁፉ ውስጥ እንደተመለከትነው የፆታ እና የስርዓተ-ፆታ *(sex and gender)* ጉዳይ በብዙ መልኩ የሚነሳ እና ሙያ እና ሀላፊነትንም የሚወስን በመሆኑ በዝርዝር ሰፋ ተደርጎ መቃኘት ነበረበት።

ቀጣዩ ፅሁፍ በቤታና ሆጤሶ አማካይነት የተዘጋጀ እና ስለ ሲዳማ ብሔሰብ ባህል የሚያትት ነው። በፅሁፉ ውስጥ ፀሃፊው ስለ ብሔረሰቡ የሐዘን ሁኔታ የገለፀበት ክፍል ይገኛል። በዚህ ክፍል ውስጥም የብሔረሰቡ የተለያዩ ዓባላት ሲሞቱ የሚደረግላቸውን የሀዘን ስነ-ስርዓት ያሳያል። በሲዳማ ብሔረሰብ ዘንድ የለቅሶ ስነ-ስርዓት እንደሚች የፅድሜ፣የማህበራዊ ደረጃ እና የፆታ ልዩነት የተለያየ ነው። በባህሉ መሠረት በጣም ህፃን ልጅ ሲሞት ለቅሶ አይደረግም። አባቱና የአባቱ ወንድሞች ብቻ ተሰብስበው ይቀብሩታል። ይህ ለቅሶ የማይካሄድበት እና አባቱና የአባቱ ወንድሞች ብቻ የሚቀብሩበት ምክንያት፣ ትንታኔ እና ትርጉሙ ምን እንደሆነ አልተገለፀም። በእድሜ ትንሽ ከፍ ያለ ልጅ የሞተ እንደሆነ ለሶስት

ቀን ብቻ ለቅሶ ይደረግና የአካባቢው ሽማግሌዎች ለእናት እና ለአባቱ ሀዘናቸውን ያበርዱ ዘንድ ቅቤ በቅጠል ይሠጣሉ። እነርሱም ግንባራቸውን እና ሆዳቸውን ከተቀቡ በኋላ አልጋቸው መሃል ላይ ያደርጉታል። ይህ አልጋ መሃል ላይ መደረጉ ትልቅ ትርጉም ያለው ይመስላል። በፀሃፊው በኩል ግን በዚህ ዙሪያ የተባለ ነገር የለም። በባህሉ ዘንድ ቅቤ፣ቅጠል፣ግንባር፣ሆድ እና አልጋ አንዳች የሆነ ትርጉም እና ፋይዳ ይኖራቸዋል።

በጉድጓድ አቆፋፈር ረገድ የያታ ልዩነት ጉልህ ሚና ይጫወታል። አባት የሞተ እንደሆነ በመጀመሪያ ልጁ መሬት ወጊነት ሁለት ጉዳንዶች በቅርብ ርቀት ይቆፈሩና ውስጥ ለውስጥ እንዲገናኙ ይደረጋል። ሚች ሴት ከሆነች ግን አንድ ጉድጓድ ተቆፍሮ ከታች ወደ ጎን እንዲቦረቦር ይደረጋል። ፀሃፊው እዚህ ጋር የሁለቱን ያታዎች ልዩነት ማንሳት እና በባህሉ ዓይን ሁለቱ ያላቸውን ቦታ ማመልከት ነበረበት። ቆፋሪዎቹ ካልደከማቸው እና ካልሠለቻቸው ለሴቷ እንደገና ሁለተኛ ጉድጓድ እንደሚቆፍሩ ይጠቁማል። ይህንን ጉዳይ ፀሐፊው እንደዋላ ባያልፈው መልካም ነበር። ባህልን የሚያህል ነገር እየተጠና እና እየተፃፈ "ካልሠለቻቸው" ብሎ ትልቅ ነጥብ ማለፍ ተገቢ አልመሰለኝም። ከቀብሩ በኋላም መቃብሩ የወንድ ይሁን የሴት ለመለየት የሚደረገው ነገርም የሁለቱን በባህሉ ውስጥ ያላቸውን ቦታ የሚያመለክት ነው። የወንዱ መቃብር በጠንካራና ባጌጠ ቀርከሀ ይከለላል። የሴቷ ደግሞ እንደነገሩ ይከለላል። በዚህ ላይ የተነሳው ሌላው ነጥብ የዳግማዊ ለቅሶ ጉዳይ ነው። ዳግማዊ ለቅሶ በክብ ቆጣሪዎች አማካይነት ቀኑ ተቆርጦ ይነገራል። በተመረጠውም ቀን ክዋኔው ይደረጋል።

በለቅሶ ስነ-ስርዓት ረገድ ሌላው ለየት ያለ ክዋኔ የሚደረግለት ገዳይ (ጀግና) ሲሞት ነው። ጀግና ሲሞት መቃብሩ ላይ የሚደረገው እንጨት ቀይ ቀለም ይቀባል። ሚች ያገባ እና የወለደ ከሆነ የዝግባ ወይም የጥድ እንጨት ተመርጦ ቅርፊቱ ተልጦ መቃብሩ ዙሪያው ይከበባል። ያላገባ ከሆነ ግን ቅርፊቱ አይላጥም። በሃዘን ወቅት ወንድ ከሞተ ሴቷ የሚችን ሱሪ እና ገዳይ ከሆነ ደግሞ የገደላቸውን አውሬዎች ቆዳ ዘቅዝቃ ትሰብሳለች። ሴት ከሞተች ደግሞ ወንድ እንደዚሁ የሴቷን ልብስ ዘቅዝቆ ይሰብሳል። እነዚህ ነጥቦችም በባህሉ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ያላቸውና ወሣኝ የሆኑ ጉዳዮች ናቸው። ይሁን እንጂ ፀሀፊው እየዘረዘረ ከማስተዋወቅ በዘለለ ጥልቀት ያለው ምልከታ እና ትንተና አላካሄደም። የአንዳንዶቹን ትርጉምም ሳይገልፅ አልፏል። ዝግባና ጥድ፣ቀይ ቀለም፣ቅርፊት፣ልብስ መዘቅዘቅ

ስለብሔረሰቡ አባላት እና ስለ ባህሉ አንዳች ትርጉም መስጠቱ አይቀሬ ነው። በዚህም ምክንያት በጥልቀት ቢመለከታቸው እና ቢተረጉማቸው መልካም ነበር።

እነዚህ ከላይ የተመለከትኳቸው የጥናት ዕሁፎች በብዙ መልኩ ከእኔ ጥናት ጋር የሚገናኙበት እና የሚለያዩበት ነጥብ አለ። አንደኛው እና የመጀመሪያው ጉዳይ ሁላችንም የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔን ማንሳታችንና መመልከታችን አንድ ያደርገናል። የምንለያይባቸው ነጥቦች በአንዳንዱ በርከት ብለው ይገኛሉ። የመጀመሪያው የጥናት አካባቢ ልዩነት ነው። ለጥናት የተመረጡት ብሔረሰቦች እና አካባቢዎች የተለያዩ ናቸው። ሁለተኛው እኔ የተመለከትኩትን የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔን ከክዋኔ አበይት ዓይነቶች፣ ባህሪያት እና አገልግሎቶች አንፃር እየተነተንኩ አቀርባለሁ። ከዚህ በተጨማሪ ከእያንዳንዱ ክዋኔ እና የክዋኔ ዓላባውያን አንፃር ያገኘኋቸውን እና የተመለከትኳቸውን ነጥቦች እተነትናለሁ። እተረጉማለሁ። ከእያንዳንዱ ክዋኔ ጋር ተያይዘው የሚመጡትን ቁሳቁሶችንም ፋይዳና ትርጉም አሣያለሁ።

2.2 የንድፈ ሃሳብ ቅኝት

2.2.1 ሞት፣ ለቅሶ፣ ክብረ-በዓል እና ክዋኔ

ለቅሶን ከሚያመጡት ሠበበ ምክንያቶች አንዱ እና ዋነኛው ሞት ነው። የሞት መምጫ መንገዱ ይለያይ እንጂ የፍጥረት ሁሉ የጋራ ባህሪይ ነው። አብይ ልዩነቱ ከሁነቱ በፊት እና በተለይ ደግሞ በኋላ ያለው ጉዳይ ነው። ሞት እንደየባህሉ የተለያየ መጠሪያ እና ፍቺ ይሠጠዋል። በክርስትና ሃይማኖት ረገድም የተለያየ ስያሜ እና ትርጉም አለው። በዚህ ሃይማኖት ረገድ ሁለት ዓበይት ሞቶች አሉ። እነዚሁም የአካል (የሥጋ) ሞት እና የነፍስ ሞት ናቸው። *"ሞት የነፍስ እና የስጋ መለየት ወይም ሕይወት ማጣት። ይህም በስጋዊም በመንፈሳዊም ሊሆን ይችላል"* (የኢትዮጵያ መፅሀፍ ቅዱስ ማህበር፣ 1972፣ 50) ይህም በመፅሀፍ ቅዱስ ሁለት ዓይነት ሞት መኖሩን ያሳያል። አንደኛው የስጋ ሞት ነው። የስጋ ሞት በአብዛኛው ሰው ዘንድ የሚታወቀው እና በተራዛሚውም ከሳይንሳዊው የሞት ብያኔ ጋር አንድነት ያለው ነው። ሁለተኛው እና መንፈሳዊው ሞት ግን ከርዕዮተ ዓለም ጋር ዝምድናው የጠበቀ ነው። መንፈሳዊ ሞት ዘርፈ ብዙ ነው። ትርጉሙም በርካታ ነው። በአንዳንድ ባህል ውስጥ እንደሚታወቀው አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር (ብዙውን ጊዜ ከአቻው ጋር) በማህበራዊ

እና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ረገድ ያነሠ ወይም የወረደ ሲሆን፤ ራሱን በብዙ መልኩ ከእቻው ጋር ማወዳደር እና ማነፃፀር ሲሳነው ራሱን እንደሞተ አድርጎ ይቆጥራል፤ የቁም ሞት። በሌላ በኩል በመንፈሳዊ ህይወቱ ረገድ ህግጋትን የተላለፈ፤ የጣሠ እና ያልተገዛ ሰው በህይወቱ ደስተኛነት ይርቀዋል፤ መንፈሳዊ ማንነቱም እንደሞተ አድርጎ ይቆጥራል። ስለራሱ የቁም ሞትም አብዝቶ ሊያለቅስ እና ሊፀፀት ይችላል። *"...በአዳም አለመታዘዝ ምክንያት ሞት ወደ ዓለም ገባ። ሞት የኃጢአት ውጤት ነውና።... አዳም ትሞታለህ በተባለው መሠረት ወዲያው በስጋ አልሞተም። ነገር ግን ከእግዚአብሔር በመንፈስ ተለየ።... እንደዚሁም ሠምኞ በኃጢአት ሲኖሩ መታን ይባላሉ።"* እንዲል መፅሀፉ። (የኢትዮጵያ መፅሀፍ ቅዱስ ማህበር፤50)

ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ዓይነት ሞቶች አንድ ላይ የሚመጡበት ሁኔታ እንዳለም ይኸው መፅሀፍ ይገልፃል። *"ኃጢአተኞች በፍርድ ዕለት ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር ፊት በእሳት ባህር ይጣላሉ። ይህም ሁለተኛ ሞት ይባላል። ስቃያቸው አያልቅም... ክርስቶስን አምነው የሞቱ ለዘለዓለም ከእርሱ ጋር ይኖራሉ።... ምዕመናን በክርስቶስ ዕረፍትን ስለሚያገኙ ሞታቸው ዕረፍት ይባላል።"* (የኢትዮጵያ መፅሀፍ ቅዱስ ማህበር፤50) በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ሞት "ማንቀላፋት" በሚለው እየተተካ እንደሚቀርብም ይኸው መፅሀፍ ይጠቁማል። ይኸው ማንቀላፋት የተሠኘው ቃል የሞት ዓይነቶችን ወደ ሶስት ደረጃ ያሳድጋቸዋል። እነዚሁም አረፍት፤ሞት እና ሁለተኛ ሞት። ይኸውም እንደየማህበረሰቡ፤ እንደየባህሉ፤ እንደየተቋመ እና እንደየ ርዕዮተ ዓለመ ደንብ እና ትዕዛዛ የሚወሰን እና የሚሰየም ነው።

ሞት ከሚያስከትላቸው ጠንካራ ስሜቶች መሃከል ዋነኛው ሃዘን ነው። ብዙውን ጊዜ የሃዘን መግለጫ ተደርጎ የሚወሰደው ደግሞ ለቅሶ ነው። *"We all believe we know that death is because it is a familiar event and one that arouses in tense emotion" (Hertz፡ 1960,27)* በማለት ሞት አብሮን የኖረ እና የተላመድነው ቢሆንም ሁሌም ከፍተኛ የሆነ የሃዘን ስሜትን እንደሚያጭር ይገልፃል። ለቅሶም ልክ እንደሞቱ ሁሉ በዓይነትም በፍቺ ልዩ ልዩ ነው። በመጀመሪያ የቃሉን ትርጉም ስንመለከት ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በመዝገበ ቃላታቸው ውስጥ *"በከይ፤ ዮት፤ (በከየ፡ ይበኪ፡ ይብኪ። ዕብ፡ በካ። ሶር፡ ብካ። ዐረ፡በከ)፤ ማልቀስ፤ እንብ ማፍሰስ፤ ዋይ ማለት፡ መጮህ፤ መንሰቅሰቅ"* (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ 1948፤269) በሚል

ይተረጉመዋል። ይህም ብያኔ በብዛት ከላይ የጠቀስናቸው ጉዳዮች (ሞት፣ መከዳት፣ መጠቃት፣ ማነስ...) ሲከሰቱ የሚያስከትለውን የስሜት ለውጥ የሚያመለክት ነው። ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አያይዘውም ማልቀስን ከማዘን፣ ከመጨነቅ እና አንባ ከማፍሰስ ጋር አያይዘው ይገልፀዋል። ፀሐፊው ማልቀስን እና ለቅሶን ከስሜት መለወጥ ጋር ተያይዞ የሚመጣ እንደሆነ ያሳያሉ። በሃገራችን እና በአንዳንድ የአለም ክፍሎች ባህል ውስጥ እንደምንመለከተው ሞት ብዙውን ጊዜ ሀዘንን ያስከትላል። ሀዘንም እንደዚሁ ለቅሶን ያመጣል። የለቅሶ ስነ-ስርዓትም ከማንኛውም ለቅሶ (አንባ መውረድ) የሚለው በክዋኔና በልዩ ልዩ ስነ ስርዓቶች መታጀቡ ነው።

ደስታ ተክለ ወልድም በመዝገበ ቃላታቸው ውስጥ ለቅሶን በይነው አስፍረዋል። ብያኔያቸው ከኪዳነ ወልድ ክፍሌ ብያኔ ብዙም የራቀ ባይሆንም አንዳንድ የተለዩ ቃላትን ገልፀው ፍቺውን ያሰፉታል። በተለይም ትካዜ፣ ቁዘማ፣ መሪኮን እና የእንባን መመንጨት፣ መፍሰስ እና መውረድ ያሉትን ቃላት ያካትታሉ። (ደስታ ተክለ ወልድ፣ 1962፣739) ይህ ብያኔ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ክዋኔንና ስነ-ስርዓቱን ያካተተ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ይኸውም በተለይ ቁዘማና መሪኮ ከሌሎቹ አንባር ትርጉማቸው ሰፋ ያለና ስነ ስርዓት አከልም ናቸው። መሪኮው በውስጡ ስነ ቃልን እና ክዋኔን ያካተተ ነው። ቁዘማም እንደዚሁም ሃዘን የሚያስከትለው ድርጊት ነው።

ለቅሶ ምን አልባትም ከሰው ልጅ መፈጠር ጋር አብሮ የተፈጠረና ስነ-ስርዓቱም ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ ነው። ሂደቱና አይነቱም እንደየ ባህሉና እንደየዘመኑ የተለያየ ነው። የሃይማኖት መፅሃፉም በዚህ ዙሪያ የራሱን ብያኔ ያስቀምጣል። ይኸውም ከጥንት ዘመን ጀምሮ (ከክርስቶስ ልደት በፊት) አይሁድ ለቅሶ ያደርግ እንደነበር ይጠቁማል። በስልጣን ረገድም ከፍ ላሉ እና ለታላላቅ ሰዎች ረጅም ቀናት የሚፈጅ ክዋኔ ያለው እና ከፍ ያለ ስርዓት ይፈፀምላቸው እንደነበር ያስታውሳል። ስርዓቱም በተለይ እንደ ዘመኑ፣ እንደ ሃገሩ፣ እንደ ሚች ማንነትና እንደ ቤተሰቡ ሁኔታ ይለያይ ነበር። በለቅሶ ስነ-ስርዓት ወቅትም የተለያዩ ክዋኔዎች እና ድርጊቶች ይፈፀሙ ነበር። ከእነዚህም መሃከል ያም መያም፣ ልብስን መቅደድ፣ በራስ ላይ ትቢያ መነስነስ፣ ማቅን ማልበስ፣ ራስን መንጨት የተለመደ እንደነበር ፅሁፉ ይጠቁማል። (የኢትዮጵያ መፅሐፍ ቅዱስ ማህበር፣ 7) የማህበራዊና ባህላዊ አንትሮፖሎጂ ኢንሳይክሎፒዲያ ፅሁፍም በሌላ በኩልም ይህንኑን ከፍ ያሉ ሰዎች እና

ታላላቅ ሰዎች የቀብር ሁኔታቸው እና ሃዘናቸው ረዘም ያለ ጊዜ እንደሚፈጅና ክዋኔውም ዘርፈ ብዙ እንደሆነ ይጠቁማል። (*Barnard and Spencer; 2005, 435)*

በሃዘን ጊዜ ሃዘንተኛ የሚያመጣው አዲስ ባህሪይ ይኖራል። ንቁው ይፈላል፤ ሳቂታው ያዝናል፤ ያለቅሳል፤ ሽቅርቅሩ ትቢያን ይነሰንሳል ማቅንም ይለብሳል። እነዚህ አዳዲስ ማንነቶችና ምልክቶችም የሃዘንተኛን ስሜት የመግለፅ አቅም ይኖራቸዋል። በነዚህ ድርጊቶች አማካይነትም ሰው ስነ ልቡናዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ግዴታውን ሊወጣ ይቻለዋል። ለቅሶ በተለያዩ ባህሎች ውስጥ እራስን በመላጨት፤ የተወሰኑ እና ሃዘንን ይገልፃሉ የሚባሉ አልባሳትን በመልበስ እና በነዚህ ሁኔታዎች ለተወሰኑ ቀናት በመቆየት ሊገለፅ ይችላል። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ሔርትዝ በዕሉፉ

> *"Death, infact, by striking the individual, has given him a new character; his body, which (except in certain abnormal ceases) was in the realm of the ordinary, suddenly leaves it; it can no longer be touched with out danger, it is an object of horror and dread. (Hertz; 1960, 37)*

በማለት ይገልፀዋል። ከዚህ በኋላም የሚመጣው የቀብር እና የአቀባበር ትርጉም እና ፍቺም እንደዚሁ እንደየባህሉ፣ እንደየሀገሩ፣ እንደየዘመኑ እና እንደቤተሰቡ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊ እና መንፈሳዊ ደረጃ የተለያየ ይሆናል።

በእኛ ሃገር ብዙ ባህሎች ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለከት በርካታ የህይወት ዑደት አበይት ክፍሎች *(Rites of passages)* ዋነኛ ማብሰሪያ ብልሃታቸው ክዋኔና ከበራ ናቸው። ለዚህ በብዙ መልኩ አስረጂ የሚሆኑን የውልደት፣ የክርስትና፣ የግርዛት፣ የጋብቻ፣ የምርቃት (በትምህርት ዘርፍ) እና የሃዘን ስነ- ስርዓቶች ናቸው። እነዚህ በሳይንሳዊ መንገድ መረጋገጥ የሚችሉ ቢሆኑም በብዙ መልኩ ማብሰሪያ መንገዳቸው ባህላዊ ክዋኔዎች እና ከበራዎች ናቸው። እነዚህ ሁለት ዓበይት ጉዳዮች የሰርክ ባህሪያቸው ሆነው ይገኛሉ። ውልደት በዕልልታ፤ ክርስትና በጥምቀት፤ ጋብቻ በቃለ መሃላ ሀዘንም በለቅሶ አማካይነት ይገለፃሉ። እነዚህ መግለጫ ብልሃቶችም የባህል ዓቢይ ዘርፍ ሆነው ይገኛሉ። የዕሁፉ ርዕሰ ነገር የሆነው የለቅሶ ከበራም እንደዚሁ።

የለቅሶ ከበራ *(Ritual)* እና ክዋኔው (*Performance)* መልክ ብዙ ነው። ለእነዚህም እንደመለያነት የሚጠቀሱት የሟች ፣የሟች ቤተሰብ፣ የሟች ዘር ማንዘር እና የሟች አካባቢ

ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና መንፈሳዊ ማንነቶች እና ደረጃዎች ናቸው፡ ከበራ ብዙ ጉዛንጉቾን በውስጡ አካቶ የሚይዝ እና ስፋት ያለው የህገረሰባዊ ልማድ አንዱ ክፍል ነው። የተለያዩ ብያኔዎችም በተለያዩ ጊዜያት ሲሰጡት ይታያል። ይህም የዘርፉን መልክ ብዙነት እና ሠፊነት የሚያሳይ ነው። የአሜሪካን ፎክሎር ኢንሳይክሎፒዲያ *"...Rituals can be practices and events associated with special occasions in the lives of a community or its members."* (Watts 2007፡ 336) በማለት ይበይነዋል። ከበራ ከክዋኔ እና ሁነት ጋር የተገናኘ እና ከማህበረሠቡ አንዳች የህይወት አጋጣሚ ጋር የተያያዘ ነው። እነዚህ የህይወት አጋጣሚዎችም መልክ ብዙ እና ከባህል ጋር ያላቸው ቁርኝትም የጠበቀ ነው። ከበራ በውስጡ በርካታ ጉዳዮችን ይይዛል። ይህንን ጉዳይ ዋትስ እና ማርታ እና ማርቲን በዝርዝር በመፅሃፋቸው ላይ ያሳዩናል። *"... A folk ritual includes not only rites of passage, but also other events of consequences for both individuals and collectives. Religious land marks account for any folk rituals, from christening to funeral services." (Watts; 2007, 336)* በማለት በጎይማኖት ረገድ ስንሄድ ከክርስትና በዓል ጀምሮ እስከ የአቀባበር ስርዓት ድረስ የሚይዝ መሆኑን ይገልፃል። ማርታ እና ማርቲንም

> *"...Most rituals bring together many types of folklore; verbal such as chants, recitations, Poems or songs; customary, such as gesture, dance or movements; and material such as food, books, awards, clothing and costumes."(Martha & Martine; 2005, 95)*

በማለት ፎክሎርን በከፈሉበት በአበይት ሦስት ዘርፎች ውስጥ ያሉ ምንምን ጉዳዮች በከበራ ውስጥ እንደሚካተቱ እና እንደሚገኙ ይገልፃሉ።

ከበራና ክዋኔ በአንዳች የባህል ክፍል ውስጥ ያላቸው ስፍራ ሰፊ ነው። ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ማናቸውም ባህላዊ፣ ማህበራዊም ሆነ ሃይማኖታዊ ሁነቶች ከእነዚህ የሚወጡ አይሆኑም። በለቅሶ ውስጥ ያለውን ሁኔታ አያይዘን ስንመለከትም በውስጡ ብዙ ስነ-ስርዓቶች እና ክዋኔዎች አሉት። ከእነዚህም መሃከል እንጉርጉሮ፣ ሙሾ፣ መውደቅ መነሳት፣ ደረት መጣል እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። ተያይዘው ከሚመጡት ቁሳቁሶች መሃከልም የአልባሳቱ አይነት እና ሁኔታ በለቅሶው ወቅት የሚቀርበው ምግብና መጠጥ አይነተኛ ምሳሌዎች ናቸው። እነዚህ ዝርዝር ጉዳዮች በጥቅሉ የክዋኔና የከበራ ዘርፎች ሆነው ይገኛሉ።

ከበራ በርካታ ባህሪያት እና መገለጫዎች አሉት። ከእነዚህም መሀከል ተጠቃሾቹ ተደጋጋሚናቱና ተከዋኝነቱ ናቸው። ካለነዚህ ሁለት ጉዳዮች ከበራ ራሱን ችሎ መቆምም ሆነ ህልውናውን ማስቀጠል አይቻለውም። መደጋገሙ አንድም ከትውልድ ወደ ትውልድ፤ ከማህበረሰብ ማህበረሰብ እንዲቀጥል ያስችለዋል። ዋትስ *"... A folk ritual can involve any event in which a tradition preserved through repetition, whether annually or on another basis."* (336) በማለት ዓመታዊ በሆነ ክብረ በዓል አልያም በሌሎች ጉዳዮች ሳቢያ የከበራው ክዋኔ እየተደጋገመ እና እየተከወነ እንደሚቀጥል ያስረግጣል። በሌላ በኩል የድግግሞሹ ጉዳይ አይነተኛ ነጥብ መሆኑን ግሪን *"Ritual is a repetitive action and can be participated in by generation after generation because it follows a restricted model."* (1997: 735) በማለት ይገልፃል። ማርታ እና ማርቲንም *"A ritual is a particular type of tradition... Rituals are repeated, habitual actions, but they are more purposeful than customs"* (95) በማለት ከበራ የሀገረሰባዊ ልማድ ዓይነት መሆኑን ይጠቁማሉ። ከዚህም በተጨማሪ ተጨባጭ ያልሆኑ የባህል እሴቶችን *(Intangible values)* የያዘ እና እነዚህንም እሴቶች በግልፅ አጉልቶ የሚያሳይ የፎክሎር አብይ ዘርፍ መሆኑን ያሰምሩበታል።

ሁለት የከበራ ዓይነቶች አሉ። የዝቅተኛ ዓውድ *(Low-context)* እና የከፍተኛ ዓውድ *(High context)* ከበራዎች ይባላሉ። *(Finnegan; 1992:102)* የዝቅተኛ ዓውድ ከበራ ብዙም ትኩረት የማይደረግበት በይዘቱም ሆነ በሂደቱ ብዙ ጊዜን የማይጠይቅ እና በታዳሚም ሆነ በከዋኝ (አቅራቢ) ዘንድ ብዙም ዝግጅት የማይፈልግ ጥብቅ ያልሆነ የከበራ ዓይነት ነው። በአንፃሩ የከፍተኛ ዓውድ ከበራ የሚባለው በጣም ሰፊ ዝግጅት የሚደረግበት፤ አቅራቢ፤ ታዳሚም ሆነ ተሳታፊ በከፍተኛ ደረጃ የሚዘጋጅበት፤ ቀድሞ የታወቀ እና የተሠየመ በአጠቃላይ በከፍተኛ ደረጃ የሚቀናበር የከበራ ዓይነት ነው። በዚህ የከበራ ዓይነት ውስጥ ከታዳሚዎቹ የአለባበስ ምርጫ እና ሁኔታ አንስቶ በከበራው ላይ እስከሚቀርቡ የቁሳቁሶች ዓይነቶች ከፍተኛ ዝግጅት እና ቁጥጥር ይደርግበታል። የክዋኔው ሂደት ምን መምሰል እና እንዴት መሆን እንዳለበት የሚያሳስቡ ተቆጣጣሪዎች እና አስተባባሪዎችም በንቃት የሚሳተፉበት የከበራ ዓይነት ነው። ማርታ እና ማርቲንም (95) እንደሚሉት፤

> *"Rituals are performances that are repeated, patterned, and frequently include ceremonial actions that incorporate symbols, actions, repetition; and perhaps most*

significant to our being able to recognize rituals they have a frame that indicates when the ritual begins and ends."

በአንድ ከበራ ውስጥ የሚከወኑ ማናቸውም ዓይነት ድርጊቶች የባህሉን ተከታዮች እና ማህበረሰቡን የመግለፅ አቅም አላቸው። ከእነዚህ መሃከልም በከበራው ወቅት የሚደረጉ ልብሶች፣ የሚቀርቡ እና አገልግሎት ላይ የሚውሉ ምግቦች፣ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎች እና የፊት ገፅታዎች ሠፊውን ድርሻ ይይዛሉ። እነዚህም ቢሆኑ ያለ አንዳች ምክንያት እና ጥቅም የሚደረጉ አይደሉም። እያንዳንዱ ድርጊት እና ምልክት መልዕክትና ፍቺ /ትርጉም ያለው ነው። ለዚህ ማሳያነት ምግብን ወስደን እንመልከት። በአንድ ከበራ ላይ የሚቀርበው ምግብ የተለያየ ዓይነት እና ትርጉሙም ብዙ ነው። ከምግብ ጋር በተያያዘ ጉዳይ የተለያዩ ትዕምርቶች ይኖራሉ። ይህንንም በተመለከተ Danesi (2004፡ 200)፣ *"Food codes, like all other kinds of social codes are regulatory systems- they regulate what kinds of food are eaten, when they are eaten, who is allowed to eat them, and so on and so forth, these very considerably from culture to culture"* በማለት ምግብ በራሱ የራሱ የሆነ ፍቺ እና ትርጉም እንዳለው ይገልፃል። ከዚህም ጋር በተያያዘ በምግብ ስነ-ስርዓቱ ወቅት ላይ የተመጋቢዎች አቀማመጥ፣ አበላል፣ የሚበሉበት ዕቃ እና የምግቡ ዓይነት በቅጡ መታየት እና መጤን እንዳለበት ያሳስባል። ይህም በራሱ የራሱ የሆነ መልዕክት እና መረጃ ስለሚሠጥ ነው።

ሌሎች የከበራ ባህሪያት ተብለው የሚዘረዘሩ ነጥቦች አሉ። ከበራ የራሱ የሆነ ቅርፅ (መደበኛነት) አለው። ይህንንም ስንል አንድም ከበራ ድግግሞሽ የሠርክ ባህሪው ነው። መደጋገሙ ቅርፁም ሆነ ይዘቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ፣ ከቦታ ወደ ቦታ፣ ከዘመን ዘመን ተሻጋሪ እንዲሆን ያደርገዋል። የሚደጋገመውም አጋጣሚ፣ ወቅትን እና ጊዜን እየጠበቀ ነው። ሌላው በጊዜ እና በቦታ የተወሰነ ነው። ይኸውም ከበራው የሚካሄድበት ጊዜ እና ቦታው የታወቀ ነው። ከጊዜውና ከቦታው ውጪ መደረጉም እርክሠትን፣ ውግዘትን እና ተቀባይነት ማጣትን ሊያስከትል ይችላል። ለምሳሌ፣ ቀብርን ከተፈቀደለት ሥፍራ ውጪ ማከናወን፣ በዓልን ያለጊዜው እና ያለ ቦታው ማክበር እንደዚሁም ለቅሶን በጭፈራ ቤት እና ሠርግን በለቅሶ ቤት አልያም በመቃብር ቦታ ማድረግ የሚያስከትለውን ማህበራዊ እና ስነ-ልቡናዊ ጫናን እና ውጤቱን ማጤን ይቻላል። ተቀባይነት ሌላው የከበራ ዓይነተኛ ባህሪይ ነው። ተቀባይነቱም ከበራውን ከሚያካሂደው ሰው፣ ማህበረሰብ እና ባህል አንጻር የሚታይ ነው።

አንዳንድ የባህል ቅንጣቶች እና ቅርንጫፎች ከጊዜ ሂደት እና ከክዋኔ እና ታዳሚ አንፃር እየተለወጡ፣ እየተሻሻሉ እና እተቀየሩ፣ ብሎምእየቀሩ መምጣታቸው አይቀሬ ነው። ይሁን እንጂ የከበራ (*ritual*) መሠረታዊ የሆኑ ስርዓቶች እና ሂደቶች አይነኩም። ብዙውን ጊዜ በክዋኔ ውስጥ ያሉት አይነኬ የሆኑ ስርዓቶች ናቸው መረጃን እና መልዕክትን የሚያስተላልፉት የመረጃው እና የመልዕክቱ ክብደት እና ቁብም በዚህ መሠረት ሊለካ ይችላል።

ከበራ በርካታ የሆኑ አገልግሎቶች አሉት። ከእነዚህ አገልግሎቶች መሃከል ዋነኛው ማህበረሰቡን እና የባህሉን ተከታይ ማስተዋወቅ፣ ማቀራረብ እና ባለፈው እና በአሁኑ እንደዚሁም በሚመጣው ዘመን መሀል እንደ ድልድይ ሆኖ ማገልገል ነው። ይህንንም ጉዳይ ዋትስ (336) እንዲህ ሲል ያስቀምጠዋል። *"... Folk rituals help connect the present to the past, new events and relationships to previous ones, and next prospects with time- honored traditions"* ሌላው የከበራ አገልግሎት ማንነትን መግለፅ ነው። ይህም ሲባል በክዋኔው እና በከበራው አማካይነት ማህበረሰቡ ማንነቱን፣ ጥንተ አመጣጡን፣ አኗኗሩን፣ አስተሳሰቡን እና ዕምነቱን ይገልፅበታል። ከበራ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ግዴታን መወጫም ነው። አንድነትን ማጠናከር፣ ባህልን (ቅርስን) ማቆየት፣ ማስተማር (ስነ-ምግባራዊም ሆነ ኃይማኖታዊትምህርት)፣ ዕውቀትን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ፣ ማዝናናት እና መቆጣጠር፣ ወዘተ. ተጨማሪ የከበራ ተግባራት ናቸው።

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ከከበራ ዓበይት ባህሪያት መሃከል አንዱ እና ዋነኛው ክዋኔ (performance) ነው። ሁሉቱ አብረው የሚቆሙ እና የሚጓዙ እንጂ የሚነጣጠሉ ዘርፎች አይደሉም። ለዚህም ነው አንደኛው ለአንደኛው የህልውና መሠረት ነው የምንለው። ይህንን ጉዳይ *Rappaport* ሲያስረዳ *"...if there in no performance, there is no ritual; performance itself is an aspect of that which is performed" (Rappaport; 1992, 249-250)* በማለት የሁሉቱን ቁርኝት ይገልፃል። በእያንዳንዱ ከበራ ላይ በቃልም ሆነ በድርጊት አንዳች መልዕክት መተላለፉ አይቀሬ ነው። ይህም መልዕክት የባህሉን እና የባህሉን ተከታይ ማህበረሰብ ማንነት፣ ምንነት እና አጠቃላይ ህልውናውን ይገልፃል። ይህ ይሆን ዘንድ ታዲያ ክዋኔ የግድ ይላል። ያለ ክዋኔ ይህ ሁሉ የሚታሰብ አይሆንም፣ *"A ritual is an order of acts and utterances and as such is enlivened or realized only when those acts are performed and*

those utterances are voiced." (*Rappaport*, 252)። በዚህ ሃሳብ ላይ እንደምንመለከተውም ከበራ በድርጊቶች እና በንግግሮች የተሞላ ነው። እነዚህ ጉዳዮች ጎልተው የሚወጡት እና የሚሰሙትም ሲከወኑ ብቻ ነው። ያለ ክዋኔ ህልውናቸው አይሰምርም።

2.2.2 ክዋኔ እና የክዋኔ አላባውያን

ክዋኔ የሁሉም የፎክሎር ዘርፎች የጋራ ባህሪይ ነው። አንድ የፎክሎር ዘርፍ ካልተከወነ በቀር ከትውልድ ወደ ትውልድ፣ ከቦታ ወደቦታ፣ ከዘመን ወደ ዘመን ሊሸጋገር እና ቀጣይነት ሊኖረው አይችልም። ህልው ይሆን ዘንድ ክዋኔ እና ድግግሞሽ ያሻዋል። የክዋኔው ጊዜ፣ ቦታ እና መልዕክት ደግሞ የፎክሎረኛው ዋና ራስምታት ነው። በክዋኔ ወቅት የተለያዩ ባህላዊ እና ልማዳዊ ዕሴቶች ሊደረጉ እና ሊተላለፉ ይችላሉ። ይህ ይሆን ዘንድ ግን ክዋኔው የሚከወንበት አጋጣሚ የግድ ያስፈልጋል። በሌላ በኩል አጋጣሚ እና ሁኔታ ለክዋኔ አብይ ጉዳዮቹ ናቸው። ያለጊዜው፣ ያለቦታው እና ያለ አጋጣሚው የሚከወን የፎክሎር ዘርፍ ዓላማው ግቡን አይመታም፤ ይከሽፋል። የቃልም ሆነ የተግባር መልዕክትን ለማስተላለፍ እና የፎክሎሩን ዘርፍ በቅጡ ሳይባክን ለመጠቀም አጋጣሚ እና ሁኔታዎች ወሳኝነታቸው የጎላ ነው። ፊነጋን ይህንን ጉዳይ ስታስረዳ፣ *"Performance take place in many kinds of situation, from highly organized and planned to quite informal or impromptu"* ትላለች (1992፡ 95)። ይህም ከፍተኛ ዝግጅት ከሚደረግበት አጋጣሚ ጀምሮ እስከ ድንገቱ አጋጣሚ ድረስ ሁነቶች ለክዋኔ ዋና መሠረት ናቸው።

በአንድ ክዋኔ ውስጥ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ እና አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦች አሉ። ከእነዚህ መሃከልም ዓውድ (ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ መቼት)፣ ቅርፅ፣ መልክት እና አስተያየት ዋነኞቹ ናቸው። ማንኛውም ሆነ የትኛውም ክዋኔ በውስጡ ዓውድ አለው። ማርታ እና ማርቲን Dan Ben-Amosን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት ሁለት ዓይነት ዓውዶች አሉ። እነዚህም ሁኔታዊ ዓውድ (*context of situation*) እና ባህላዊ ዓውድ (*context of culture*) ናቸው። በአንድ በተወሰነ አጋጣሚ ላይ ያለውን ነገር የምንመለከትበት እና ብዙም ሰፋ የማይለው ክዋኔ ሁኔታዊ ዓውድ ይባላል። ባህላዊ ዓውድ በአንፃሩ ሰፊ እና በውስጡም ከማህበራዊ እና ባህላዊ አስተሳሰቦች አንስቶ እስከ ዕምነት ድረስ ያለውን ጉዳይ እና ዝርዝር ሁኔታዎችን የሚመለከተውን ጭምር ያጠቃልላል (137-138)።

ከእነዚህ ሁለት የአመዳደብ አይነቶች በመነሳትም አጠቃላይ የሆኑ ሁለት አይነት ዓውዶች እንዳሉ ያስረግጣሉ። እነዚህም አካላዊ ዓውድ (*physical context*) እና ማህበራዊ ዓውድ (*social context*) ናቸው። (137-138) አንድ ፎክሎሬኛ አንድ ክዋኔን ሲመለከት ከአካላዊ ዓውድ ጀምሮ ያሉትን ነገሮች ማጤን ይገባዋል። ይህም ሲባል ክዋኔው ከሚካሄድበት መልክአ ምድር ጀምሮ እስከ ውስኑ መቼት ድረስ አፍተልቦ ሆኖ መቃኘት እና መረዳት ያስፈልጋል። አካላዊ ዓውድ በውስጡ በርካታ ጉዳዮችን ይይዛል። ማርታ እና ማርቲን ከእነዚህ መሃከል አንደኛውን ሲጠቅሱ *"The physical environment also includes who is present-performers and audience members* (138) በማለት በክዋኔው ላይ ያሉትን ከዋኝ እና ታዳሚዎችንም ጭምር እንደሚያጠቃልል ያስረዳሉ። ከዚህም በተጨማሪ የከዋኝ እና የታዳሚው (የተሳታፊው) አካላዊ እንቅስቃሴ፣ የድምፅ ከፍታ እና ዝቅታ ሁሉ በዚህ ክፍል ውስጥ እንደሚጠቃለል ይገልፃሉ። የክዋኔው ድምቀት እና ፍዘት፣ መሟቀት እና ቅዝቃዜ፣ የአየሩ ሁኔታ እና የአካባቢው አቀማመጥ ሁሉ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ የአካላዊ ዓውድ ክፍሎች ናቸው። ማህበራዊ ዓውድ የሚባለው ደግሞ በበኩሉ በክዋኔው ላይ የተገኘውን ከዋኝ እና ታዳሚ (ተሳታፊ) ማህበራዊ ማንነት፣ የስራ ድርሻ፣ እምነት፣ አስተሳሰብ፣ ዕድሜ፣ ታሪካዊ ዳራ እና አጠቃላይ የሆነ ማህበራዊ ተሳትፎን የሚመለከት ነው። በክዋኔው ላይ የተገኙት ሰዎች ማህበራዊ ደረጃቸው በክዋኔው ላይ አንዳች የሆነ ተፅዕኖ ያሳርፋል። በክዋኔው ላይ የሚቀርበውን ጉዳይ እስከመወሰን ድረስ።

ከዋኝ፣ የክዋኔ አብይ አላባውያን ከሚባሉት መሃከል አንደኛው ነው። ከዋኙ የበቀለበት እና ያደገበት ማህበረሰብ ማንነት፣ ማህበራዊ ደረጃው፣ ዕድሜው፣ የአነጋገር፣ የአገላለፅ እና የአከዋወን ብቃቱ፣ የመድረክ እና የታዳሚ አያያዝ ችሎታው፣ የፈጠራ እና የአቀራረብ ክህሎቱ ሁሉ በክዋኔው ላይ ለሚመጣ አስተያየት፣ አድናቆት፣ ስምረት እና ውድቀት የማይናቅ ድርሻ አለው። ከዚህም ሌላ ከዚህ በፊት የነበረው ልምድ እና ችሎታ፣ የመሪነት እና የከዋኝነት ኃላፊነቱን የመወጣት አቅሙ፣ በዚህ ሙያ ዘርፍ ያለው ተቀባይነት እና ዝና፣ ያታው፣ የማህበራዊ ህይወቱ ሁኔታ ሁሉ በክዋኔው ላይ ጉልህ ሚና ይኖረዋል። ፊነጋን ይህንን የከዋኝ ባህሪይ ስትገልፅ

> *"How performers carry out their role(s) relying mainly on words and gestures, or also exploiting music or dance; purporting to deliver works by others (human or*

supernatural); creative or otherwise in the sense of composing during or before performance." (Finnegan; 1992, 90)

በማለት በከዋኝ ዙሪያ የሚነሱ ዓበይት ነጥቦችን ትዘረዝራለች።

ከከዋኝ ትይዩ በሆነ መልኩ በክዋኔ ላይ አብይ ተፅዕኖ መፍጠር የሚችለው ታዳሚ (ተሳታፊ) ነው። በክዋኔ ወቅት የከዋኝ እና ታዳሚ (ተሳታፊ) ሚና እንደክዋኔው እና እንደከበራው ዓይነት የተለያየ ይሆናል። ይህንን መሠረት በማድረግ ፊነጋን ስድስት ዓይነት የከዋኝ እና ታዳሚ (ተሳታፊ) ሚናዎችን የሚወስኑ የከበራ ነጥቦችን ትዘረዝራለች። (92) የመጀመሪያው በከዋኝ እና ታዳሚ (ተሳታፊ) መሃከል ግልፅ የሆነ የሚና ልዩነትን የሚፈጥር የክዋኔ አይነት ነው። ሁለተኛው ከዋኝ እና ታዳሚ በመጠኑ የሚለያዩበትን ሚና የሚፈጥር ነው። ለዚህ ማሳያ የሚሆነን አንድ ተረት በሚከወንበት ወቅት ተራች የራሱ ሚና አለው። አዳማጭም እንደዚያ። ይሁን እንጂ አዳማጭ አልፎ አልፎ መልሶችን የሚሠጥበት ነው። መሳቅ፣ ማዘን፣ መደመም፣ ማልቀስ ... በዚህ የተነሳም የከዋኝ አንዳንድ ድርጊቶች ሊሻሻሉ እና ሊስተካከሉ ይችላሉ። ይህም የከዋኝን የፈጠራ ችሎታ መጠየቁ የማይዘነጋ ነው። ቀጣዩ የሚና ልዩነት አጠቃላይ በሆነ ሁኔታ የተለያዩ ነገር ግን በአንደንድ ቦታዎች ላይ ሁለቱም ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በዝማሬ ወቅት ያለ የመቀበል እና የመሳተፍ ሚና ነው። ተሳታፊ ከከዋኝ ተቀብሎ ይዘምራል። ከዋኝም በተራው እየተቀበለ ይከውናል።

አራተኛው ነጥብ በአንዳንድ ቦታዎች እና አጋጣሚዎች ላይ የታዳሚን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቁ ናቸው። ያለ ታዳሚ ንቁ ተሳትፎ ክዋኔው ሊቀጥል የማይችልበትን አጋጣሚ የሚፈጥሩ ናቸው። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነን የተረት አጀማመር ቀመር ነው። ተራች "ተረትተረት" ሲል ታዳሚ "ላምበበረት" ካላለ እና ካልተሳተፈ ክዋኔው ሊቀጥል አይችልም። ለመስማት ፈቃደኛ የሆነ የለም ማለት ነው። ስለዚህ ከዋኝ ክዋኔውን መቀጠል አይቻለውም። ቀጣዩ የሚና ልዩነት የለም ሊባል በሚያስችል ሁኔታ በጣም ውስን ልዩነት የሚያመጣ ነው። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው የህብረዝማሬ መዝሙር ነው። በብዛት ሁሉም በአንድነት የሚለው ቢሆንም አንዳንዴ የመቀባበል ነገር አይጠፋውም። የመጨረሻው ነጥብ ደግሞ በሁለቱ መሃከል ምንም ልዩነት የማያመጣ እና ሁለቱንም አንድ የሚያደርግ የሚና

ክፍፍል የሌለበት ነው። የዚህ ማሳያ የስራ ላይ ዘፈን ነው። ሁሉም በጋራ እየዘፈነ ስራውን መስራት ነው።

ሁሉም ነገር ከግዜ እና ከስፍራ ውጪ እንደማይሆነው ሁሉ ክዋኔም እንደዚሁ የራሱ የሆነ መቼት አለው። ክዋኔው ከዚህ መቼት ውጪ ሊደረግም ሆነ ሊከወን አይቻለውም። እነዚህ መቼቶች በማህበረሰቡ እና በባህሉ ዘንድ አንዳች የሆነ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊ ከፍ ሲልም ስነ-ልቡናዊ ፋይዳ መስጠታቸው አይቀርም። ለምሳሌ ተረትን የተመለከትን እንደሆነ በሃገራች ባሉ በርካታ ባህሎች ውስጥ ብዙውን ጊዜ መቼቱ ማታ፤ አሳት-ዳር፤ ዋርካ ስር አልያም ተራቹ ቤት፤ ከዋኝ ፊት ለፊት ተቀምጦ ነው ክዋኔው የሚቀርበው። ማታ መሆኑ እና ቦታው መታወቁ ከሚወራው ተረት ጋር ተያይዞ አንዳች የሆነ ማህበራዊ አልያም ስነ-ልቡናዊ ተፅዕኖ መፍጠሩ አይቀሬ ነው። የመቃብር እና የአቀባበር ሁኔታንም ስንመለከት ከዚህ የራቀ ዓይደለም። ባህሉ እና ማህበረሰቡ ባዘዘው እና በለመደው መሠረት መቅበርም ሆነ ማቃጠል የራሱ የሆነ ጊዜ እና ስፍራ አለው። ከዚህ ውጪ የተደረገ እንደሆን ማህበራዊ እና ስነ-ልቡናዊ ቀውስ ሊያመጣ ይችላል። እነዚህን መሠል የባህል ቅንጣቶች እና ክፍሎች የራሳቸው የሆነ ገፅታ እና አገልግሎት እንዳላቸው እመሩን ነው። ማንም ያለምክንያት ማታን አይምርጥም፤ ማንም ያለምክንያት መሬት አይመርጥም። ሁሉም ትርጉም እና ፋይዳ አለው።

አንድ ክዋኔ በውስጡ በቃልም ሆነ በድርጊት የሚተላለፉ በርካታ መልዕክቶችን ሊይዝ ይችላል። ይህ እንዲሆን ሁለት ዓበይት ፍሬ ነገሮች ይነሳሉ። እነዚህም የሚተላለፈው መልዕክት ቅርፅ እና የሚተላለፍበት ቅጥ ናቸው። የቃላዊው ክዋኔ ቅርፅ በዝርው ሊሆን ይችላል፤ በግጥም መልክ ሊሆን ይችላል፤ ከዜማ ተዋህዶ በግጥም ሊቀርብ ይችላል። እነዚህ ነጥቦች የሚተላለፉበት ቅጥ ነው ዋነኛው መሳሪያ። በመጀመሪያ መልዕክቱ በቃል አልያም በተግባር ሊቀርብ ይችላል። በቃል ሲባልም ከላይ እንደተጠቀሰው በዜማ፤ በድምፅ ከፍታ እና ዝቅታ ተቀናብሮ ሊቀርብ ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ በተግባር በልዩ ልዩ እንቅስቃሴ፤ የፊት ገፅን በመቀያየር፤ አለባበስን እና አጋጊያጥን በመቀያየር መልዕክትን ማስተላለፍ ይቻላል። ሌላው ደግሞ ሁለቱንም በመቀየጥ የሰመረ መልዕክት ማስተላለፍ ይችላል። ሌላው በክዋኔ ወቅት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ የታዳሚ ከድምፅ ከፍታ እና ዝቅታ ጋር የሚቀያየር የገፅ ምስል መልስ ነው። የታዳሚ መልስ ከዋኝን እና ክዋኔን

የመቀየር፤ ድባቡን የመለወጥ አገልግሎት እና መልዕክቱንም የመወሰን ተፅዕኖ አለው። በአንዳች ክዋኔ ያልተደሰተ ታዳሚ የተቃውሞ ድምፅ ካሰማ እና ድምፁም ወደ ተግባር ከተሸጋገረ ክዋኔው ተሠናክሎ ቀረ ማለት ነው። እነዚህ መልሶች ከዋኝን ማኮሰሻ፤ ማትጊያ፤ ማበርቻ፤ ማስጠንቀቂያ፤ ማስፈራሪያ እና መቃወሚያ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህን የታዳሚ መልሶች በቅጡ ያስተዋለ ከዋኝ ክዋኔውን የማቃናት እና የማስቀጠል ክህሎት ካለው የአድናቆት መልስ ሊመጣለት ይችላል። ከዚህም ሌላ የታዳሚን መልስ በቅጡ ያስተዋለ የፎክሎር ባለሙያ የማህበረሰቡን ፍላጎት፤ስሜት፤ማንነት እና የክዋኔውን አጠቃላይ ትርጉም እና አገልግሎት መረዳት ይችላል።

3. ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ዳራ

3.1 የአካባቢው መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስትን ከመሠረቱት ዘጠኝ ክልሎች መሃከል አንዱ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ነው። ክልሉን በምዕራብ ጋምቤላ፣ በደቡብ ምዕራብ ሱዳን፣ በሰሜን ምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ ኦሮሚያ በደቡብ ደግሞ ኬንያ ያዋስኑታል። በኢትዮጵያ ካርታ ላይም በ$34^0$88'-$39^0$14' ምስራቅና $4^0$43'-$8^0$58' ሰሜን ላቲትዩድና ሎንግቲዩድ መካከል ይገኛል። የክልሉ አጠቃላይ ስፋትም 110,931.9 ስኩየር ኪሎሜትር እንደሆነ እና ይህም አጠቃላይ ከሃገራቱ 10% እንደሚሸፍን ይገመታል። ክልሉ በ13 ዞኖችና 8 ልዩ ወረዳዎች በ22 የከተማ አስተዳደሮች የተደራጀ እንደሆነ በክልሉ አማካይነት የተዘጋጀው የክልሉ ኘሮፋይል ይጠቁማል። (የብ/ም/ቤ/ባ/ቋ/ታ/ቅ/ጥ/ተ ኘሮፋይል፣2001፣1)

የደቡብ አሞ ዞን በደቡብ ክልል ካሉት 13 ዞኖች መሃከል አንዱ ሲሆን ምቹ የተፈጥሮ አካባቢ፣ ገና ጥቅም ላይ ያልዋለ የተፈጥሮ ሃብት እና ከውርጭ እስከ በርሃማ የአየር ንብረት አላቸው ከሚባሉት ዞኖች አንዱ ነው። በተጨማሪም ዞኑ ብርቅዬ የዱር አራዊትና የተለያዩ መልክአ ምድራዊ ገጽታ እና ሌሎችም የተለያዩ የተፈጥሮ እና የባሕል ሀብት ያሏቸው ከ16 በላይ ብሔረሰቦችን አካቶ ይዟል። ይህም በክልሉ ከሚገኙት 56 ብሔር ብሔረሰቦች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 28.7 በመቶውን ይሸፍናል።

ዞኑ ከክልሉ ደቡባዊ ክፍል በ4.43^0-6.46^0 ሰሜን ላቲቲይድ እና 35.79^0-36.06^0 ምስራቅ ሎንግቲዩድ መካከል ይገኛል። ዞኑ በስተሠሜን ከጋሞ ጎፋ ዞን፣ ባስኬቶ እና ኮንታ ልዩ ወረዳዎች፣ በስተደቡብ ከኬንያ፣ በስተምስራቅ ከደራሼና ከኮንሶ ልዩ ወረዳ፣ በስተደቡብ ምስራቅ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን እና በስተምዕራብ ከቤንች ማጂ ዞን እና ከሱዳን ጋር ይዋሰናል። የደቡብ አሞ ዞን የክልሉን 21 በመቶ ወይም 23535 ስኩዌር ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት በመያዝ በአንደኝነት የሚገኝ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 60% ከፊል በረሃ፣ 5.1% ወይና ደጋ፣ 0.5% ደጋና 34.4% በረሃ ነው። የዝናብ ስርጭቱም ሲታይ ከ400-1600 ሚሊ ሜትር ይደርሳል። በአሁን ወቅት የዞኑ መስተዳድር በ8 ወረዳዎች እና በአንድ የከተማ አስተዳደር የተከፈለ ሲሆን የዞኑ ዋና ከተማ ጂንካ መሆኑን የዞኑ የስነ-ሕዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና

መተግበር ዋና የሥራ ሂደት ያወጣው ዕሁፍ ይጠቁማል (በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ መንግስት የደቡብ አሞዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መመሪያ፤2002፤1-2)።

በ1999 ዓ.ም በተደረገው የሕዝብና የቤት ቆጠራ ውጤት መሠረት የዞኑ ሕዝብ ብዛት 577,673 ደርሷል። ከእነዚህ መሃከል 288,658 ወንዶች ሲሆኑ 289,035 ያህሉ ሴቶች ናቸው። የደቡብ አሞ ዞን እንደማንኛውም የክልሉ ዞኖች ሁሉ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገትና ከዚህም ጋር በተያያዘ ዘርፈ-ብዙ የስነ-ሕዝብና ልማት ችግሮች የሚታዩበት ዞን ነው። ለዞኑ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ዋና ምክንያት ደግሞ ከፍተኛ የውልደት መጠንና እየቀነሠ በመጣው የሞት መጠን መካከል ያለው የጎላ ልዩነት እንደሆነ ይኸው ዕሁፍ ይጠቁማል (ገጽ 2)።

በደቡብ አሞ ዞን ውስጥ ከሚገኙት 8 ወረዳዎች መሃከል አንዱ የበና ፀማይ ወረዳ ነው። ከ1993 ዓ.ም በፊት የሐመር-በና ወረዳ ይሠኝ ነበር። በና ፀማይ ወረዳ ከአዲስ አበባ በ725 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል። ከሀዋሳ ደግሞ በ499 ኪ.ሜ ርቀት በደቡብ ምዕራብ በኩል ይገኛል። በወረዳው ውስጥ ከአራት በላይ የብሔረሰብ አባላት ይገኛሉ። እነዚህም በና (65%) ፀማይ (28%)፣ ብራይሌ (0.6%) እና ሌሎች (6.4 %) ናቸው። በወረዳው ሁለት ዓበይት ቋንቋዎች ይነገራሉ፤ እነዚህም በኒኛ እና ፀማይኛ ናቸው። የወረዳው ዋና ከተማ ደግሞ ቀይ አፈር ትባላለች። ቀይ አፈር ከሀዋሳ 530 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች። አጠቃላይ ስፋቷ 254,907 ሄክታር ሲሆን በውስጧ 31 ቀበሌዎችንም ይዛለች። ወረዳው በሰሜን ከደቡብ አሪ፣ በደቡብ ከሐመር፣ በምዕራብ ከሰላማጎ እና በምስራቅ ከኮንሶ ልዩ ወረዳ ጋር ይዋሠናል።

የወረዳው አጠቃላይ የሕዝብ ብዛት 60,566 ሲሆን ከእነዚህ መሃከል 30,587 ወንዶች ሲሆኑ 29,979 ሴቶች ናቸው። የወረዳው ሕዝብ መተዳደሪያዎችም ከብት እርባታ (65%)፣ግብርና 30% እንዲሁም ሌሎች (የሸክላ ስራ፣ ማነብ እና አደን) 5% ያህል ናቸው። የአየር ንብረት ሁኔታውንም ስንመለከት 13.7% ወይና ደጋ፣ 81.3% ከፊል በረሃ እና 5% በረሃ ነው። በአካባቢው በብዛት በቆሎ እና ማሽላ የሚመረቱ የእህል ዓይነቶች ናቸው። የመሬቱም አጠቃቀም በአራት ዓይነት ይመደባሉ፤ የእርሻ፣ የግጦሽ፣ የደን እና የቁጥቋጦ ተብለው። የሙቀት መጠኑንም ስንመለከት ከፍተኛው 47^0c ሲሆን ዝቅተኛው 16^0c ነው። የአካባቢው አማካይ የሙቀት መጠንም 31^0c ሲሆን ሁለት ዓይነት የአየር ንብረት እንዳለው አቶ ታምራት በየነ ባዘጋጁት እና በተረጎሙት ጥራዝ ላይ ተጠቅሷል። እነዚህም 14% ወይና

ደጋ ሲሆን 86% ደግሞ በረሃ ነው (*Tamirat,* 2011: 5)። በበና ፀማይ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙት ብሔረሰቦች መሃከል ሠፊውን ቁጥር የሚይዘው እና የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው የበና ብሔረሰብ ነው።

3.2 የበና ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ እና አሠፋፈር

ስለ በና ብሔረሰብ አመጣጥ እና አሠፋፈር የሚገልፁ ብዙም የፅሁፍ መረጃዎች ባይኖሩም ያሉት ጥቂት ምንጮች የተለያየ ታሪክ እንዳለው ይገልፃሉ። አቶ ታምራት ባዘጋጁት ፅሁፍ ውስጥ የበና ብሔረሰብ በመጀመሪያ የሠፈረው ፍንቱ ተራራ ላይ ነው። ፍንቱ ተራራ በአልዱባ እና ቦሪ ቀበሌዎች መሃከል ላይ የሚገኝ ቦታ ነው (7)። በሌላ በኩል ደግሞ ጌንቶ የሚባለው ከፍ ያለ ሜዳማ ቦታ ላይ አሪኮር እና በናአኖ የተባሉት የበና ብሔረሰብ ክፍሎች ሠፍረው እንደነበር ይነገራል። ሌላው የማህበረሰቡን አመጣጥ በተመለከተ የሚሠጠው ሃሳብ ከአሪ "ገታ"፤ ከማሌ "ገርሽማ"፤ ከደባሴ "በነት"፤ ከቦረና "ፐረን" እና ከካራ "ወልመክ" የተሰኙ የብሔረሰብ ክፍሎች ከተጠቀሱት አካባቢዎች በመምጣት በአካባቢው ከመስፈራቸው በፊት ነባር ሕዝቦች በአካባቢው እንደነበሩ ይነገራል። እነዚህ ነባር ሕዝቦች "ጋሲ" በመባል ይታወቃሉ። በአጠቃላይ በበና ብሔረሰብ ውስጥ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ከተለያዩ አቅጣጫዎች የመጡና የነባር ሕዝቦች ድምር ውጤት መሆናቸውን የሃገር ሽማግሌዎች ይገልፃሉ፤

> "... ሁሉ በና መምጣቱ ከዚህ ከማሌ ነው። አንዳንዱ ከአሪ እኛ ከገዋዳ ነው። ቀሌ ማለት ነው። ... ይኸውላቹ ከቦሪ መጣ ግራማች አድነው ነው። አድነው ጋርሾ እሱ ከየት መጣ ከጅንካ መሀከል ቤተሰብ። መሀል የተባለው እዚህ ዳገት ላይ አሪ ከጅንካ ወዲህ አንድ ዳገት አለ አይደለም የዚህ ቤተሰብ ነው። እሱ ቀጥታ የት ሄደ እኛ ድሮ ታሪክ ነው የሠማሁት ቀጥታ ወደየት ነው የሄደው ወደ ዳገቱ ወደ ቦሪ ዳገቱ ላይ ወጣ።" "(ከአቶ ዳውዴ ኪሎ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፤ 18/08/03 ዓ.ም፤ 10፡25)

ከዚህ ቀደም በነበረው የብሔረሰቡ አሠፋፈር መሠረት የአካባቢው ወሰን የነበሩት ቃቆ ወንዝ አካባቢ የሚገኘው ጫሊ ተራራ፤ ዳንጉሪባባ የተባለው ሜዳማ ቦታ እና ጋሪ ወንዝ ነበሩ። ወሰኑ በማሌ በኩል ጫሊሳሌ በተባለችው ፀማይ ውስጥ በምትገኝ መንደር፤ ኢንጨቱ ቀበሌ ውስጥ በሚገኘው ዲል ተራራ፤ በክታኪሜ ተራራ፤ የብራይሌ ብሔረሰብ የሠፈረበት ቦታ፤ አሮ ተራራ፤ አለታ ወንዝ እና ማዲት ወንዝ እስከ አባካ ተራራ ድረስ ይደርሳል።

በአሁኑ ወቅት የብሔረሰቡ ወሰን በሠሜን ከአሪ፣ በሠሜን ምስራቅ ከማሌ፣ በደቡብ ከሐመር፣ በደቡብ ምዕራብ በሻዳይ፣ በምዕራብ ኩካሮ እና ሙርሲ እንደዚሁም በምስራቅ ከፀማይ ብሔረሰብ ጋር ይዋሠናል። የበና ብሔረሰብ በበና ፀማይ ወረዳ ውስጥ ቦሪ፣ አልዱባ፣ አርጎ፣ ቃቆ፣ በፎ፣ አንሶንዳ፣ ኡሩሪ እና መቀጫ በሚባሉት ቀበሌዎች ውስጥ በዋነኝነት ይገኛል። ብሔረሰቡ የሚገኝበት የመሬት አቀማመጥ ተራራማ ሲሆን የአየር ንብረቱም በብዛት ቆላማ ነው። የፀማይ፣ የአሪ፣ የሽንሰታ፣ የሀመር የካራ እና የአማራ ብሔረሰብ ከበና ብሔረሰብ ጋር በስብጥር ይኖራሉ። በ1999 ዓ.ም በተደረገው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሠረት የብሔረሰቡ ሕዝብ ብዛት 27,022 ነው።

የበና ብሔረሰብ ዋነኛ መተዳደሪያ ንብ ማነብ ነበር። በሚያመርቱት ማርም እህል፣ የጦር መሳሪያና ሌሎች ነገሮችን ይለውጡበት እንደነበር ይነገራል። አሁን ግን በዋነኝነት ከብት እርባታና በተጓዳኝ እርሻን ያከናውናሉ። ዋነኛዎቹ የእርሻ ምርቶችም ማሽላ፣ በቆሎ፣ አደንዝሬ እና ዳጉሳ ናቸው። በእርሻ ስራው በዋነኝነት የሚሳተፉት ወንዶች ሲሆኑ ሴቶችና ልጆች በብሔረሰቡ ደንብ መሠረት ከተመደበላቸው ሥራ በተጨማሪ ወንዶችን በእርሻ እንደሚያግዙ በብሔረሰቦች ምክር ቤት በባህል፣ቋንቋ፣ታሪክ እና ቅርስ ጥናት ተቋም የተዘጋጀው ጽሁፍ ይጠቁማል። (በብሔረሰቦች ምክር ቤት በባህል ቋንቋ ታሪክ እና ቅርስ ጥናት ተቋም፣2001፣235) በብሔረሰቡ ዘንድ ለከብቶች ያለው ክበሬታ እና አመለካከት ከፍ ያለ ነው። የበርካታ ከብቶች ባለቤት መሆንም የሀብት መለኪያ ተደርጎ ይወሰዳል። ብሔረሰቡ ሁለት ዓበይት ጎሳዎች እና 18 ንዑሳን ጎሳዎች አሉት።

3.3 የበና ብሔረሰብ ባህላዊ አስተዳደር

የበና ብሔረሰብ እንደ አብዛኛው የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች እና እንደ ብዙኃኑ የደቡብ ክልል ብሔረሰቦች የራሳቸው የሆነ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት እና የስልጣን ተዋረድ አላቸው። የመጀመሪያውን የባላባትነትን ስልጣን የሚይዘው "ቢታ" ይባላል። ከቢታ ስር እንደየስልጣን ተዋረዳቸው መሠረት ቆጎ፣ ጉዲል እና ከይሲ የተባሉ የስልጣን ተዋረዶች ይገኛሉ። "ቢታ" የአካባቢው ባላባት ሲሆን ለብሔረሰቡ አባላት እንደ ከፍተኛ ባለስልጣን፣ አስተዳዳሪ እና ከፈጣሪ በታች እንዳለ አካል ተደርጎ ነው የሚቆጠረው። "ቢታ" የሚመረጠው በአካባቢው ካሉት ሁለት ዓበይት ጎሳዎች "ብናስ" እና "ገላቦ" መሃከል በብናስ ስር ካለው እና "ገታ" ከተባለው ንዑስ ጎሳ ብቻ ነው። በዚህም ሳቢያ የስልጣን ርክክቡ ከአባት ወደ

የመጀመሪያ ልጅ ብቻ የሚተላለፍ በመሆኑ እስከአሁን ጊዜ ድረስ የዚህ ጎሳ አባላት ብቻ "ቢታ" ተደርገው ይመረጣሉ። ቢታ ካልሞተ በቀር ስልጣን ለልጅ አይተላለፍም። ልጅ ለመሪነት የማይበቃ እና አመለብልሹ ቢሆን እንኳን እርሱ እስኪሞት ይጠበቃል እንጂ ስልጣን ለሌላ ሰው አይሰጥም። ባላባቱ እንደሞተ ልጁ በእርሱ ቦታ ተተክቶ ነው የቀብር ስነ-ስርዓት የሚፈፀምለት። ስልጣን ካልተሸጋገረ እና ባላባት ካልተሾመ የባላባቱ ሬሳ ሳይቀበር ለበርካታ አመታትም ሊቀመጥ ይችላል።

የቢታ አገልግሎት እና የስራ ድርሻው በርካታ ነው። የተጣላ ያስታርቃል፤ አካባቢው በበሽታ እና በድርቅ በተመታ ግዜ ፀልዮ ምህረት ያመጣል፤ ያጠፋን ይገስፃል ይመክራል። ይህንንም የአካባቢው ሽማግሌ ሲገልፁ

> "...ለበና ህብዝ ባላባት ማለት ከመንግስት ስር ያለ ነው።... በአካባቢው ላይ የአየር መለዋወጥ ከመጣ እና ዝናቡ ከጠፋ ሕብዙ ገንዘብ አሠባስቦ በግ እና ከብት ገዝቶ ይሠጣል። ባላባቱም አመቱ ጥሩ አመት እንዲሆን፤ጥሩ እህል እንዲበስል ይመርቃል፤ የመመረቅ ስነ-ስርዓት ያካሄዳል ጥሩ እህል ይብሰልላችሁ፤ እህላችሁ ላይ አውሬ አይድረስበት፤ ተምች ምናምን አይምጣበትም እያለ ኢመርቃል።" (አቶ ፍቃዱ ጋሴ፤ 15/08/03 5፡20)

በሌላ በኩል ደግሞ

> "...የባላባት ስራ ፀሀይ ጊዜ ደረቅ ሆኖ ሕዝቡ ፀሃይ ሲያሸንፈው ልመና ይመጣል፤ማር ይይዛል፤ወተተ ትኩስ ይይዛል፤ ፍየል ይይዛል ይመጣና በር አለ ደንብ የሚሠራው እሱ እንደገና እግዜያር ይለምናል ድሮ የፈጠረ አምላክ አንተነው ለምነው ብለዋል ዝናብ ከዚህ አካባቢ የለም ደርቋል ሃገሩ ዝናብም የለም ብሎ እጁን ዘርግቶ በር ላይ ኢለምናል። አንካሴ ኢዞ ሽማግሌዎቹ ጋራ ቁጭ ብሎ ፍየሉ የመጣም ከዚህ ሆድ ላይ ይወጋል፤ ወግቶ ኢለምናል ከዚህ በኋላ ዝናቡ እንደ ድሮ ይዘንባል። አንዳንድ ቀን አንድ ፀሀይ ላይ ኢዘንባል። አንድ ቀን ኢቆያል ይዘንባል ከዛ እርጥብ ኢሆናል።... ባላባት ለእዝጋቤር ታቹ ነው ከዛ በዋለ ሕዝቡ እንደገና ታቹ ነው። ህዝቡ ባላባት ጋር ይመጣል ሲመጣ በቃ አብረን እንለምናለን ብሎ በቃ እዝጌያሩን ያለምናለን ባላባቱ በር ላይ በር አለ በር ላይ ደንብ የሚራው ከዚህ በዋላ በፀሀይ፡ቀን ዝናብ ይመጣል። አንዳንድ ቀን ሁለት ሶስት ቀን ቆይቶ ይመጣል። ንቡ ከዚህ አካባቢ የሚጠፋ ከሆነ ማር ቆርጦ ይመጣል ማር ቅሉ ሙሉ ሌላ ይይዛል ትንሽ እንጀራውን ቆርጦ ያመጣል። ከዚያ ቆርጦ ሲያመጣ በቃ ይለምናል ከዛ ንቡ ይመጣል ሌላ ሃገር ሙርሲም ያለ ከሆነ ውሃ ያለበት ቦታ ነው ንቡ በፀሃይ ጊዜ የሚረባው እሱ ይመጣል ወይ ቫርየት የተባለው እዚህ ወንዝ አለ ከወይጦ ከዚም እዚ ድሮ ከሌለ ይመጣል እዚ ቀፎ ውስጥ ኢገባል ከዛ በኋላ ማር ኢወጣል። ኢሄ ሁሉ የሚሆን ባላባቱ ከመረቀ በኋላ ነው። ህዝቡ ለመለመን ማር ይይዛል፤ እህል እንዳው በስልቻ እህል ልመና የሚመጣ እኮነው ኢህል ዩዩሳል ስልቻ ሶስት አራት ስልቻ ለየንጉስ ንጉስ ይመጣል ከዚ ጎረምሶች ሽክመው ይመጣል። "ኢህል የለም አባ" ሲል "ኢሽ" ዝናብ ጠፍቷል ሲል ዝናብ ኢምጣ እህል ኢብሰል ብሎ ይመርቃል ከዚያ በዋላ ኢህሉ ኢበስላል። ባላባት እንደነዚህ ኢሠራል"። (በኒ ኪሎ 14/08/03፤ 3፡40)

በማለት የባላባትን የስራ ድርሻ ይገልፃሉ።

ከቢታ በታች የሚገኘው ባለ ስልጣን ቆጎ ነው። በብሔረሰቡ ዘንድ አምስት ቆጎዎች ይገኛሉ። ሁለቱ ከአዳር (ቢኖ እና ኪሎ ዚሎ)፣ ሁለቱ ከኩርቱም (ካልዳ ዚሎ እና ውልሻ ዚሎ) እና አንዱ ከጋርሹዋ (የጉዞ ዚሎ) ናቸው። የጉዞ ዚሎ የመጣው ከጎሬ ሲሆን የመጣበት አቅጣጫ በአሪ በኩል ነው። ሲመጣም የሽክላ ማብሰያ መሳሪያዎችን ይዞ ነበር የመጣው። ከአሪ እንደመምጣቱም እራሱን የቢታ የዘር ሃረግ ክፍል አድርጎ ይመለከታል። በዚህም ሳቢያ የዳኞቹ ማህበረሠቦች ክፍል ሆኗል። ስለዚህም የባላባቱ ቀጥተኛ ተጠሪ ሆኖ ያገለግላል። ኩርቱሞች ደግሞ ከማሌ ነው የመጡት። በማንኛውም መንደር ውስጥ ባላባቱን በመወከል የተለያዩ ስራዎችን ያከናውናሉ። ባላባቱ ወደ ሌላ መንደር ከተንቀሳቀሰ ህዝቡ ማር እና ወተት ይዞ በመሄድ ይለምነዋል። እርሱም ይፀልይላቸዋል።

ጉዲል የሚባሉት ባለስልጣናት ደግሞ ማህበረሠቡን የሚያገለግሉ፣ የእርስ በእርስ ጦርነት እና ግጭት እንዳይከሰት የሚያደርጉ እና ሠላምን የሚጠብቁ ናቸው። በአንድ መንደር ውስጥ አንድ ጉዲል የሚገኝ ሲሆን ከማንኛውም ጎሳም ሆነ ንዑስ ጎሳ ሊመረጥ ይችላል። ጉዲል በየዓመቱ እሸት በሚደርስበት ወቅት የቆየውን እሳት በማጥፋት አዲስ እሳት በሠበቃ ፈጥሮ የበቆሎ እሸት ተጠብሶ እንዲበላ ያደርጋል፤ ለበቆሎ ምርቱ ፀሎት ያደርጋል፤ የዱር እንስሳት የቤት እንስሳትን እና ከብቶችን እንዳይተናኩሉ ይፀልያል። ከጉዲል በታች ያሉት ከይሲ ይባላሉ። ከይሲ ማለት የመጨረሻው ህዝብ ማለት ነው። ህዝቡ ቀጥታ ግንኙነት እና ተጠያቂነት ያለው ለጉዲል ነው። ከዚህ ሌላ "በጀ" የሚባል ጎሳ አለ። ይህ ጎሳ የሽክላ ሥራን እና የአንጥረኝነት ሥራን የሚሠራ በመሆኑ የሚናቅና ከከይሲ በታች ተደርጎ የሚታይ ነው። በብዙዎቹ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥም ተሳትፎ የለውም። ይሁን እንጂ የባላባት ሬሳን በመጠበቅ አገልግሎት ይሰጣል።

3.4 የበና ብሔረሰብ ባህላዊ እሴቶች፣ በዓላት እና ክብረ በዓላት

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ውስጥ ከሚገኙት ዞኖች መሃከል የደቡብ አሞ ዞን በብዙ መልኩ የተለያዩ ባህሎችን የያዘ እና የቱሪስት ፍሰቱም ከፍተኛ የሆነ አካባቢ ነው። በዚህ ዞን ውስጥ ከሚገኙት 16 ብሔረሰቦች መሃከል አንዱ የሆነው የበና ብሔረሰብም በርካታ የሆኑ ባህላዊ እሴቶችን፣ በዓላትን እና ክብረ በዓላትን የያዘና በዚህም ሳቢያ ለቱሪስቶች መስህብ የሆነ ነው። በዚህ ብሔረሰብ ውስጥ ከሚገኙት ባህላዊ እሴቶች፣

በዓላትና ክብረ-በዓላት መሃከል የስም አወጣጥ፤ የህፃናት አመጋገብ፤ የጋብቻ፤ የከብት ዝላይ፤ የምሽት ጭፈራ (ኢቫንጋዲ) የቤት አሠራር እና የለቅሶ ስነ-ስርዓት በዋናነት ይጠቀሳሉ። የስም አወጣጡን ስንመለከት ልጅ እንደተወለደ በሶስተኛው ቀን ጋሌ የተባለ ተክል እና ውሀ ይርከፈከፍበታል። ልጁ ወንድ ከሆነ የአባቱ የቅርብ ዘመድ የሆነች ሴት፣ልጅቷ ሴት ከሆነች የአባቷ የቅርብ ዘመድ የሆነ ወንድ ከቤት ወደ ውጪ ልጆቹን አራት ጊዜ እያስወጡ ያስገባሉ ከዚህም በኋላ ህፃኑን ለእናቱ ያስረክባሉ። ቀጥሎም ለህፃኑ ስም ያወጣሉ። ስም ያወጣው ዘመድ ትኩስ ቅቤ ይቀባል። ከብት እና ጌጣጌጥ ተሠጥቶት ስነ-ስርዓቱ ምርቃት ተደርጎ ይቋጫል። ከአራት ወራት በኋላም ህፃኑን ምግብ የማስጀመር ክብረ በዓል ይደረጋል።

በበና ዘንድ ለጋብቻ የደረሠ ወንድ መጀመሪያ ከብት መገዛል ይጠበቅበታል። ለመገዛለል ሲዘጋጅም በመጀመሪያ ለጓደኞቹ እና ለወዳጅ ዘመዶቹ ከብት ሊዘል መሆኑን አሳውቆ ይዘጋጃል። ከዝላዩ በኋላ የማጨቱ ሂደት ይቀጥላል። እስከ ትጭጭቱ ድረስም ከወተት፣ ማር እና ስጋ በቀር አይመገብም። ከዚህ በኋላ ለቤተሰብ ሽማግሌ ይልካል አልያም ሊጠልፍ ይችላል። ከብት ዘሎ ያገባት የመጀመሪያ ሚስቱ "ቢኛሬ" ትባላለች። ከእሷ በኋላ የሚያገባት ሚስት ካለች ደግሞ "ማሪ" ትባላለች። ሌላው በማህበረሰቡ የውርስ ጋብቻ "ባስኪን" የተለመደ ነው። ታላቅ ወንድም ሲሞት ታናሽ የታላቁን ሚስት ይወርሳል። በቤተሰብ ስምምነት የሚፈፀመው ጋብቻ ደግሞ "ኮሊ" ይባላል። ለጋብቻ መስፈርትነት በሚውለው የከብት ዝላይ ወቅት የተለያዩ የኢቫንጋዲ ጭፈራዎች ሊካሄዱ ይችላሉ። ኢቫንጋዲ ብዙ ጊዜ ከምሽቱ ሶስት ሠዓት በኋላ የሚደረግ የጭፈራ ስነ-ስርዓት ነው። በከብት ዝላይ ወቅት ዘላዩ በሁለተኛ ደረጃ የሚረግጠው ከብት ቀለም ታይቶ የእርሱ ስም ይሠጠዋል።[1] ከዚህ በኋላም እንደ ሁለተኛ እና እንደ መፎከሪያ ስም ሆኖ ያገለግለዋል።

[1]በሁለተኛው የከብት ቀለም መሰየሙን የአካባቢው ሰዎች "ደንብ" ነው በማለት ብቻ አልፈውታል። ይሁን እንጂ የሁለተኛ ስሙ መጠሪያ በመሆኑ እና በእንደኛው ላይ ተሸጋግሮ በሁለተኛው ላይ የሚደላደልበት በመሆኑ ስሙ ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው የሚል ግምት አለኝ። የሚፎክርበት፣ ሚስት የሚያጭበት እና የሚጠራበት ስሙ በመሆኑ።

የበና ብሔረሰብ የቤት አሠራር ሂደት ወቅት የእንበላውን ድርሻ የሚይዙት ወንዶች ናቸው። ብሔረሰቡ ከትልልቅ እንጨት እና ከሳር የሚሠራ "ሙራ" ተብሎ የሚጠራ ባህላዊ ቤት አለው። በአካባቢው ያለውን መቀት ለመቋቋም ሲባል የቤቱ ግድግዳ አይመረግም። በዚሁ የአየር ንብረት ሳቢያ በአካባቢው በብዛት የሚመረቱት የማሽላ፣ የበቆሎ እና የዳጉሳ ምርቶች ናቸው። ከእነዚህም ምርቶች ዱቄት ከጎመን ጋር በመቀላቀል የአካባቢው መለያ የሆኑት "አይዛና ኩርኩፋ" የተባሉት ምግቦች በዋነኝነት ይዘጋጃሉ። በመጠጥ ረገድ ደግሞ ከቡና ገለባ (ቅርፊት) ተቀቅሎ የሚዘጋጀው "ሾፎሮ" ተጠቃሽ መለያ ነው። በአለባበስ ረገድ ደግሞ ከለሠለሠ የበግ ቆዳ የሚዘጋጅ ባህላዊ ልብስ ለቀንና ለመኝታ ልብስነት ይጠቀማሉ። ሴቶች በዛጎል የተንቆጠቆጠ የቆዳ ልብስ ከላይና ከታች ይለብሳሉ። ፀጉራቸውን በቀጭኑ ተጎንጉነው በቅቤ የተለወሠ ቀይ አፈር ይቀባሉ። ያገባች ሴት ካላገባች ሴት በምትለብሰው ቆዳ ቅርፅ ተለይታ ትታወቃለች። ከዚህ ሌላም የማንኛውም ሠው የመጀመሪያ ሚስት ከሆነች አንገቷ ላይ "ቢኛሬ" የሚባል ጌጥ ታስራለች። ይሁንና ይህ ጌጥ የመጀመሪያ ልጇን ስትድር እንደሚፈታ ይነገራል። ወንዶች የተለያዩ የቆዳ ዓይነቶችን ከማሸረጥም አልፈው ፀጉራቸውን በተለያየ ቅርፅ ተሠርተው የተለያዩ ጌጣጌጦችን በፀጉራቸው ላይ ይሠካሉ። ከጨሌ የተሠሩ ጌጣጌጦችን በእጅ እና በእግራቸው ላይ በማሠር እንደሚያጌጡ የብሔረሰቡ ኘሮፋይል ይገልፃል። (በብሔረሠቦች ምክር ቤት በባህል በቋንቋ ታሪክና ቅርስ ጥናት ተቋም፤ 2001 ፤239)። ከዚህም ሌላ የለቅሶ ስነ-ስርዓታቸው እንደዚሁ በዋነኝነት ይጠቀሳል። ለህፃን፤ለወጣት፤ለጎልማሳ፤ለሽማግሌ እና ለባላባት የተለያየ ዓይነት የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ ይደረጋል።

4. የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ በበና ብሔረሰብ

በዚህኛው የጥናት ዕሁፍ ክፍል ውስጥ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ በበና ብሔረሰብ ዘንድ ምን እንደሚመስል ከተለያየ አቅጣጫ አንፃር እየተነተንኩ አቀርባለሁ። በመጀመሪያ ክፍሉን እንደገና በአራት ንዑሳን ክፍሎች መድቤ አስቀምጣለሁ። በቀዳሚው ንኡስ ክፍል ውስጥ የቅድመ ሞት ዝግጅቶች ምን እንደሚመስሉ አሳያለሁ። ጎልተው የሚታዩት ሞት መቅረቡን ማረጋገጫ ብልሃቶች፣ ኑዛዜ እንደዚሁም ለለቅሶ ማስሄጃ እና ለለቀስተኛው ማስተናገጃ የሚደረጉ ዝግጅቶች የሚሉት ነጥቦች ይዳሰሳሉ። ግዜ ሞት በሚለው ቀጣይ ንኡስ ክፍል ውስጥ ደግሞ ከሁነቱ በኋላ ወዲያው ስለሚደረጉ ክንዋኔዎች፣ ጉዞ ወደ መቃብር እንደዚሁም በቀብሩ ወቅት የሚደረጉ ስነ-ስርዓቶች እና ፍቺዎቻቸው እንደምን ያሉ እንደሆኑ እየተነተንኩ አሣያለሁ። በመጨረሻም ከቀብር በኋላ የሚከናወኑ ስነ-ስርዓቶች እና የቀጠሮ ለቅሶን ምንነት እና ፋይዳውን አገልግለሁ።

4.1 የቅድመ ሞት ዝግጅት

ሞት የመምጫ ምክንያቱ በጣም ብዙ ነው። በበሽታ፣ በአደጋ፣ በገዛፈቃድ፣ በቅጣት፣ በትዕዛዝ እና በብዙ ሌሎች ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል። ይሁን እንጂ የሞት መምጫ መንገዱ ብዙውን ጊዜ ከሁለት አይዘልም። አንደኛው በድንገተኛ መንገድ የሚመጣ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ተጠብቆ እና ተዘገጃጅቶ የሚጠበቅበት መንገድ ነው። የሞት መምጫ መንገድ በሃዘን ስሜት እና በአመለካከት ላይም የሚያመጣው ተፅእኖ ቀላል አይደለም። ድንገተኛ የመጣ ሞት በቀሪ እና በሠሚ ላይ የሚያመጣው ስሜት ድንገተኛ እና ያልተጠበቀ ነው። በዚህ መልክ የሚመጣውም ሃዘን ከባድ እና ጥልቅ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ አስጠንቅቆ፣አዘጋጅቶ እና ምልክት ሰጥቶ የሚመጣው ሞት በአንባሩ የሚያስከትለው የሃዘን ስሜት ብዙም የሚጎዳ እና ጥልቅ አይሆንም። ብዙውን ጊዜ በዚህ መልክ የሚመጣው ሞት ለቀጣይ ስራዎች እና ዝግጅቶችም እድል የሚሰጥ ይሆናል። አንዳንድ ጊዜም በዚህ መልክ የመጣውን ሞት እንደ ዕድል፣ግልግል፣ዕረፍት እና እንቅልፍ የሚመለከቱ ማህበረሰቦች አሉ። ለመሆኑ የበና ብሔረሰብ የሞት መምጫን የሚያውቀው እና የሚዘጋጀው እንዴት ባለ መልኩ ነው የሚለውን ቀጥለን እንመለከታለን።

4.1.1 ሞት መቅረቡን ማረጋገጫ ብልሃቶች

በበና ብሔረሰብ ዘንድ የደከመ ሰው እና እጅግ የታመመ ሰው ካለ እርስ በእርሳቸው መረጃ በመለዋወጥ አዲስ ነገር የሚፈጠር እንደሆነ ነቅተው ይጠብቃሉ። ይህም የሚሆነው በየመጠጥ ቤቱ፣ በየመንገዱ እና በተለይ ደግሞ ብዙ ሰው በሚሰበሰብበት የሀመሱ ገበያ ወቅት ነው። የታማሚው ሰው ቤተሰብ ደግሞ የደከመውን ሰው ሁኔታ ካዩ በኋላ የተለያዩ ነገሮችን ያደርጋሉ። በመጀመሪያ የታመመውን ሰው የሚጠብቅ አንድ ሰው ይመደባል። ይህ ሰው ስራው ብዙ ነው። ያስታምማል፣ መልዕክት ይቀበላል፣ ያደርሳል፣ ጠያቂ ሲመጣም የሰውየውን ሁኔታ እየነገረ እና የተፈጠሩ አዳዲስ ነገሮች ካሉ እነሱን እያስረዳ ያገለግላል። ከዚህ በኋላ ቤተሰብ የታማሚን ሁኔታ እየተመለከተ የተለያዩ ምግቦችን፣ መጠጦችን እና ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ያቀርባል። ሰውየው ላይ ሰውጥ አልታይ ብሎ ቤተሰብ ከተቸገረና ከተጨነቀ ወደ አካባቢው አዋቂ ቤት ዘንድ በመሄድ የሰውየውን ቀጣይ እጣ ፈንታ እና ሞት መቅረብ እና አለመቅረቡን ይጠይቃል። ከዚህ በኋላ አዋቂ ቤት ሄዶ በተነገረው እና በተሠጠው መልዕክት እና ትዕዛዝ መሠረት ቀጣይ ስራዎችን ያከናውናል። "ሰውየው ይቆያል ሞት ብዙም አልቀረበም" ከተባለ የማስታመሙ እና የማገልገሉ ስራ ይቀጥላል። "ሰውየው በቅቶታል ሞትም ቀርቧል" ከተባለ ቤተሰብ በመጀመሪያ እራሱን እና ሌሎች ሰዎችን በማረጋጋት በቅርብ ሰዎች አማካይነት ብቻ ከሞት በኋላ ስላለው ስነ-ስርዓት እና ክዋኔ መዘጋጀት ይጀምራል። የአካባቢው ሰዎችም የሰውየው ይበልጥ መድከም እና ሰውጥ አለማሳየት በተለያየ መልኩ መረጃ እንዲደርሳቸው ይደረጋል።

ምንም እንኳን የአዋቂ ትዕዛዝ እና ፍርድ የሚከበር እና ተቀባይነቱም ከፍተኛ ቢሆንም ሰውየው በህይወት እስካለ የደከመው ሰው ሊሞት ነው ተብሎ አይነገርም። አንድም ሰውየው ላይ ማሚረት እና ሞትን እጅግ በቶሎ እንዲመጣ መፈለግ በመሆኑ፣ አንድም ደግሞ በጠያቂ ብዛት አልያም በሚደረጉ ልዩ ልዩ ዝግጅቶች ሳቢያ ሰውየው መሞቱን እንዳያውቅ እና እንዳይሠማ ነው። ይህም የሚሆነው ሰውየው ከቤተሰቦቹ ተለይቶ ብቻውን መንገድ የሚይዝ ተንኝር በመሆኑ እንዳይፈራ እና እንዳይጨነቅ ነው። ሁለተኛ የበና ህዝብ እርስ በርስ ያለው ፍቅር እና አንዱ ለአንዱ ያለው አክብሮት የሚታወቀው በድንገተኛ ችግር እና በጭንቀት ወቅት ነው። ቀድሞ ከሠማ እና ካወቀ እርሱ እንኳን ፍላጎት ባይኖረው በሌሎች ሰዎች ጉትጎታ፣ ምክር እና ተግሳፅ ወደ ታማሚው (ሟች) ቤተሰብ በመምጣት

ሊያገለግል እና ሊሳተፍ ይችላል። በበና ህዝብ ዘንድ ይህ ነውር ነው። ማንም ያለፍላጎት እና ያለፈቃድ በሰው ጉትጎታ እና ምክር አንዳች ተግባር አንዲፈጽም አይፈቀድም። ልቡ ንፁህ ካልሆነ በቀር በስራው ብቻ እንዲያስመስል አይደረግም። ስለዚህም ለቅሶው ድንገት ተሰምቶ ወዳጅ እና ጠላት ወዲያው በሚያደርገው ነገር ነው የሚመዘነው። በእነዚህ ምክንያቶች የተነሳ ጉዳዩ ለማንም አይነገርም። ይሁን እንጂ በአጋጣሚ በሰሙ እና ባወቁ ሰዎች በኩል መረጃ መሸሉክ አይቀሬ ነው።

በእድሜ ገፋ ያለ ሰው ከታመመ እና ከደከመ ግን ይህንን ሁሉ ሳይሰማ ማድረግ ከባድ ነው። አንደኛ በባህሉ መሠረት ሽማግሌ ሰው አስታራቂ፣ መካሪ፣ ዘካሪ፣ ባላባቱ ዘንድ እየሄደም የብሔረሰቡን ችግር፣ ጥያቄ እና ስጦታ ይዞ የሚቀርብ በመሆኑ በጣም ይከበራል። ለሁለት አልያም ለሦስት ቀናት ሽማግሌው ሰው በአካባቢው ካልታየ እና ድምፁ ከጠፋ የአካባቢው ሰው ወደ ሽማግሌው ቤት ማቅናቱ አይቀሬ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በብሔረሰቡ ዘንድ ሽማግሌዎች ጠንከር ያለ ግንኙነት እና ብዙ የቤተሰብ ቁጥር ስለሚኖራቸው ይህንን ጉዳይ አለመስማት አይቻልም። አንዳንድ ሽማግሌዎች በአልጋቸው ላይ ሆነው ከጠባቂያቸው እና ከቤተሰቡ ጋር እየተነጋገሩም በቀጣይ ምን ምን ስራዎች መሰራት እንዳለባቸው እና ምን ቅድመ ዝግጅት መደረግ እንዳለበት ውይይት ያደርጋሉ፤ ትዕዛዝ እና መመሪያዎችንም ያስተላልፋሉ። እየደከመ ከመጡም ወዳጆቻቸውን፣ ቤተሰቦቻቸውን፣ ሽማግሌዎችን እና የአካባቢውን ባላባቶች ሁሉ አስጠርተው "ደክሜያለሁ መሄዴ ነው፣ መቆየት አልቻልኩም" ብለው ይናገራሉ። በህይወት ዘመናቸውም ብዙ ተሞክሮዎችን ያዩ እና ልምድም ያካበቱ በመሆናቸው ከሌሎቹ ሽማግሌዎች ጋር አብረው በመሆን ቤተሰቡን እና የአካባቢውን ሰው ሁሉ ይመክራሉ፣ ያዕናናሉ በመጨረሻም ይሠናበታሉ።

የባላባት እና የአንዳንድ ሽማግሌዎችን የሞት መድረሻ ማወቂያ ብልሃት ከላይኞቹ በተለየ መልኩ ይካሄዳል። ይህም የሚሆነው ባላባት በዘሩ፣ በስልጣኑ እና በአገልግሎቱ ረገድ የተለየ በመሆኑ ነው። ሽማግሌዎቹም ቢሆን በማስታረቅ፣ ማህበረሰቡን በማገልገል፣ በበጎ ተግባራት ህዝቡን ከጥቃት በመከላከል፣ ከባላባቱ ጋር ባላቸው ግንኙነት እና የስራ ትብብር የተነሳ በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ክብር የሚሠጣቸው ናቸው። እነዚህ ትላልቅ ሰዎች ሲደክሙ እና ሲታመሙ የሞታቸው ነገር የሚረጋገጠው እንደነሱ ትልቅ በሆነ ክዋኔ እና ቁስ ነው። በበና ብሔሰብ ዘንድ የአንድ ሰው ሀብት የሚለካው ባለው የከብት እና የንብ ቀፎ ብዛት

ነው። በዚህም የተነሳ ለክብት እና ለጠጅ ያለ አመለካከት ከፍተኛ ነው። ክብት የንካ፣ የገደለ እና የሠረቀ ዉጉዝ ነው። የማር ጠጅ የሚያዘወትር እና ከቤቱ የማይጠፋ ሰው ደግሞ በአንባሩ የተከበረ ነው። በዚህም ምክንያት የባላባት እና የአንዳንድ ሽማግሌዎች የሞት መምጫ የሚታወቀው በጠጅ አማካይነት ነው።

በጣም የደከመ እና የታመመ ባላባት ወይም ሽማግሌ ቤተሰብ የመጀመሪያ ስራው እንደቀደሙት ሰዎች ሁሉ ጠባቂ መመደብ ነው። ጠባቂው የማስታመም እና መልዕክት የማመላለስ ስራውን ያከናውናል። ከትንሽ ቀናት በኋላ ቤተሰብ ወደ ማወቂያ ብልሃቱ ተግባር ይሸጋገራል። የአካባቢው ነዋሪ ወደ ባላባቱ እና ሽማግሌው ቤት በመምጣት የተለያዩ ክብቶችን እና ማር ይሠጣል። ይህም ለቤተሰቡ፣ ለበሽተኛው እና ለአስተማሚው ነው። ቤተሰብ በመጣው ማር አማካይነት ጠጅ ይጥላል። ከሁለት እና ሦስት ቀናት በኋላ የተጣለው ጠጅ ይታያል። ጠጁ ዝም ካለና ሲቀመስም ያዝ እና ቆምጠጥ ካደረገ ሰውየው ላይ ያለው በሽታ ያዝ የሚያደርግ እና ቆምጣጣ ነው። ቤቱ ላይ ዝምታ ይሠፍንበታል ማለት ነው። ልክ እንደ ጠጁ ቤት እንደ ጋኑ። በዚህ ጊዜ የሰውየው ሞት እና መሄድ አይቀሬ በመሆኑ ቤተሰብ ለቀጣይ ስራ ይዘገጃጃል። የደከመውም ሰው ይህንን ጉዳይ ስለሚያውቀው መጨረሻውን መገመት አይቸግረውም። እርሱም ቢሆን ለቀጣይ መንገድ እና እጣፈንታው ይጠቅሙኛል የሚላቸውን ነገሮች ያደርጋል። ያኮረፈው ካለ ይቅርታ ይጠያየቃል፣ ቂም የተያያዘው ካለ ቂሙን ያነሳል። መንገደኛ ነውና መንገድ እንዲቃናለት እና እንዲሳካለት በሄደበትም ቦታ መልካም እንዲያጋጥመው ሽክሙን አራግፎ ንፁህ ሆኖ ይዘጋጃል።

በሌላ በኩል የተጣለው ጠጅ ሲሰቅ እና ሲፍነከነክ የተጣለበት ቤት ይጠበዋል። ደስታው ከበዛ እና ቤቱ ካልበቃውም ገንፍሎ ይወጣል። የዚህን ጊዜ የበሽተኛው ቤት ደስታ እና ፍሰሃ አላለቀም ማለት ነው። ቀሪ ከቤቱ አልፎ ለአካባቢው እና ለህዝቡ ሁሉ የሚሆን ሠላም እና ሳቅ አለ ማለት ነው። የዚህን ምልክት እንዳዩ የቤተሰቦች እና የአካባቢው ሰዎች እፎይታ ወደር የለውም። እንድም ሞት መከራ እና ችግር ነው። አንድም በሚሄደው ሰው ምክንያት አካባቢው ትልቅ ዋርካ ያጣል። ሰብስቦ የሚይዝ፣ የሚያስታርቅ፣ የሚለምን፣ የሚፀልይ እና የሚጠብቅ የአካባቢው ማገር ነውና። ጠጅ ለእነዚህ ሰዎች ሕይወት እና ህልፈት ዋና የምልክት መሳሪያ መሆኑ በምክንያት ነው። አንደኛ ጠጅ የትልቅ ቤት እና የትልቅ ሰው መለያ ምልክት እና ቤተሰብም ጭምር ነው። ሁለተኛ ለእነዚህ ቤት አባወራ

ከጠጅ የበለጠ ጓደኛ እና ወዳጅ የት ይገኛል። ወዳጅ ለወዳጅ ይፈላለጋል፣ይተዋወቃል፣ግንኙነቱም ጥብቅ ነው። ስለዚህ ለቤቱ አባወራ ከጠጅ የቀረበ ወዳጅ እና መስካሪ ከወደየት ይመጣል። በደረጃው ዝቅ ላለው እና በስልጣንም ሆነ በማህበራዊ አገልግሎቱ ንቁ ተሳታፊ ላልሆነ ሰው ጠጅ ምስክርነት አይቆምም። ስለ ማይተዋወቁ እና ግንኙነታቸውም እጅግ በጣም ውስን እና በሩቁ በመሆኑ። ከላይ በተዘረዘሩት ሁለት ዓበይት ነጥቦች ላይ እንደተመለከትነው ሞት መቅረቡን እና መዘግየቱ በተለያዩ ክዋኔዎች ይረጋገጣል። ካልቀረበ ጥሩ ነው። ከቀረበ ግን ወደ ቀጣይ ስነ-ስርዓቶች የሚያደርስ ክዋኔ ይካሄዳል።

4.1.2 ኑዛዜ

ሞቱ እንደቀረበ ያወቀ እና የመዳን ተስፋው እንደተሟጠጠ የተረዳ ሰው ቀጣይ ተግባሩ ኑዛዜ ነው። በበና ብሔረሰብ ዘንድ የድንገተኛ ሞትን ሃዘን እና ምሬት ከሚያጠነክሩት ምክንያቶች መሃከል አንዱ እና ዋነኛው የኑዛዜ ስነ-ስርዓት መጓደል ነው። ኑዛዜ በጣም ጠንካራ እና ከሚች ህልፈት በኋላ በቤተሰቡ ላይ ለሚከሠት ችግር፣ ደስታ፣ መከራ እና ሃዘን የአንበሳውን ድርሻ የሚይዝ ነው። የቀጣይ እጣፈንታቸውን መጨረሻ ያወቁ ሽማግሌዎች የመጀመሪያ ተግባራቸው ቤተሰባቸውን እና የአካባቢውን ሽማግሌዎች ማስጠራት ነው። ከዚህ በኋላ በተሰበሰቡት ሰዎች ፊት ከህልፈት በኋላ መከናወን ስላለባቸው ስነ-ስርዓቶች እና የሀብት ክፍፍሉ ምን መምሰል እንዳለበት ያሳስባሉ። ብዙውን ጊዜ በኑዛዜ ላይ ትኩረት የሚሠጠው ጉዳይ የመቀበሪያ ቦታ፣ የለቅሶ ዝግጅት እና ሁኔታ እንዲሁም የክብቶች ጉዳይ ነው። ሚች ለወዳጅ ዘመዶቹ ይበጃል የሚለውን ጉዳይ አፅንኦት ሰጥቶ ይናዘዛል። ኑዛዜውም ይፈፀምለት ዘንድ የተሠበሠቡትን ቤተሰቦቹን እና ሽማግሌዎችን አደራ እና ኃላፊነት ይሠጣል።

በመጀመሪያ በሚች ዘንድ ትኩረት ተሠጥቶት የሚነገረው የክብቶች፣ የሃብት እና የንብረት ክፍፍል ጉዳይ ነው። ሚች እርሱ ካለፈ በኋላ ቀሪ ቤተሰቦቹ በሠላም እና በፍቅር እንዲኖሩ ይፈልጋል። ይህ የሚሆነው ለረዥም ዓመት ሲገነባው የነበረው ስም፣ክብር እና ዝና በቤተሰቦቹ ዘንድ እንዳይደፈር እና እንዳይገረሰስ ይፈልጋል። ቤቱም እንዳይደፈር ዋና ጥረቱ ነው። ቀሪ ቤተሰብን የሚበጠብጠው እና የሚረብሸው ብዙውን ጊዜ የንብረት እና የሀብት

ክፍፍል ጉዳይ ነው። ይህ እንዳይሆን የደከመው ሰው ቀድሞ ሃብቱን እና ንብረቱን ለቤተሰቦቹ ያከፋፍላል። ያለውን ከብት ሁሉ በልጆቹ ቁጥር ልክ እንዲከፋፈል ይናዘዛል። የንብ ቀፎ ሰቅሎ ከሆነ እንደ ከብት ክፍፍሉ ሁሉ እኩል እኩል እንዲደርሳቸው ያደርጋል። የሰው እዳ ካለበት ያለበትን እዳ መጠን እና አይነት ይናዘዛል። አበዳሪ በቦታው ከተገኘ ያለውን ጥያቄ እና አስተያየት ይሠጣል። የተዘነጋ እዳ ካለ እና ምህረት ማድረግም ይፈልግ እንደሆነ ሃሳቡን ይሠጣል። የደከመው ሰው ያበደረው ነገር ካለ እና ተበዳሪም ካለ እንደዚሁ። በመጨረሻም በሃብት እና ንብረት ክፍፍል ረገድ የተሰጠውን ኑዛዜ የተቀበሉ ቤተሰቦች እና ሽማግሌዎች ያላቸውን አስተያየት እና ሃሳብ ይሠጣሉ። ቀጥሎም ልጆቹም ሆኑ ቀሪ ቤተሰቦቹ እንደተሰማሙ በማረጋገጥ ለሟች ኑዛዜውን እንደሚያስፈፅሙ እና ኃላፊነቱን እንደሚወጡ ቃል ገብተው ጉዳያቸውን ይቋጫሉ።

ሌላው በኑዛዜ ወቅት ትልቅ ትኩረት የሚሠጠው ጉዳይ የመቀበሪያ ቦታ እና የለቅሶ ሁኔታ ነው። ብዙውን ጊዜ በዕድሜ መግፋት ምክንያት ለሚመጣ ሞት የሚዘጋጁ ሰዎች ለዚህ የኑዛዜ ዓይነት በጣም ስሱ ናቸው። የመቃብር ቦታው "አልካኪቦ" የሚባል ቀበሌ ውስጥ ይገኛል። በዚህ ቦታ ላይ ደግሞ የተለያዩ የቀብር ቦታዎች አሉ። የቀብር ቦታዎቹ ስያሜ የሚሠጠው በጎሳው ስያሜ መሠረት ነው። "ሲሌ" የተባለው ጎሳ "ሲሌ" በሚባለው ቦታ ላይ ይቀበራል። ይህ የሁሉም የበና ብሔረሰብ የጋራ ጉዳይ ነው። ሟች የሚመርጠው አቅጣጫውን እና ልዩ ቦታውን ነው። *"ከእከሌ መቃብር አጠገብ ከትልቁ ድንጋይ በስተጀርባ"* እያለ ልዩ መለያ ምልክቶችን ይሠጣል። እዚያ ቦታ ላይ እንዲቀበርም አበክሮ ይናገራል። ከቤተሰቦቹ አባል መሃከል አብዛኛዎቹ የተጠቀሰውን ቦታ ማወቃቸው አይቀሬ ነው። ይህም በብዙ ለቅሶ ላይ በመገኘት እና የተለያዩ ክዋኔዎች ላይ በመሳተፍ የሚገኝ ልምድ ነው። ሟች ቦታውን የሚመርጥባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉት። አንደኛው እዚህ ቦታ አካባቢ ላይ ወዳጆቹ እና የቅርብ ሠዎቹ ተቀብረው ይሆናል። ሁለተኛ ደግሞ ለእርሱ ቤተሰቦች እና ዘሮች ተብሎ ቀድሞ የተመረጠ ሊሆን ይችላል። ባላባቶች ብዙውን ጊዜ በዚህ ጉዳይ ላይ ላይቸገሩ ይችላሉ። ባላባት የሚቀበረው በዋሻ ውስጥ ነው። ዋሻው ውስጥ ይቀመጣል እንጂ ጉድጓድ ተቆፍሮ መሬት ውስጥ አይገባም። ባላባት ነዋ። አንደኛ ዘሩ እና ጎሳው የተለየ ነው። ሁለተኛ በህይወት መሬት ላይ ሳለ በስልጣንም ሆነ በክብር ከብሔረሰቡ አባል ሁሉ ከፍ ያለ ነው። ስለዚህ ከመሬት ውስጥ መግባት ከሌሎች ጋር እኩል መሆን ነውና ከላይ እንደኖረ ሁሉ

ራሳውም ከመሬት በላይ በዋሻ ውስጥ ይቀመጣል። ሌሎቹ ግን እንደኑዛዜያቸው መሠረት ግብዓተ መሬታቸው ይፈፀማል።

የለቅሶው ሁኔታ እንዴት መሆን እንዳለበት የሚወስነው እና የሚመርጠው ሟች እና ብሔረሰቡ ነው። በበና ብሔረሰብ ዘንድ የሚለቀሰው ለህፃናት እና ለወጣቶች ብቻ ነው። ይህንን ጉዳይ የአካባቢው ሽማግሌ የሆኑት አቶ ጋያ ፊዮ ሲገልጹ

"... ትልቁ ሰው፣በጣም ያረጀው እና ሽማግሌው ሲሞት ሲል ይናዘዛል። በኑዛዜው መሀከል አንዳንዶቹ እንዳታለቅሱ ጨፍራችሁ፣ በልታችሁ፣ ጠጥታችሁ ቅበሩኝ። አሁን የኔ ሞት ዕረፍት ነው እንጂ ሞት አይደለም። ካሁን በኋላ ብናርስ ምን አደርግላችኋለሁ። ለእኔስ ከዚህ በላይ መቆየት ምን ያደርጋል። በማለት እንዳናለቅስ ይናዘዛሉ። ያልተናዘዙ እና በለቅሶው ጊዜ ሰው ሲያለቅስ ሌሎች ትላልቅ ሰዎች ይቆጣሉ። ይመክራሉ ይበቃዋል ብዙ ኖረ አይደለም ወይ ለምን ታለቅሳላችሁ። አይረፍ ነው ወይ የምትሉት በማለት ይቆጡናል "(ታለመጠየቅ፣ ሚያዚያ14/2003)

አልፎ አልፎ ግን በድንገተኛ መንገድ ለሞቱ ጎልማሶች እና ባላባቶች ይለቀሳል። የበና ሽማግሌ ብዙውን ጊዜ ሲናዘዝ የለቅሶው ሁኔታ ድል ባለ ድግስ እና በደመቀ ጭፈራ እንዲሆን ይፈልጋል። ለአላውንት ማልቀስ ነውር ነው። ከፍ ሲልም ሟችን መናቅ እና ባህሉን መጋፋት ነው። ኑዛዜ ሲያደርግም ይህንን ጉዳይ አበክሮ ያሳስባል። ለምን ቢሉ አንደኛ ሽማግሌ ሲሞት አረፈ፣ ተገላገለ፣ ሄደ፣ ተኛ ነው እንጂ ሞተ አይባልም። በበና ዘንድ ሞተ የሚባለው በምድር ላይ ብዙ ሳይቆይ፣ ቤተሰቡን እና ማህበረሰቡን ሳያገለግል፣ ሳያገባ እና ሳይወልድ የቀረን ሰው ነው። ሽማግሌ ግን አስፈላጊ የተባለውን እና የሚጠበቅበትን ሁሉ አድርጓል ተብሎ ስለሚታመን ይበቃዋል፣ ይረፍ ነው የሚባለው። በኑዛዜ ወቅትም በደንብ ጨፍራችሁ፣ ተደስታችሁ፣ በልታችሁ እና ጠጥታችሁ ቅበሩኝ ብሎ ይናዘዛል። ይሄ ለእኔ እረፍት፣ ለእናንተም ከዚህ በላይ ባረጅ ድካም እና መሠልቸትን ስለማተርፍ ይበቃኛል። ደስ ብሏቹህ ሸኙኝ ብሎ ይናዘዛል። ይህንንም ኑዛዜ ለቤተሰቦቹ እና ለክዋኔው አስተባባሪ ሽማግሌዎች አደራ ይሠጣል። በርካታ ሰዎች መጥተው ስነ-ስርዓቱ ላይ እንዲካፈሉለትም አደራ ይሠጣል። እስከ ዛሬ ድረስ ያገለገልኳቸው ሰዎች ለተወሰነ ቀን አገልግለው ይሸኙኝ ይላል።

የከብቶች እና ከከብቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ሌሎቹ በኑዛዜ ወቅት ትኩረት የሚሰጥባቸው ነጥቦች ናቸው። የከብቶች ሃብት ክፍፍል ጉዳይ ከዚህ በላይ በነበረው ክፍል

ተመልክተናል። በዚህኛው ክፍል ደግሞ ከቁጥራቸው፣ ከቀለማቸው እና ከቆዳቸው ጋር በተያያዘ የሚደረገውን ጉዞ እንመለከታለን። ሟች ሲሞት ካሉት ከብቶች መሃከል ለቤተሠቦቹ ይበቃቸዋል ብሎ ያሰበውን ያህል ካከፋፈለ በኋላ የቀሩት ከብቶች ታርደው ለለቀስተኛው እና ለማህበረሰቡ እንዲቀርቡ ይናዘዛል። አንዳንዴ በቁጥር ሊገልፅ ይችላል። በቁጥር የሚገልፁት ብዙውን ጊዜ ለሰው አውሰው መልሰው የተቀበሏቸውን ነው። ይህም አንዴ ስለወጣ ተመልሶ ይውጣ በማለት የሚደረግ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ስቀበር እንደዚህ ዓይነት ቀለም ባለው የከብት ቆዳ ቅበሩኝ ይላል። የቀለሙ ምርጫ መጀመሪያ በነበረው የከብት ቀለም መሠረት፣ በሚወደው ከብት ቀለም መሠረት እና ስያሜ ሲሰጠው (ሁለተኛ ስያሜ) በተጠራበት ቀለም መሠረት አንዱን መርጦ ይናዘዛል። በተመረጠው የከብት ቆዳም መሠረት እንዲጠቀለል እና እንዲቀበር አደራ ይላል። ከእነዚህ የኑዛዜ መልዕክቶች በኋላ አደራ እና ኃላፊነት የተሰጣቸው ሽማግሌዎች ሃላፊነቱን እንደሚወጡ ቃል በመግባት ክዋኔውን ይጨርሳሉ። ለኑዛዜው መልዕክትም በጣም ይጠነቀቃሉ። በበና ብሔረሰብ ዘንድ ሂያጅ፣ ተንኘር እና ሟች የሚሰጠው አደራ ከባድ ነው። ሃላፊነት የተቀበሉትም አደራ በመብላታቸው እና ባለመፈፀማቸው በቀሪ ሕይወታቸው አለመረጋጋት እና መከራ እንደሚገጥማቸው ያምናሉ። በዚህም ሳቢያ ኑዛዜው በተገቢው ሁኔታ እንዲያዝ እና እንዲፈፀም ያደርጋሉ።

4.1.3 ለለቅሶው ማስዬጃ እና ለለቀስተኛ ማስተናገጃ የሚደረጉ ዝግጅቶች

በበና ብሔረሰብ ዘንድ የሞተ ሰው እንደመንገደኛ ነው የሚቆጠረው። ከህይወት በኋላ ያለው ነገር ጉዞ እንደሆነ የብሔረሰቡ ሽማግሌዎች ይገልፃሉ። የሞተ ሰው ጉዞ ጀመረ እንደሚባልም አቶ ዳውዴ ኪሎ ይናገራሉ። መድረሻውም መጀመሪያ የመጣበት የፈጣሪው ስፍራ ነው ተብሎ ይታመናል። የሟች መሄድ (መሞት) እንደማይቀር ከታወቀ እና ኑዛዜ ከተደረገ በኋላ ቀጣዩ ስራ ለለቅሶው ማስዬጃ እና ለለቀስተኛ ማስተናገጃ የሚደረጉ ዝግጅቶችን መጀመር ነው። በዚህ ጊዜ ትኩረት የሚሠጣቸው ጉዳዮች የለቅሶ ቦታ ማሰናዳት፣ ቤት ማስተካከል፣ የእርድ ከብቶችን ማዘጋጀት፣ ለቅርብ ሰዎች መልዕክት መላክ እና የተለያዩ የምግብ እና የመጠጥ ዝግጅቶችን ማካሄድ ናቸው። እነዚህ ጉዳዮችም ሁለት ዓበይት

ምክንያቶችን መሠረት ያደረጉ ናቸው። ኑሃዜ እና ባህል። ስለዚህም በእነዚህ ሁለት ዓበይት ምክንያቶች ላይ በመመርኮዝ ቤተሰብ እና ወዳጅ ዘመድ ሽርጉዱን ይጀምራል።

ባላባት እና ታላቅ የሃገር ሽማግሌ ከሞተ ዝግጅቱ ሰፊ እና ደማቅ ነው። በመጀመሪያ ስራ እንዲያግዙ እና ቤት እንዲያስተካክሉ የቅርብ ቤተሰቦች ጋር መልዕክት ይላካል። መልዕክት የተላከባቸው ሰዎች ቀደም ብለው በጭምጭምታ ሰምተው ከሆነ እና በኑሃዜው ወቅት ተገኝተው ከሆነ አረቄ ይገዛሉ፤ ኩርኩፋ ያዘጋጃሉ፤ ጠላ ይጠምቃሉ፤ እንደዚሁም እንደሚችሁ ሁኔታ ጠጅ ጥለው ይቆያሉ። ከዚህ በኋላ ያዘጋጁትን ነገር ይዘው ወደ ጥሪው ቤት ይመጣሉ። ይህ ጉዳይ የሃገር ሽማግሌ ያረፈ እንደሆነ ነው። ባላባት ሲሞት ከተቃረበ ግን የማህበረሰቡ አስተዳዳሪ እና መሪ እንደመሆኑ መጠን ፍላጎት እና አቅም ያለው ሁሉ የቻለውን የማድረግ የውዴታ ግዴታ አለበት። ህዝቡን ሲመራ እና ሲያገለግል ስለቆየ የሸኘቱን ሁኔታ ለማድመቅ ሁሉም ህብረተሰብ የራሱን ርብርብ ያደርጋል። ህብረተሰቡ እና የቅርብ ቤተሰብ ከመጣ በኋላ የደከመው ሰው ቤትን የማስተካከል ስራ ይጀመራል። መኖሪያ ቤቱ ይጠረጋል፤ይፀዳል። የቤቱ ቅጥር ግቢ ተብሎ የተከበበው አካባቢ ውስጥ ሰጥ ያለ ሜዳ የመሠለ ቦታ እንዲዘጋጅ ይደረጋል። ይህንን የጉልበት ስራ በብዛት የሚያከናውኑት ወንዶች ናቸው። ሴቶች በፊናቸው ጠላ ይጠምቃሉ፤ ኩርኩፋ ያዘጋጃሉ፤ እንደዚሁም እንደሚችሁ ደረጃ እና ሁኔታ ጠጅ ይጥላሉ።

በዚህ ቅድመ ዝግጅት ጊዜ የወንዶች ወሳኝ ሚና የሚሆነው በኑሃዜው መሠረት ለእርድ የታዘዙትን ከብቶች መምረጥ እና ማዘጋጀት ነው። በተመረጠው የቀለም እና በተወሰነው የቁጥር መጠን መሠረት እያቀናጁ እና እያስተካከሉ ያስቀምጧቸዋል። እንደ ሚቹ የማህበራዊ ደረጃ መሠረት ሊመጣ ይችላል ተብሎ ለሚታሰበው ለቀስተኛ ማስተናገጃ የሚሆን ሰፊ ቦታ ይዘጋጃል። መብላት፤ መጠጣት፤ መጨፈር፤ መቀመጥ እና ስራ መስራት ለሚፈልጉ ለቀስተኞች የሚሆን ቦታ የመመደብ እና የማስተካከል ስራ ይካሄዳል። ቀድመው ለእርድ የሚሆን ከብት፤ ለመጠጥ የሚሆን አረቄ፤ ጠላ እና ጠጅ እንዲሁም ለምግብ የሚሆን ኩርኩርፋ ያመጡ የቅርብ ቤተሰቦች፤ ወዳጆች እና የአካባቢው ሰዎች ካሉ ተቀብለው በመልክ በመልኩ አስተካክለው ያስቀምጣሉ። ከመጡት ምግብ እና መጠጦች መሃከል የቅድመ ዝግጅት ስራውን እያቀላጠፉ ላሉ ሰዎች ይሠጣል። በበና ዘንድ እህል እንዲጠፋ፤ ሰው እና

ክብት እንዲራብ አይፈቀድም። ሰው በደንብ ከልቡ የሚሰራው ሆዱ ካልጎደለ እና ደስተኛ ከሆነ ነው።

በራሱ አቅም እና ሃብት ይህን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያልቻለ እና እጁ ያጠረበት ቤተሰብ የጎረቤቱን፣ የወዳጆቹን እና የአካባቢውን ሃብታሞች ፊት ለማየት ይገደዳል። ሰውየው ሲያርፍ ለለቅሶ የሚመጡ ሰዎችን ማስተናገጃ እና የዝግጅት ስራውን ለሚሠሩ ሰዎች ተገቢ የሆነ እንክብካቤ እና መልስ መሰጠት አለበት። ይህ ይሆን ዘንድ ደግሞ በቂ አቅም ሊኖር ያስፈልጋል። በዚህ መልክ ለብድር የወጣ ቤተሰብ አፍሮ አይመለስም። አበዳሪም ፊቱን ማዞር አይቻለውም። ቀሪ ቤተሰብ እና ማህበረሰብ እንዲሁም ተጓዥ መንገደኛ የሆነ ሰው እንዲያዝንባቸው አይፈልጉም። በቀሪ ሰዎች እና በተጓዥ መንፈስ አማካይነት ቀሪ ሕይወቱ እንዳይመሳቀል ይሠጋል። ስለዚህም እርሱ እሠጣለሁ እና አለግሳለሁ ብሎ ካሠበው የክብት መጠን ሌላ ተበዳሪዎች በሚጠይቁት እና እርሱ ባለው አቅም መሠረት ክብት ቆጥሮ ያስረክባል። ብድር ጠያቂም ለለቅስተኛ ማስተናገጃ የሚሆን እና ከለቅሶው በኋላ የመመለስ አቅመን ከግምት በማስገባት ይረከባል። ለቀሪ ቤተሰብ እና ለሟች መንፈስ ባለ አመለካከት የተነሳ ብድር ጠይቆ የሚያፍር ሰው የለም። ስለዚህም ብዙ ቦታ መንከራተት አያስፈልገውም። ሁለት በዛ ከተባለ ሦስት ሰው ቤት ሄዶ በሚጠይቀው ብድር የሚያገኘው መልስ ከበቂ በላይ ስለሚሆንለት አይቸገርም። ባላባትና የባላባት ቤተሰብ ግን ይህ ሁኔታ ብዙም አያሳስበውም። ምክንያቱም ወጪውን ሁሉም ችሎ የሚያከብረው እና የሚሰጠው ማህበረሰቡ ነው። ለተዋለለት ውለታ በዚህ መልክ ብድር ለመመለስ ይሞክራል።

የለቅሶው ቦታ እና ቤት ከተስተካከለ፣ የቅርብ ሰዎች ጋር መልዕክት ከተላከ እና የክብቶች ጉዳይ መልክ መልኩን ከያዘ በኋላ የአስተናጋጆቹ ስራ የሚሆነው የታመመውን ሰው መጨረሻ መጠበቅ እና ለተቀረው ሰው መልዕክቱ እንዴት ይድረስ የሚለውን ጉዳይ ማሰብ ነው። ይህ ሁሉ ቅድመ ዝግጅት ተደርጎ የደከመው ሰው ካልሞተ ሃዘንም፣ ጭንቅም፣ እፎይታም በመጠኑም ቢሆን ደስታ ነው። የተጣለው ጠጅ እና የተጠመቀው ጠላ ጣዕሙን እንዳይቀይር እና እንዳይበላሽ ስጋት አለ። ይህ ከተከሰተ እና አንጉል ሰዓት ላይ ሰውየው ከሞተ ለቀስተኛ መጉላላቱ እና መድከሙ ነው። ይህ ደግሞ ለሃዘንተኛ ቤተሰብ ሌላ ሃዘን ነው። በሌላ በኩል የሰውየው መቆየት ለቤተሰብ መጠነኛ ደስታ ሊሰጥ ይችላል። አንደኛ ስራ እስኪጠናቀቅ እና ተዘጋጅተው እስኪጨርሱ እድል ይሰጣል። ሁለተኛ በህይወት መቆየቱ

ውስጥ ውስጡን ደስታን ይፈጥርላቸዋል። በዚህ መሃል እንኳን አንዳች የተለየ ክስተት እና ለውጥ ካየ እንደ ዕድለኛ ይቆጥሩታል። በሌላው ዕንፍ ደግሞ የሰውየው መከራ እና ህመም፣ ድካም እና ጭንቀት ስለሚበዛ ቤተሰብ በጊዜው መርዘም በጣም ያዝናል። ደክሞኛል እና ይህ ለእኔ እረፍት ነው ብሎ ለሚያስብ እና ለሚናገር እንዲሁም ለሚያዕናና ተጓዥ አለማረፍ እና መቆየት ሃዘን ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የሰውየው ማረፍ እና መሄድ ለማህበረሰቡ እንዴት ይነገር፣ በቀጠሮ ይምጣ ወይስ እንደሞተ ወዲያው ይምጣ፣ ቀድመው መምጣት እና ሰውየውን መገነዝ ያለባቸውስ እነማን ናቸው፣ ከአካባቢው የራቀ ቤተሰብ እና ወዳጅ ካለስ ይህ ጉዳይ እንዴት እና በማን በኩል ይድረሰው የሚለውን ጉዳይ ተሰብስበው ይመካከሩበታል። ብዙውን ጊዜ አስከሬኑን የሚገንዙት የአካባቢው ሽማግሌዎች እና በቤተሰቡ ውስጥ በዕድሜ ገፋ ያለ ሰው ካለ ሊገንዙት ይችላሉ። በተለይ ኑዛዜ የተቀበለ እና ለሰውየው ቅርበት ያለው ሰው የግንዘት ስርዓቱን እንዲያካሂድ ይመረጣል። ሰውየው እንዳረፈ ስነ-ስርዓቱን ሊያስተባብሩ የሚችሉ እና ተሰሚነት ያላቸው ቀድመው እንዲመጡ ይደረጋል። ይህም በኑዛዜው እና በባህሉ መሠረት ክዋኔው እንዲካሄድ እንዲያደርጉ እና እንዲቆጣጠሩ ነው። አንድም የሰው ኑዛዜ የመጠበቅ እና የማስፈፀም ኃላፊነት አለባቸው። በሌላ በኩል ከተለመደው ስነ-ስርዓት ውጪ ሌላ ስራ እንዳይሰራ እና ልማዳዊ ድርጊቱ እንዳይቀር የማድረግ ሀላፊነት አለባቸው።

4.2 ጊዜ ሞት

ኑዛዜ እና ለለቅሶው ማስዒጃ እና ለለቀስተኛ ማስተናገጃ የሚደረጉ ዝግጅቶች ከተከናወኑ በኋላ የሚጠበቀው ሁነት ሞት ነው። ሟች ከሞተ እና መሞቱ ከታወቀ በኋላም እንደመጀመሪያው ሁሉ የተለያዩ ክንዋኔዎች ይደረጋሉ። ከእነዚህ መሃከልም ዋነኛዎቹ ድህረ ሞት የሚደረጉ ስነ-ስርዓቶች፣ ጉዞ ወደ ቀብር እና በቀብር ወቅት የሚደረጉ ስነ-ስርዓቶች ናቸው። በእነዚህ ዓበይት ጉዳዮች መሃከል የተለያዩ ንዑሳን ርዕሶች እና ነጥቦች መገኘታቸው አይቀሬ ነው። እነዚህም ምን እንደሚመስሉ እና በውስጣቸው ያለው ትርጉም ምን እንደሆነ እየዘረዘርኩ አመለክታለሁ።

4.2.1 ድህረ-ሞት የሚደረጉ ስነ-ስርዓቶች

አይቀሬው ሞት ከተከሠተ እና ከሆነ በኋላ የመጀመሪያው ተግባር ጥይት መተኮስ ነው። ጥይት የሚተኩሠውም የሟች የመጀመሪያ ልጅ ነው። የሟች የመጀመሪያ ልጅ የቤቱ ወራሽ እና ቀጣይ አባወራ በመሆኑ "እቤቱ ውስጥ ችግር ተፈጥሯል እና ኑ! ድረሱልኝ" በማለት ጥይት ይተኩሳል። በበና ዘንድ ጥይት የችግር እና የሃዘን መግለጫ መሳሪያ ነው። በዚህን ጊዜ ጉዳዩን ሲጠባበቁ የነበሩ እና ተኩሱን የሰሙ ሰዎች እየሮጡ ወደ ተተኮሠበት ቤት ይመጣሉ። ከዚህ በኋላ ከመጀመሪያ ልጅ በመቀጠል ሁሉም ጥይት ይተኩሳል። የጥይት ተኩሱ ሁኔታ እንደ ሟች ማንነት የሚለያይ ነው። ህፃን ልጅ ከሞተ ብዙም ጥይት አይተኮስም። የቤቱ አባወራ ብቻ ወጥቶ አንድ ጥይት ይተኩሳል። ለማረጋገጫ ይሆን ዘንድ አንድ ይደግማል። ይህ የይድረሱልኝ እና ሃዘን ገጥሞኛል ጥሪ ነው። ከዚህ በኋላ ሰው እየመጣ አምርሮ ያለቅሳል። አንድም ማህበረሰቡን ሳያገለግል እና ቤተሰቡን ሳይጠቅም ሄደ ነው። አንድም ደግሞ አቅመ ሳይደርስ ጉዞ ጀመረ ነው። ለጉዞ የሚሆነውን ልምድ እና ብርታት በህይወት ዘመኑ የቆየበት ጊዜ ይወስነዋል። በህይወት በቆየበት ጊዜ ያደረገው ነገር ሁሉ ለቀጣይ መንገዱ ስንቅ ነውና። ይህንን ሀሳብ አቶ ቃሮ ቡኔ

> "በና ህፃን ልጅ ሲሞት ብቻ ብዙ በጣም ይለቂሳል። ምን መሰለህ ህፃን ምንም አያቂም ኢኮ... (ከንፈራቸውን እየመጠጡ) በቃ ቲኒሽ ብቻ ከእኛ ጋር ሆኖ ይጨርሳል። ብዙ የለም... ሚስት የለም... ልጅ የለም... መሬትና ከብቲ የለም። በቃ ቲኒሽ ነው። እኛ ያለቂሳል። አባቱ፣ እናቱ፣ ሁሉ ልጁ የሚያቅ በና ይለቂሳል። ... ቲኒሽ ነዉ በቃ።" (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 14/2003 ዓ.ም.)

በማለት ያጠናክራሉ። ስለዚህም ህፃን እንደቆይታው እና ልምዱ አለመጥናት አምርሮ ይለቀስለታል። ህፃናት የጦር መሳሪያ ለመያዝ ጊዜያቸው ገና በመሆኑ ሳቢያ ሲሞቱ ብዙ ጥይት አይተኮስላቸውም። ለእርዳታ መጥሪያ ብቻ አንድ አልያም ሁለት ጥይት ብቻ ይተኮሳል። እንደ አዋቂዎቹ የደመቀ እና ብዙ ጥይት እንደማይተኮስላቸው ሽማግሌው አያይዘው ገልፀውልኛል።

ጥይት ለጎልማሳ፣ ለሽማግሌ እና ለባላባት የዘወትር ትጥቃቸው ነው። ካለእርሱ አይንቀሳቀሱም። አብዛኛው ሽማግሌ እና ሁሉም ባላባት መሳሪያ አለው። የሶስቱ አካላት ህልፈት እንደተሰማም የአካባቢው ሰው ሁሉ መሳሪያው ያለውን ጥይት እስኪጨርስ ድረስ ይተኩሳል። በበና ብሔረሰብ ዘንድ ጎልማሳ፣ ሽማግሌ እና ባላባት ያለውን ከብት እና ማሩን

አቅም እና ሃብት ማሳያ ነው። ሁለተኛ የጀግንነት እና የማንነት መለያ ነው። አንድ ሽማግሌ ከወጣትነቱ ጀምሮ ከመሳሪያ ጋር ያለው ግንኙነት የጠበቀ ነው። በመንገድ ሲጓዝም፣ክብቶቹን ሲያሳማራ መጠጥ ቤትም ሲገባ፣ገበያም ሲወርድ፣ሩቅ አካባቢ ተጓዥም ሲሆን መሳሪያው ዘወትር አጠገቡ ነው። በመንገድ ላይ ከበድ ያለ ችግር ካጋጠመው አልያም ሩቅ ተጓዥ ሲሆን የዱር አራዊት ካጋጠመው መሳሪያውን ይጠቀምበታል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ባለበት ቦታ ላይ ድንገት አንዳች መርዶ ከሠማ ዋና መሳሪያው ነው። ለዚህም ነው ሲሞት ውስጡ ያለው ጥይት እስኪያልቅ ድረስ የሚተኮስለት። ግንኙነታቸው የረዥም ጊዜ በመሆኑ፣ ጀግና በመሆኑ፣ ትልቅ በመሆኑ እና የለቅሶው ስነ-ስርዓት የደመቀ እንዲሆንለት ያለ ገደብ ይተኮስለታል። ባላባትም እንደዚሁ በህይወት ዘመኑ ላደረገው አስተዋፅኦ እና ማህበረሰቡን በሚገባ ስለመራ እና ስለጠበቀ የሚተኮስለት ጥይት ስፍር ቁጥር የለውም።

የለቅሶው ስነ-ስርዓት ክዋኔም እንደዚሁ እንደ እድሜ እና የስልጣን ደረጃቸው የተለያየ ነው። በተለይም በዚህ ጊዜ ለየት ያለ ስነ-ስርዓት የሚካሄደው በባላባት የለቅሶ ስነ-ስርዓት ወቅት ላይ ነው። ይኸውም ከለቅሶው ስነ-ስርዓት ጋር ተያይዞ የስልጣን ሽግግር ስነ-ስርዓት አብሮ ይካሄዳል። ባላባቱ ሲሞት ደንብ ተሠርቶለት እና ክብት ዘሎ ካገባት የመጀመሪያ ሚስቱ (ቢኛሬ) የወለደው የመጀመሪያ ልጅ የባላባትነት ስልጣኑን ይረከባል። የአካባቢው ሽማግሌዎች እና ደንብ አዋቂዎች መጥተው የባላባትነት መለያ የሆኑትን የተለያዩ ጌጣጌጦችን ከሬሳው ላይ እያነሱ ለአዲሱ ባላባት ይሠጣሉ። በሚች አንገት፣ ክንድ፣ እጅ፣ ጣት እና እግር ላይ ያሉ የተለያዩ ጌጦች በሽማግሌዎቹ አማካይነት ወልቀው በአዲሱ ተሿሚ ላይ በየቦታቸው ያደርጉለታል። ሽማግሌዎቹ ያላደረጉለት እንደሆነ ግን ንግስናው አልፀደቀም ማለት ነው። ይሁን እንጂ ስልጣኑን ከእርሱ ሌላ ማንም ሊረከበው ስለማይችል የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በቀር መፅደቁ አይቀሬ ነው። አዲሱ ባላባት ካልተሾመ በቀር የሞተው ባላባት አይቀበርም። ይኸውም አንደኛ ስልጣኑን ሳያስረክብ እንዳይሄድ፣ ማህበረሰቡ ያለ መሪ እንዳይቀር እና ባላባት ስለሆነ መቀበር ያለበት ባላባት ተሹሞ በባላባት ስነ-ስርዓት መሪነት መሆን ስላለበት ነው።

ባላባት እና በእድሜ የገፉ ሰዎች ሳይቀበሩ ከአራት ቀን እስከ አራት አመት እና ከዚያ በላይ ሊቆዩ ይችላሉ። ይህም በተለያዩ ምክንያቶች ሳቢያ ሊከሰት ይችላል። የመጀመሪያው ሩቅ ያሉ ቤተሰቦች እና ወዳጅ ዘመዶች እስኪመጡ ለመጠበቅ፣ ሁለተኛ

የደመቀ እና የተሳካ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ለማካሄድ፤ ሶስተኛው በባላባት የስልጣን ሽግግር ወቅት እንከን ከተፈጠረ ነው። በአንዳንድ አጋጣሚ የሁለተኛ እና ሦስተኛ ሚስቶች (ማሪዎች) የመጀመሪያ ልጆች በተለያየ ምክንያት ሳቢያ የስልጣን ይገባናል ጥያቄ ካነሱ እና መስማማት ካልቻሉ ባላባቱ አይቀበርም። ካልተቀበረ ደግሞ በሕይወት አለ ይመራል ማለት ነው። ስለዚህ እስኪስማሙ እና አዲሱ ባላባት ተመርጦ ስነ-ስርዓቱን እስኪያስተባብር ድረስ ሬሳው ይቀመጣል። ይህ ጉዳይ የሽማግሌ እና በሌላ የእድሜ እርከን ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች ለቅሶን የማይመለከት ነው። የሽማግሌ እና የሌሎቹ ሰዎች ለቅሶ ከሁለት እስከ አራት ቀናት ብቻ ይቆያል። በዚህ ጊዜ እሩቅ ያለ ሰው እየተጠበቀ እና ለቅሶው ላይም የተገኘው እየበላ፣እየጠጣ እና እየጨፈረ እስከ አራት ቀን ድረስ ይቆያል። አንዳንድ ሽማግሌዎች እና ሌሎች አካላት ግን ከሁለት ቀን በዘለለ እንዳታቆዩኝ ብለው ሊናዘዙ ይችላሉ። በተቻለ መጠንም በዚህች ሁለት ቀን ሰውየውን ሊመጥን የሚችል ደማቅ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ይካሄድለታል። ህፃን የሞተ እንደሆነ ግን በነጋታው ጠዋት ወዲያው ይቀበራል።

በለቅሶው ስነ-ስርዓት ወቅት የተለያዩ ጭፈራዎች ይደረጋሉ። በተለይ ለሽማግሌዎች እና ባላባቶች ይህ የተለመደ ነው። በቤቱ እና በግቢው ውስጥ በተዘጋጀው የለቅሶ ቦታ ላይ ክዋኔው ይካሄዳል። በዚህን ጊዜ በዋናነት የሚጠቀሱ አራት ዓይነት የጭፈራ ዘይቤዎች አሉ። የመጀመሪያው እና በሁሉም ዘንድ የሚከወነው "ማማሾሌ" የተባለው ጭፈራ ነው። "ማማሾሌ" ለቀስተኞች ወደ ለቅሶው ቤት እና ወደ ግቢው ሲገቡ የሚጨፈር ነው። የመጡት ሰዎች በቁጥር አስርም ሆኑ ከዚያ በላይ "ማማሾሌ" የተባለውን ዘፈን እየዘፈኑ እና እየጨፈሩ ነው የሚገቡት። አንድ ቡድን አስርም ይሁን ከዚያ በላይ የተለያዩ ቦታዎችን እና የዕድሜ ደረጃዎችን የያዙ ሰዎች በውስጡ ሊኖሩ ይችላሉ። በአንደኛው መሪነት (አውጪነት) ዘፈኑ እየተዘፈነ እና ሌሎች እየተቀበሉት በሁለተኛው እና በመጨከሪያ ስሙም እየተጨፈረ፣እየተጮከረ እና በአንዳንድ አጋጣሚዎችም እየተለቀሰ ይመጣሉ። ከዚያም ግቢው ውስጥ ሲደርሱ ራመድ ራመድ ይሉና ዘለል ብለው መሬቱን ረገጥ እያደረጉ እየዘፈኑ እና እየጨፈሩ አብረው ይገባሉ። በዚህን ጊዜ የሃዘንተኛው ቤት ቀድመው የመጡት ለቀስተኞች ተቀብለው አብረው ይጨፍራሉ። ከጭፈራው በኋላ "ቱፍታ" ይደረጋል። ቱፍታ ማለት የመጡት ለቀስተኞች ወደ ሽማግሌ የቤተሰቡ አባል ዘንድ በመሄድ ከንፈሩን ይስማሉ። ሽማግሌውም ግንባራቸው ላይ "ኡፍ..." ይልባቸዋል። ይቅለላችሁ፣ሃላብ አይምጣባችሁ

ተዕናኑ ማለት ነው። ከጭፈራው እና ከቱፍታው በኋላ የቤቱ አባወራ እና እማወራ ሾፌሮ ይሰጧቸዋል። ከቆይታ በኋላም ለመጣው ቡድን አንድ ፍየል ይሠጠዋል። እሳው አርደው ይመገቡታል። ትንሽ ቆይቶ ሌሎች ቡድኖችም እንደዚሁ "ማማሾሌ" እያሉ ይገባሉ። ለእነርሱም ተገቢው መስተንግዶ ይሠጣቸዋል። ሁለተኛውና "አረፖዶባር" የሚባለው ዘፈን እና ጭፈራ እንደ "ማማሾሌ" ሁሉ ወደ ለቅሶ ቦታ ሲገባ የሚከወን የጭፈራ አይነት ነው። ልዩነታቸው "ማማሾሌ" በዜማውም ሆነ በጭፈራው ረገድ ከ"አረፖዶባር" ይፈጥናል። ብዙውን ጊዜ በእድሜ ገፋ ያሉ ሰዎች ተሰብስበው ከመጡ እና ብዛት ካላቸው "አረፖዶባር"ን ይመርጣሉ። ብዙም እንቅስቃሴ እና ፍጥነት ስለማይጠይቅ ለእነርሱ ተመራጭ ነው።

"ዎሴ" እና "ዳንዳሸዋ" የሚባሉት የዘፈን እና የጭፈራ ዓይነቶች ደግሞ በአከዋወናቸው ለየት ይላሉ። ለቀስተኞቹ እየበሉ እና እየጠጡ ባሉበት ወቅት ግቢው ውስጥ ጭፈራ ከጠፋ እና አዲስ የሚገባ ቡድን ከሌለ የተወሰኑ ሰዎች ተጠራርተው ይገባሉ። እነዚህ የሚጠራሩት እና የሚመረጡት ሰዎች በአካባቢው ሰዎች ዘንድ በ"አዛዚያም" እና በጭፈራ የተዋጣላቸው ተብለው የታወቁ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ተጠራርተው ከቆሙ በኋላ የቀረው ለቀስተኛ ክብ ይሠራላቸዋል። እነርሱ መሃል ቆመው እየተንጎራደዱ እና እየዘለሉ ጭፈራቸውን ያቀርባሉ። በዚህን ጊዜ ክብ የሠራው ታዳሚ እያጨበጨበ እና እየዘፈነ ያግዛቸዋል። በዚህ ጊዜ በድባቡ የተደሠተ እና የነሸጠው ሰው መሃል ገብቶ ከሰዎቹ ጋር አብሮ እየጨፈረ እና ስለ ሚች ጀግንነት እና ጠንካራነት እየዘፈነ ይቆያል። በዚህ መሃል የደከመው እየተቀመጠ የበረታው እና የነሸጠው እየተነሳ ይጨፍራል። በዚህ ጊዜ ሴቶች ለቀስተኛውን የማስተናገድ እና ምግብ እና መጠጥ የማዘጋጀት እና የማቅረብ ስራ ላይ ስለሚጠመዱ በዚህ ክዋኔ ላይ ያላቸው ተሳትፎ አነስተኛ ነው። ይሁን እንጂ ዕድል እና አጋጣሚውን አግኝታ የተመለከተች እና በድባቡ የተመሠጠች ሴት መሃል ገብታ ልትጨፍር ትችላለች። ዘፈኖቹ የመሰናበቻ መልዕክትንና እስከ አለተ ሞቱ ላበረከተው አስተዋዕኦ ምስጋና እና ከበሬታን ያዘሉ ናቸው።



ምስል 1፦ የአካባቢው ነዋሪዎች ሀዘናቸውን በተያየ መልኩ ሲገልፁ

ይህ የለቅሶ ስነ-ስርዓት እየተካሄደ ባለበት ወቅት የተወሰኑ ወጣቶች በመጀመሪያው ልጅ መጠን የራሳ ማደሪያ ቤት ይሠራሉ። ከዋና ቤቱ ወጥቶ ለጉዞ የሚዘጋጅበት መሸጋገሪያ ቤት። በልጁ ልክ መሠራቱ ደግሞ በቀጣይ የአባቱን ንብረት እና ቤተሰብ የሚያስተዳድረው እርሱ በመሆኑ እና ወራሽ ስለሆነ የቤቱ ልክ እርሱ ይሆናል። በማለት አቶ በላቸው ሉማር ያስረዳሉ። በመቀጠልም

> "አባቱ ነው ዋናውን ቤት የሚይዘው አይደለም?... አዎ! አሁን እዚህ ደንብ ቤት ይሰራል። የሞተ የሚያድርበት። ከዚህ ወጥቶ ሄዶ ይቀበራል። በኃላ የቀበረ ልጁ መጥቶ በራሱ ልክ የተሰራውን ቤት ያፈርሳል። በቃ ከሰውዬ ጋር አብሮ ፈረሰ ማለት ነው። ከዚህ በኃላ የፈረሰው ቤት ታቹ ነዋ የሆነው ቤት ልጁ ወርሷል ማለት ነው። ከዚህ በኃላ ሁሉ ንብረቱ ከብቱ፣ ንቡ፣ መሬቱ ሁሉ የልጁ ሆነ ማለት ነው። ለዚህ ሲባል በልጅ ልክ የደንብ ቤት ይሰራል።" (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 14/2003 ዓ.ም.)

ሲሉ የራሳ መደሪያ ቤት በልጁ ልክ የሚሰራበትን ምክንያት ያብራራሉ። በመቀጠል የተመረጡ እና ልምድ ያላቸው ሽማግሌዎች ራሳውን የመገነዝ ስራ ይሠራሉ። በበና ብሔረሰብ ዘንድ ራሳ ቀጥ ብሎ አይቀበርም። ልክ የሟች ህልፈት እንደታወቀ የአካባቢው ትላልቅ ሽማግሌዎች እና የቅርብ ዘመድ የሆኑ ሰዎች ራሳው ያለበት ቦታ ይገባሉ። ከዚያ ቀጥሎ ሁለቱን እጆቹን ጀርባ ግንዱ ላይ ያደርጋሉ። እግሩንም ከጉልበቱ በማጠፍ ወደ ደረቱ

ቀጥሎ ሁለቱን እጆቹን ጀሮ ግንዱ ላይ ያደርጋሉ። እግሩንም ከጉልበቱ በማጠፍ ወደ ደረቱ ያስጠጋሉ። ከዚህ በኋላ እንዳይዘረጋጋ በኑሃዜው መሠረት በቀለሙ በተመረጠው የክብት ቆዳ ተጠቅልሎ ይቀመጣል። ይህ የአገናነዝ ሁኔታ ከህፃን እስከ ሽማግሌ ላሉት የሚደረግ ነው። የባላባት አገናነዝ ከዚህ በመጠኑ ለየት ያለ ነው። የግራ እጁን የግራ ጀሮ ግንዱ ላይ ያደርጉታል። ቀኝ እጁን ደግሞ ወደፊት በማምጣት በአፉ ትይዩ መዳፉን ዘርግቶ እንዲቀመጥ ይደረጋል። በመጨረሻም አልጋው ወይም መደቡ ላይ እንዲቀመጥ ያደርጉታል። በግንዘቱ ላይ እጅን ጀሮ ግንድ ላይ ማድረግ ትርጉሙ ሰፊ ነው። አንደኛ ተጓዥ ነኝና እየጮኻችሁ እና ድምፃችሁን እያሠማችሁ አታባበኝ፣ ተመለስ አትበሉኝ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ሲደክም ያለበትን ቂም፣ ቁርሾ እና ችግር ሁሉ ፈትቶ እና ንፁህ ሆኖ ነው የሚጠብቀው። ስለዚህም መንገድ ከጀመርኩ በኋላ ስለ እኔም ሆነ ስለ ሌላ ሰው ምንም መጥፎ ነገር አታሠሙኝ። ጩኸት በቃኝ፣ ሁከት በቃኝ አሁን ምንም ሳልሰማ እና ውስጤ ሳይቆሽሽ እና ሳልረክስ ቶሎ ልተኛ። ቶሎ ልሂድ ማለት መሆኑንን አቶ በላቸው ይገልፃሉ።

የባላባት ከዚህ የሚለየው የቀኝ እጁ መዘርጋት እና የራሳው መቀመጥ ነው። የአካባቢው ባላባት አቶ በኒ ኪሎ ይህ የሆነበትን ምክንያት ሲያስረዱ የግራ እጁ ጀሮ ግንድ ላይ መሆን እንደቀደመው ሁሉ ሁካታ፣ ጫጫታ፣ ለቅሶ፣ ሀሜት እና ብሶት አታሰሙኝ፣ አልሠማም ነው። የቀኝ እጁ መዘርጋት ደግሞ እስከ ዛሬ ድረስ አገልግያችኋለሁና ለዚህ አገልግሎቴ፣ ለዚህ ልፋቴ፣ ለዚህ ውለታዬ ምላሽ ምንድን ነው? ክፍያዬ የታለ ማለት ነው። (ቃለ መጠይቅ፣ሚያዚያ 18/2003 ዓ.ም.)መቀመጡም ከዚህ በፊት በስልጣኔ እና በቦታዬ ላይ ሆኜ (ተቀምጬ) እንዳገለገልኳችሁ እና እንዳስተዳደርኳችሁ ሁሉ ክፍያዬንም ሳልተኛ እዚሁ ቁጭ ብዬ እጠብቃለሁ፣ እቀበላለሁ ማለቱ ነው። በዚህ መልክ ከተገነዘ በኋላ አዲስ በተሠራለት ቤቱ ውስጥ ይቀመጣል። ይህ ቤት ለጉዞ የሚዘጋጅ ቤት ነው። የቀድሞውን ቤት ለአዲሱ ባላባት ካስረከበ እና የስልጣን መለያ ጌጣጌጦቹ ተወስደው ለአዲሱ ከተደረጉለት በኋላ ወደ አዲሱ የጉዞ መሸጋገሪያ ቤቱ እንዲገባ ይደረጋል። እዚህ ቤት ውስጥ ከገባ በኋላ ከራሳ ጠባቂው "በጅ" በስተቀር ማንም አይገባም። "በጅ"ው ከሚቹ ጋር እየተነጋገረ እና መልዕክት እየተቀበለ ለውጪ ሰዎች ያደርሳል ተብሎ ይታመናል። በጀው ማር አልቋል አምጡ ካለ ቤተሰቡ ማር ይሠጠዋል። ጠጅ የለም ጠጅ አምጡ ተብላችኋል ካለ ጠጅ ይቀርብለታል። ሽማግሌዎች ራሳው ትንሽ ከሸተተ ለምንድን ነው ራሳው የሸተተው። ለምንድን ነው ቢታ

የጠየቀው ሁሉ ይሠጠዋል። ራሳው ትንሽ ከሸተተ በጀው በእፉ አድርጎ ፊቱ ላይ ይነሠንስበታል። ቅቤም እየተቀበለ ግንባሩን ቅቤ ይቀባዋል። የተዘረጋው እጁ ላይም ቅቤውን፣ ማሩን እና ስጋውን ያስቀምጥለታል። በዚህ ሁኔታ እስኪቀበር ድረስ የለቅሶ ስነ-ስርዓቱን እና ስጦታውን ሁሉ ተቀምጦ ይመለከታል።



ምስል 2- የበና ብሔረሰብ የአገናነዝ ሁኔታ



ምስል 3- ተገንዞ በቆዳ የተጠቀለለ እራሳ

እነዚህ የግንዘት ሁኔታዎች የበናን ብሔረሰብ ማንነት እና አመለካከት የሚገልፁ ሆነው ይገኛሉ። መንገደኛ (ሟች) ህሊናው ንፁህ ሆኖ እና ተረጋግቶ እንዲጓዝ ይፈለጋል። ለዚህም ሲባል ነው ሁሉም ሰው ሲገነዝ ጆሮ ግንዱን እንዲይዝ እና እጥፍጥፍ ብሎ እንዲቀበር የሚደረገው። እንደ የአካባቢው ሽማግሌዎች ገለፃ መተጣጠፉም እንደ ጆሮ ግንድ መያዙ ሁሉ ትርጉም ያለው ነው። አንደኛው ለአቀባበር እንዲመች ነው። ሁለተኛው እና ዋናው ምክንያት ደግሞ ራሱን ብቻ ይዞ ከማንም ጋር ሳይነካካ እና ምስኪን ሆኖ እንደሚሄድ የሚያመለክት ተግባር ነው። በበና ብሔረሰብ ዘንድ ተዘረጋግቶ የሚተኛ እና ቀጥ ብሎ የሚቀበር በሰው ንብረት እና ላብ የደለበ እና ለሰው ግድ የሌለው ተደርጉ ነው የሚታሰበው።

"በና ቀጥ አድርጎ ራሳ ጉድጓድ ውስጥ አይጨምርም። ቀጥ ብሎ የሚገባ አማራ ብቻ ነው። አማራ በሰው ጉልበት የሚኖርና የህዝብ ሀብት የሚወስድ ነው። ከንቱ ጀምሮ አማራ የሰው ይበላል። ሰው ይገዛል። ይጨክናል። በና እንደዚህ አይደለም የሰው ነገር አይፈልግም። ሰላው ይሰጣል፤ ይረዳል። አይጨክኒም ለዚህ እንደ አማራ ቀጥ ብሎ ጉድጓድ መግባት የለም።" (ቃለ መጠይቅ፤ ሚያዚያ 15/2003 ዓ.ም.)

በማለት የአካባቢውን የአቀባበር ሁኔታ ወ/ሮ ሶፋ ዶቢያር ያስረዳሉ። በዚህም ምክንያት እጥፍጥፍ ብሎ እራሱንና ንፁህ ህሊናውን ይዞ እንደሄደ እና እንደሞተ ነው የሚታሰበው። በበና ብሔረሰብ ዘንድ በማንኛውም የእድሜ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሰው ተዘረጋግቶ እና ቀጥብሎ አይቀበርም።

4.2.2 ጉዞ ወደ ቀብር

ሟች ከሞተ እና በቤቱ ውስጥ እና በቤቱ አካባቢ የተለያዩ የለቅሶ ስነ-ስርዓቶች ከተካሄዱ በኋላ ጉዞ ወደ ቀብር ይደረጋል። የሟች አስከሬን ካረፈበት ለመውጣት ሲዘጋጅ አስከሬን የሚሸከሙ ሰዎች ይመረጣሉ። የሰዎቹ ምርጫ ከቤተሰቡ ጋር ባላቸው ቅርበት እና ከሟች ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ነው። ተጓዥን የሚሸኙት እና መንገድ የሚያስጀምሩት ረጅም አመት አብረውት የቆዩ ወዳጆቹ ናቸው። ሶስት ራሳ ተሸካሚዎች ተመርጠው ወደ ራሳው ቤት ይገባሉ። አራተኛው የሟች የመጀመሪያ ልጅ ነው። ሟች ጎልማሳ ወይም ሽማግሌ ከሆነ የመጀመሪያ ልጅ ቀጣይ ቤት ወራሽ እና ቤተሰብ አስተዳዳሪ ስለሆነ እንደዚሁም ከልጆቹ ሁሉ አባቱን ቀድሞ ያወቀ እና ያገኘ እርሱ በመሆኑ አባቱን የመሸኘት ኃላፊነት አለበት። ሟች ባላባት ከሆነ ደግሞ ስልጣኑን የተረከበው እና በቀጣይ ማህበረሰቡንም ጭምር የመምራት ኃላፊነት ያለበት የመጀመሪያው ልጅ የአባቱን ራሳ ከፊት በመሆን ይሸኛል። ራሳው አዲስ ከተሰራለት ማደሪያ ስፍራው ሲወጣ በጭንቅላቱ በኩል ነው። ራሳ ከቤቱ ወጥቶ በሚሸኝበት ጊዜ ከፊት በቀኝ በኩል ያለውን ቦታ የሚይዘው የመጀመሪያ ልጅ ነው። ለጎልማሳው እና ለሽማግሌው ራሳ በቀኝ በኩል አለኝታው ልጁ እንደሆነ እና የአባቱ ቀኝ እጅ እንደነበር እና ወደፊትም በዚሁ ቀጥሎ አባቱን እንደሚክስ ለማሳየት በሚል ነው። የባላባቱ ራሳ ደግሞ በቀኝ በኩል ያለው ጀሮው ክፍት ስለሆነ ለባላባቱ የሚባለውን እና የሚነገረውን ነገር ሁሉ አዲሱ ባላባት እንደ እርሱ ሆኖ እንደሚሠማ እና እንደሚያዳምጥ፤ አዳምጦም እንደሚያገለግል የሚያሳይበት ነው ተብሎ ይታመናል።

በዚህ ሁኔታ ሬሳውን ከተሸከሙ በኋላ ሬሳው ያረፈበትን ዋናውን ቤት አራት ጊዜ በመዞር ይሠናበታል። ይህ አራት ጊዜ መዞር በአራቱም አቅጣጫዎች ለሚገኙ ሰዎች መሠናበቱን የሚጠቁም ነው። ይህንን ጉዳይ አቶ ማሌ ኢሾ ሲያስረዱ በእነዚህ አራት አቅጣጫዎች (ሰሜን፣ምስራቅ፣ምዕራብ እና ደቡብ) የሚገኙ ቤተሰቦቹን፣ ወዳጆቹን እና የማህበረሰቡን ሰዎች በአጠቃላይ በቤቱ እና በቤተሰቡ አማካይነት መሠናበቱን እና መሄዱን የሚገልፅበት ተግባር ነው። ሬሳው ካለበት ቦታ ወጥቶ መንገድ ሲጀምር ማንም ሰው ከአስከሬኑ ፊት አይቆምም። ይኸውም አንደኛ ሟች መንገዱ የተቃና እና የሠመረ እንደዚሁም ከመጀመሪያ ጀምሮ መንገዱን እያየ እንዲሄድ በማሰብ የሚደረግ እንደሆነ ይገልፃሉ። በዚህ ጉዞ ወቅት ከተወሰነ ርቀት በኋላ የደከመው ተሸካሚ በሌላ ሰው እየተቀየረ፣ በየመንገዱ መሃልም ሬሳውን እያሳረፉ እና እነርሱም እያረፉ እንደገና መንገድ ይጀምራሉ። በዚህ ሂደት ሬሳውን የሚሸኝ ሰው ጥይት መተኮሱን አያቆምም። ይሄም ከኋላህ አለን፣ አይዞህ፣ በርታ የሚል መልዕክት የያዘ ነው። (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 18/2003 ዓ.ም.) ከዚህም ሌላ ከኋላህ ትተኸው የሄድከው ቤተሰብ እና ማህበረሰብ እንደደመቀ እና እንደሞቀ ይኖራል። አንተ በርታና መንገድህን ብቻ ያለሃሳብ ያዝ የሚል የተስፋ መልዕክት የያዘ ክዋኔ ይደረግለታል። ይህ በበና ብሔረሰብ ዘንድ ስንቅነቱ ለሟች ብቻ ሳይሆን ለቀሪም ጭምር ነው። ለቀሪው ቤተሰብ እና ማህበረሰብ "አይዞን እንደደመቅን እና ከዚህ በፊት እንደኖርነው ሁሉ አሁንም አብረን እንኖራለን" የሚል ተስፋ ይሠጣል። ይህም ቤተሰቡን በማፅናናት እና ተስፋ በመስጠት ረገድ ወሳኝ የሚባል ክዋኔ ነው።

ሬሳው በጉዞ ወቅት ከፊት ለፊት በአራቱ የቅርብ ሰዎቹ አማይነት ይሄዳል። ከአራቱ በኋላ ደግሞ በብሔረሰቡ ዘንድ ከፍ ያለ ተቀባይነት ያላቸው ግለሰቦችና ባላባቱ አብረው ይከተላሉ። ይህም ለሟች በዕድሜ፣በማህበራዊ ደረጃ፣ በወዳጅነት እንደዚሁም በቅርበት ካላቸው ግንኙነት የተነሳ ነው። ተጓዥን ማበረታታት እና ሂድ ግፋ የማለት ልምድ እና ብርታት ያላቸው እነርሱ ናቸውና። ከእነርሱ በኋላም የሟች የቅርብ እና የሩቅ ቤተሰብ እና ወዳጅ ዘመድ ይከተላል። በመጨረሻም ሌሎች የአካባቢው ሰዎች እና ቀባሪዎች በህብረት ጥይት እየተኮሱ ይከተላሉ። በተለይ የባላባት ሬሳ ሽኝት ከሆነ የአካባቢው (የቀበሌው) ሰው በሙሉ ሊባል በሚችል ሁኔታ ነቅሎ ወጥቶ ይሸኛል። በዚህ ጊዜ የሚተኮሰው ጥይት

የመንገድ ስንቅ ከመሆኑም በተጨማሪ በህይወት ዘመኑ ሳለ ላደረገው ነገር እና ለማህበረሰቡ ለሰጠው አገልግሎት ምስጋና እና ክበሬታ ነው።

4.2.3. በቀብር ወቅት የሚደረጉ ሥነ-ስርዓቶች

የሟች አስከሬን በህዝብ አጀብ ተከቦ የመቃብሩ ቦታ ከደረሰ በኋላ የሚደረጉት ስነ-ስርዓቶች የተለያዩ ናቸው። በመጀመሪያ ለሬሣው ማረፊያ የሚሆን ቤት እንደገና በመጀመሪያ ልጅ ቁመት ልክ ተደርጎ ይሠራል። አስከሬኑ በተሰራለት ቤት ውስጥ ከገባ በኋላ ለቀስተኛዎቹ በቡድን በቡድን እየሆኑ ይቀመጣሉ። ሽማግሌዎች እና ባላባት ለብቻ አንድ ላይ፣ ያላገቡ ወጣት ወንዶች እና ሴቶች አንድ ላይ፣ ጎልማሳዎች ለብቻ፣ መቃብር የሚቆፍሩት ስምንቱ ሰዎች ለብቻ እንደዚሁም ቤተሰብ እና የቅርብ ሰው ለብቻ ሆነው በየቡድናቸው ይቀመጣሉ። የሟቹ የመጀመሪያ ልጅ ህፃን ከሆነ ደንብ ለመስራት አቅም ስለማይኖረው አንድ ተወካይ ከሟች የቅርብ ጓደኛ መሀል ይመረጥለታል። ልጁ እና ተወካዩም አብረው ሆነው የተለያዩ ደንቦችን ማክናወን ይጀምራሉ።

በመጀመሪያ ረጅም መንገድ አቋርጦ ሲቀብር ለመጣ ለቀስተኛ ምግብ እና መጠጥ መዘጋጀት አለበት። ለእዚህ ማዘጋጃ የሚሆነውን የመጀመሪያ እሳት የሚለኩሰው እና የሚጭረው የመጀመሪያ ልጅ ነው። ይህም ለወደፊት ለሚያስተዳድረው ቤት እና ቤተሰብ ብርሃን እንደሚሰጥ እና በደስታ ቤተሰቡን እንደሚመራ ምልክት የሚሠጥበት ክዋኔ እንደሆነ ከወ/ሮ ወንገላ ሰጎ ጋር በተደረገ ውይይት ተመልክቷል። እርሱ በጫረው እና በተያያዘው እሳት ለለቀስተኛ የሚሆን ምግብ እና መጠጥ መዘጋጀት ይጀምራል። ከቤት ተርፈው የመጡት ፍየሎችም እዚሁ መቃብር ቦታ ላይ አጥር ተከልሎላቸው ይቆያሉ። ለምግብ የሚሆነውን ፍየል ገብቶ የሚመርጠው እና የሚጠቁመው የመጀመሪያ ልጅ ነው። ፍየሉ ከመጣ በኋላ የመጀመሪያ ልጅ የፍየሉን ልብ በእንጨት ይጠቁማል። ህፃን ከሆነ ደግሞ አቅም ስለሌለው የሚወጋበትን ቦታ ይጠቁማል። እርሱ በጠቆመው ቦታ ላይ ተወካይ ቀጣይ ስራውን ያከናውናል። ለአባቱ መሸኛ የሚሆነውን እና ለህዝቡ ምግብነት የሚውለውን ፍየል መምረጡ በአባቱ ፍየሎች ላይ እና በንብረቱ ላይ የማዘዝ መብት እንዳለው እና አባቱን አክብረው እና አጅበው የመጡትን ሰዎች የማመስገን እና የማስደሰት ኃላፊነት እንዳለበት የሚጠቁም ነው። ከዚህ በኋላ ያለውን ክዋኔ ሁሉ የሚመራው ወራሽና ተተኪው የመጀመሪያ ልጁ ነው።



ምስል 4- የሚች የመጀመሪያ ልጅ የስነ-ስርአቱን የመጀመሪያ እሳት እንደጫረ

በመጀመሪያ ልጅ አማካይነት የተጠቆመው ፍየል ተጠልፎ ይጣላል። ከዚያ በኋላ የመጀመሪያ ልጁ መጥቶ ልቡ ላይ አነስ ባለ ሹል እንጨት ይጠቁማል። በዚህ ጊዜ የህፃን ልጁ ተወካይ የተጠቆመው ቦታ ላይ በስለት ይወጋዋል። የመጀመሪያው ልጅ ትልቅ ከሆነ ግን ሙሉ ስራውን የሚሰራው እራሱ ነው። በበና ብሔረሰብ ዘንድ በቀብር ወቅት ከብት አንገቱ አይታረድም። ይህም የሚሆነው አንገቱ ሲታረድ በአፍንጫው ደም ስለሚወጣ ነው። የታረደው ፍየል በአፍንጫው ደም ከመለሰ መሬት ሚችን አትቀበለውም። ትመልሰዋለች ተብሎ ይታመናል። ስለዚህ በአፍንጫው ደም እንዳይመልስ የግድ አንገቱ ላይ መታረዱ ቀርቶ ልቡ ላይ ተወግቶ ህይወቱ እንዲያልፍ ይደረጋል። ልቡ ላይ ተወግቶ እንኳን እንደ ድንገት ፍየሉ በአፍንጫው ደም ከመለሰ ስጋውን ማንም አይመገበውም። ፍየሉ የረከሰ ነው። እርሱ ረክሶ ወዳጃችንን ከጉዞው ሊያደናቅፈው እና ሊያረክሰው ነው በሚል እሳቤ ስጋው ይጣላል። ለቀስተኛውም የረከሰውን ስጋ በልቶ ሚችን ከመንገዱ ማስተጓጎል እና እርሱም ራሱ መርከስ አይፈልግም። በዚህም መሠረት ለእያንዳንዱ ቡድን ፍየል ይወጋለታል። የተወጋውን ፍየል የሚገፈው የልጅ ተወካይ ተደርጎ የተመረጠው ሰው ነው። ልጁ ትልቅ ከሆነ ደግሞ ሁሉንም ስራ ራሱ ነው የሚሠራው። ተወካይ የፍየሉን ቆዳ እየገፈፈ ባለበት ወቅት የሚያግዘው እና እግር የሚይዝለት የሚቹ የመጀመሪያ ልጅ ብቻ ነው። ሚች በርካታ ልጆች ያሉት ከሆነ ደግሞ ሁሉም እንደ ቅደም ተከተላቸው አንዳንድ ፍየል ይወጋሉ።



ምስል 5- በሚች የመጀመሪያ ልጅ የተጠቆመው ፍየል በተወላዩ አማካይነት በስለት ሲወጋ



ምስል 6- የሚች የመጀመሪያ ልጅ በቆዳ ገፈፋ ወቅት ተወላዩን ሲረዳ

ሁሉም ቡድን የተወጋለትን ፍየል እና የተዘጋጀለትን ሾፍሮ እያጣጣመ ይቆያል። የፍየሎቹ ቆዳዎች ተገፈው እንዳለቁ ዛፍ ላይ ከፍ ብለው ይሰቀላሉ። በህይወት ዘመኑ ሚችን በሀብት ከፍ አድርጋችሁ ኖራችኋልና ከፍ በሉ ተብለው ይሠቀላሉ። ቀባሪዎቹ የሚመገቡት ፍየል ቆዳ ግን አይሠቀልም። የዚህ ፍየል ቆዳ ሬሳው መሬት ተቆፍሮ ሲገባ የሚለብሰው ይሆናል። ቀደም ብሎ ሚች የተናዘዘበት የከብት ዓይነት እና ቆዳ ከሆነ ቀባሪዎቹ የዚህን ከብት ስጋ ይመገባሉ። ካልተመረጠ ግን ልጅ በመረጠው ፍየል ቆዳ እንዲቀበር እና ስጋውን እነርሱ እንዲበሉት ይደረጋል። የዚህ ተግባር ትርጉም ሠውየው ሞቶ ከቤቱ ከወጣ በኋላ ቀጣይ ቤቱን የሚሠሩለት እና ይዘው የሚሸኙት እነርሱ ስለሆኑ ይሄ ግንኙነታቸው እስከ መጨረሻዋ ሰዓት ድረስ ይቀጥላል። ስለዚህም በፍየሉም መገናኘት አለባቸው እና ስጋውን ለእነርሱ ቆዳውን ለእርሱ ያደርጋሉ። የዚህን ፍየል ቆዳ የሚለብሰው ሚች ስለሆነ የሚች ቤተሰቦች እና ሌሎች ለቀስተኞች እንዲበሉት አይፈቀድም። አንድም ቀደም ብለው ስለተሰናበቱት እንደገና መገናኘት እና መነካካት የለባቸው። አንድም በዘር እና በደም ስለተገናኙ ከህልፈት በኋላ በምንም መልኩ እንዲገናኙ አይፈለግም በኋላ እንዳይጠራሩ እና እንዳይሳሳቡ ስለሚፈራ ነው። ልጁ የደረሰለት እና ሁሉንም ደንብ እየሠራ የቀበረው አባት ሬሳ ጉድጓድ ውስጥ የሚገባው በከብት ቆዳ ተሸፍኖ ነው። ልጁ ያልደረሰለትና አቅሙም የማይፈቅድ በፍየል ቆዳ ተጠቅልሎ ይቀበራል። ልጁ ሲያድግ እና አግብቶ ሲወልድ ሬሳውን

ቆፍሮ አውጥቶ በክብት ቆዳ ጠቅልሎ ሁሉንም ክዋኔ አድርጉ እንደገና ይቀብረዋል። አሁን አቅመ ስላልደረሰ በወጠጤ ፍየል ቆዳ ተጠቅልሎ ይቀበራል። ይህም ክዋኔ "ገሉ" ይባላል። ከጊዜ በኋላ ደግሞ የክብት ቆዳ ለብሶ ይቀበራል።

በጊዜ ከወጡ እና ወደ ቀብሩ ቦታ ቀድመው ከመጡ ቀጣዩ ስራ ጉድጓድ መቆፈር ነው። ጊዜው ከመሸ እና በጣም ከሩቅ ቦታ ከመጡ መቃብር ቦታው ላይ የተለያዩ ስነ-ስርዓቶችን ያካሂዳሉ እንጂ ጉድጓድ አይቆፈርም። ይህም የሚሆነው ጉድጓድ እንደተቆፈረ ሬሳው ቶሎ መግባት ስላለበት ነው። ተቆፍሮ ካደረ እና ሬሳው ካልገባ ዝናብ ሊዘንብ፤ አፈር ሊመለስበት፤ ወይንም የተለያዩ እንስሳት ሊገቡበት ይችላሉ። ይህ ደግሞ የሟች አዲሱ መኖሪያው እና የዘወትር ቤቱ ከፍት ሆኖ እንዳይቆይ እና እንዳይበላሽ በሚል የሚደረግ ነው። በማታ ደግሞ ቀብር አይደረግም። ጉዞ በማለዳ ሲጀመር ይሰምራል ካሰቡትም ይደርሳሉ፤ ከረፈደ እና ከመሸ የተጀመረ መንገድ ግን አንጉል ስለሚሆን ቀብር የሚደረገው በማለዳ ነው። መሸቶ ከተደረሰ ግን የተለያዩ ስነ ስርዓቶች እየተደረጉ ያድራሉ። ሟች ብዙም በዕድሜ ያልገፋ እና በድንገተኛ መንገድ የሞተ ስለሆነ እየተለቀሰ እና እየተበላ፤ እየተጠጣ እና ስለሟች እየተወራ ይታደራል። ነግህ ላይ ሾፎሮ የመጠጣቱ እና ፍየል የመውጋቱ ስነ-ስርዓት ይቀጥላል። ከዚያ በኋላ የመጀመሪያ ልጅ በትንሽ እንጨት ሲቆፈር የታሰበው ቦታ ላይ ጫር ያደርጋል። ስምንቱ ሰዎችም በተጫረው ቦታ ላይ በእንጨት እና በእጅ መቆፈር ይጀምራሉ። ቀጣይ ቤቱ የተረጋጋ እና መሠረቱ የጠበቀ እንዲሆን መሬቱ በአካፋና በደማ በችኮላ መቆፈር የለበትም ተብሎ ይታመናል።በእንጨት ነካ ነካ እያደረጉ በእጃቸው አፈሩን እየጠረጉ ይቆፍራሉ። ጎድጎድ ማለት ሲጀምር ሰውየው /ሟች/ ይጠቀምበት በነበረው ሾርቃ አማካይነት አፈሩ ይወጣል። የጉድጓድ አቆፋፈሩም በመጀመሪያ በክብ ቅርፅ አንድ ሜትር ያህል ወደ ውስጥ ይቆፈራል። ከዚያ በኋላ የተጠቀለለው ሬሳ ርዝመቱ ይለካና በርዝመቱ ልክ ወደ ጎን እና ጎን ይቆፈራል። ይህም የቀብሩ ቦታ ጫካ ውስጥ ስለሆነ አውሬዎች ቶሎ እንዳያገኙት በሚል ነው። ከዚህ ሌላም በቀጭን መንገድ ገብቶ ሰፋ ብሎ እንዲተኛ እና በጠባብ መንገድ ገብቶ በሰፊ መንገድ ይንዛል ተብሎ ስለሚታሰብ የሚደረግ ተግባር ነው።[2]

---

[2]. ይህ ሃሣብ ምናልባትም የሠው ልጅ ወደዚህ አለም ከሚመጣበት ተፈጥሯዊ መንገድ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችል ይመስለኛል። ልጅ በጠባብ የብልት መንገድ ከሠፊው ማህፀን እንደሚወጣው በመጣበት መንገድ እየተመለሠ ይሆናል።

ጉድጓዱ ከተዘጋጀ በኋላ ስምንቱ ሰዎች የተመገቡት ፍየል ቆዳው ተዘጋጅቶ ይቀመጣል። ሬሳው የመጣበት ቆዳ ከሁለት ቀን በላይ የቆየበት እና የደረቀ በመሆኑ እንደልብ አይተጣጠፍም። ስለዚህ ሬሳውን ወደ ጉድጓዱ ቦታ አምጥተው ቆዳውን ይፈቱለታል። ከዚያም በኋላ በአዲሱ ቆዳ መሬት ውስጥ ሳይገባ ይጠቀለላል። በህይወት ዘመኑ ታታሪ እና ትጉህ ሰው ስለነበር ከሞተ በኋላ አፈር እንዲነካው እና ችግር እንዲያይ አይደረግም። ውስጥ ከገባ በኋላ በቀኝ በኩል እንዲተኛ ይደረጋል። በቀሪው መንገዱ ቀኝ እንዲገጥመው። አቅጣጫውም የእርሱ ጎሳ ወደ መጣበት አቅጣጫ ይሆናል። ወደ በና በመጣበት አቅጣጫ ተመልሶ መንገዱን ይዞ ወደመጣበት እንዲመለስ በሚል ወደ ጎሳው መምጫ አቅጣጫ ያርፋል። በዚህ ጊዜ ለቀስተኛው ራቅ ብሎ እያለቀሰ እና እያዘነ ይመለከታል እንጂ ወደ ጉድጓድ አይጠጋም። በአቀባበሩ ሁኔታ እና በአቅጣጫው ላይ ሀሳብ፣ አስተያየት እና ማስተካከያ ካለው ራቅ ብሎ በቃል ብቻ ይናገራል። ወደ ጉድጓድ ከገባ በኋላ የመጀመሪያ ልጅ ገብቶ ጀሮውን፣ አፍንጫውን፣ አፉን፣ እና ቂጡን በቆዳ ይሸፍነዋል። ይህም በመንገዱ ላይ ምንም ወደ ውስጡ ሳይገባ እና እርሱም ሳያወጣ እንደነበረው እንዲጓዝ በሚል ነው።



ምስል 7- የመቃብር ጉድጓዱ የሚቆፈርበት ቦታ እየተስተካከለ



ምስል 8- ጉድጓዱ በመጀመሪያ በጠባቡ ወደ ውስጥ እየተቆፈረ

ልጅ የአባቱን ሬሳ ካለበሰ እና ከአዳደነ በኋላ እግሩ ካለበት አቅጣጫ አፈር ዘግኖ ይወጣል። አፈሩንም ወደ መሬት ይበትነዋል። እዚህ የቀሩት ቤተሰቦችህ እና ዘሮችህ በበና ምድር ላይ ይብዙበት። ይኑሩበት ማለት ነው። ከዚህ በኋላ ሬሳውን የቀበሩት ስምንቱ ሰዎች እና የመጀመሪያ ልጁ ጉድጓዱ ላይ ክብ ሰርተው ለጉድጓዱ ጀርባቸውን ሰጥተው ይቆሙና በተረከዛቸው ዳር ላይ ያለውን አፈር ወደ ጉድጓዱ ይከታሉ። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ዞረው በእጃቸው በደንብ ማልበስ እና መደልደል ይጀምራሉ። ይህም የመጨረሻ ስንብታችን ወቅት እንዳንተያይና ከመንገዳችን እንዳንስተጓጎል የሚል መልዕክት ያለው ነው። አንተም ጨክነህ ሂድ እኛም ጨክነን እንሸኝህ ስንተያይ እንዳንሳሳብ በሚል ያለብሱታል። ጉድጓዱ ከለበሰ እና ከተደለደለ በኋላ የመጀመሪያው ልጁ መቃብሩ ላይ ቆሞ በተወካዩ አጋዥነት ጥይት ይተኩሳል። ሟች ሌሎች ልጆች ካሉት በየተራ እየመጡ ይተኩሳሉ። የዚህ ሟች ልጅ አንድ እና እርሱም ያልደረሰ በመሆኑ በአይዞህ ባይነት ይተኩሳል። ቀጥሎ የልጁን ያህል ደንብ የሠራው ተወካይ ይተኩሳል። ከዚያ በመቀጠል ቤተሰብ በየተራ ይተኩሳል። በመጨረሻም የመተኮስ ፍላጎት ያለው ሁሉ እየወጣ ይተኩሳል። በድል ሸኝተነዋል። በድምቀት ልከነዋል ማለት ነው።

ጥይት ከተተኮሰ እና የቀብሩ ስነ-ስርዓት ካለቀ በኋላ መጨረሻ ላይ ቀባሪዎቹ ሰዎች ብቻ እጃቸውን መቃብሩ ላይ ይታጠባሉ። እነሱ ሥጋውን በበሉት ፍየል ቆዳ እርሱ በመተኛቱ፤ እስከ መጨረሻው ሰዓት ድረስ የአሸኛኘት ዝግጅቱን ስላካሄዱለት በእንድ በቀጭን መንገድ ተገናኝተዋል ተብሎ ይታመናል። ስለዚህ ከመንገድ ለመመለስ እና ከሟች ጋር ለመለያየት የተኛበት ቦታ ላይ የመንፃት ስነ-ስርዓት ያካሂዳሉ። እጃቸውን ከታጠቡ በኋላ እንደገና ሌላ ፍየል ተወግቶላቸው ይመገባሉ። የዚህ ፍየል ቆዳ ከሌሎች ቆዳዎች ጋር አብሮ ይሰቀላል። በዚህም መንፃታቸውን እና ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር መቀላቀላቸውን ማረጋገጫ ይሆንላቸዋል። በመጨረሻም ከበሉ እና ከጠጡ በኋላ ለምልክት እንዲሆን የድንጋይ ክብ በመቃብሩ ላይ ይደረድራሉ። ባላባት ሲቀበር ግን ጉድጓድ ውስጥ ስለማይገባ ክብ አይሠራለትም። በእንጨት ብቻ ዙሪያውን ይከበባል።

4.3. የድህረ ቀብር ክዋኔዎች

የግብዓተ መሬቱ ስነ-ስርዓት ከተፈጸመ በኋላ ቀጣይ ክዋኔዎች እሳው መቃብሩ ቦታ ላይ ይደረጋሉ። በመጀመሪያ ወንድም ወደ መቃብሩ ጠጋ ብሎ ቃለ መህላ ይፈጽማል። አስክሬኑ ካረፈበት ቦታ አጠገብ ሳር ቦጨቅ አድርጎ በእጁ ይይሳል። ቃሌን ከበላሁ አጠገብህ ያለው ሳር ይፍረድብኝ በሚል። ሣሩ ይጥለፈኝ፣ ዘር ብጥልበት አያፍራልኝ በማለት ቃል ይገባል። በቃሉም መሠረት ቤቱን፣ ቤተሰቡን እና ለአቅመ አዳም ያልደረሰውን ልጁን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብ እንደራስ አድርጎ ለማሳደግ ቃል ይገባል። አንተ መንገደኛ ነህ። እዚህ ለቀረው ንብረትህ እና ዘርህ አታስብ። እኔ እንደአንተ ሆኜ አውጣዋለሁ። መንገድህን ብቻ ተመልከት ስለእኛ ጉዳይ አታስብ በማለት ቃል ይገባል። ይህንን ቃለ መህላ እየፈፀመ ባለበት ወቅት የሀገር ሽማግሌዎች፣ የቤተሰቡ አባላት አብረው ይቆማሉ። የገባውን መሃላ እንዲጠብቅ እና ከወንድም የሚጠበቀውን ሁሉ እንዲያደርግ አደራ ይሰጡታል። ይፈፅም ዘንድም ዋስ እና ተቆጣጣሪ ሆነው እንደሚከታተሉ በመግለፅ ሚች እንዲሄድ ቀሪም እንዲዕናና ያደርጋሉ።

በሌላ በኩል፣ ልክ የቀብሩ እና የቃለ መህላው ስነ-ስርዓት እንዳበቃ፣ በለቅሶው ላይ ያልተገኘ፣ አርፍዶ የመጣ እና የሚጠበቅበትን አገልግሎት ያልሰጠ ሰው ይቅርታ የሚጠይቅበት ስነ-ስርዓት ይደረጋል። አርፍዶ የመጣው ሰው አልያም በለቅሶው ላይ ላልተገኘ ሰው ተወካይ የሆነ በእጁ ሳር ነጨት አድርጎ ይዞ ከሽማግሌዎቹ መሀከል አንድ ሁለቱን መርጦ ይጠራና ችግሩን ይገልፃል። ሽማግሌዎቹም ጉዳዩን ከሰሙ እና ክብደት እና ቅለቱን ከመዘኑ በኋላ ይቅርታ ጠያቂውን ሰው በመያዝ ወደ ሚች ወንድም ዘንድ ይቀርቡና ችግራቸውን ይገልፃሉ። ወንድም እና የተወሰኑ ቤተሰቦች ከሽማግሌዎቹ እና ከይቅርታ ጠያቂዎቹ ጋር በመሆን ወደ መቃብሩ ይሄዳሉ። መቃብሩ አጠገብ ተሰብስበውም ጉዳያቸውን ይነጋገራሉ። አርፋጅ ያረፈደበትን ምክንያት ይገልፃል። ክብት ለማሰማራት፣ ለመመለስ ወይም ለመፈለግ፣ ሰው ለመጠየቅ ከአካባቢው ርቆ እንደነበር እና እንደሰማም በቻለው መጠን በፍጥነት እንደመጣ ይገልፃል። የቀሪ ተወካይም የቀረበትን ምክንያት ያስረዳል። ስለዚህም በክፋት፣ በጥላቻ እና በንቀት ሳይሆን በነገሮች አለመጣጣም ምክንያት የተፈጠረ እንደሆነ ያስረዳል። ከዚህም ሌላ ከቤተሰቡ ጋር የተቀያየመ እና ጥል ያለበት ሰው በሀዘንና በመንገደኛ አይጨክንም በሚል ወደ ለቅሶው ቦታ ይመጣል። ከዚህ በኋላም በሽማግሌዎቹ

አማላጅነት በቀሪ ህይወታቸው እና ግንኙነታቸው እንዳይቃቃሩ እና ቂም እንዳይያያዙ በያዙት ለምለም ሳር አማካይነት ቀሪ ዘመናቸው እንደዚህ ቀደመ ሁሉ ለምለም እንዲሆን ይጠይቃሉ። ሽማግሌዎችም የሚች ቤሰቦች እና የሚች ሬሳ የሰዎቹን ይቅርታ እንዲቀበሉ እና ቀሪዎቹም እንደቀደመው ሁሉ አብረው በፍቅር እና በመተሳሰብ እዲኖሩ ያስማማሉ። ይቅርታ ጠያቂም ለይቅርታው ስምረት ይሆንለት ዘንድ ፍየል እንደሚሰጥ ቃል ይገባል። በዚህ መሠረት በለቅሶው ሂደት በለቀስተኛ እና በሚች ቤተሰብ መሀከል ያለ ክፍተት እየተሸፈነ እና መቃቃሩም እየረገበ እንዲሄድ ይደረጋል። በዚህ ወቅትም የሽማግሌዎች ሚና ጎልቶ ይታያል።

የቃለ መሃላው እና የይቅርታው ስነ-ስርዓት ከተከናወነ በኋላ ቀጣይ ስነ-ስርዓት አካባቢውን ጥሎ መሄድ ነው። ሾርቃውን፣ ጋኑን፣ ቆዳዎቹን፣ ሾፎሮ የተሰራበትን ድስት እና መገልገያ እቃዎቹን ሁሉ እዛው ጥሎ መሄድ ነው። ከዚህ በኋላ ማንም ሰው እርሱ በተሸኘበት እቃ እና እርሱ ይገለገልበት በነበረው መሣሪያ አይጠቀምም። እርሱ ሲሄድ እና ሲያርፍ እነርሱም መሔድ እና ማረፍ አለባቸው። ስለዚህም ዕቃዎቹ ሁሉ ከዚህ በኋላ አገልግሎት አይሰጡም። ከመቃብሩ ቦታ ሲኬድ የሚች ቤተሰቦች የቀብሩ ቦታ መግቢያ አካባቢ ሽንኩርት ፈልቅቀው ያስቀምጣሉ። የቀበረ እርሱን እየረገጠ ይሄዳል። በእርጥብና በንፁህ መንገድ ተመለሱ ውስጣችን ንፁህ ሆኗልና በእኛ ላይ አለፉ፣ በእኛ ላይ ተማመኑ ማለት እንደሆነ የአካባቢው ሽማግሌዎች ይገልፃሉ። የመጣው ለቀስተኛ ሁሉ እንደ አመጣጡ ባደ እጁን ይመለሳል። ነገር ግን እንደ ሞተ የተገነዘበት ቆዳ ተይዞ ወደ ወላጆቹ ቤት እንዲሄድ ይደረጋል። ወላጆቹም ቆዳውን የቤታቸው የውጭ ግድግዳ ላይ ይሰቅሉታል። ይህም ከአሁን በኋላ እርሱን ፈልጎ ለመጣ ሰው፣ ለክብቶቹ እና ለህመም እና ለሞት መንፈስ መሄዱን እና እዚህ አለመኖሩን ምልክት መስጫ ነው። ክብቶቹ በእርሱ ናፍቆት ሊጠቁ ይችላሉ ተብሎ ስለሚታመን ቤተሰቡን እንዳያስቸግሩ ምልክቱ እና መልዕክቱ ከውጪ ይደረግላቸዋል።



ምስል 9- አርፍዶ የመጣ ለቀስተኛ በሽማግሌዎች አማካይነት ይቅርታ ሲጠይቅ

ባላባት ወይም ሽማግሌ የሞተ እንደሆነ ግን ቀባሪዎቹ፣ ለቀስተኞቹ እና ሀዘን እንዲወጣላቸው እና እንዲሰናበቱት የመጡት የሚች ከብቶች ከቀብሩ ስነ-ስርዓት በኋላ ከአካባቢው በሩጫ እንዲርቁ ይደረጋል። ይህም የደስታው ስሜት እንዳይጠፋ እና ስንብታቸው የሠመረ እና የተሳካ እንዲሆን በማሰብ የሚደረግ ነው። ብዙውን ጊዜ ከለቅሶ እና ከቀብር በኋላ ስነ-ስርዓቱ ወደ ማክተሙ ይሄዳል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ከቀብሩ በኋላ ደመቅ ያለ ለቅሶ እና የትልቅ ሰው ሞት ከሆነ የምግብና የመጠጥ ግብዣና የጭፈራ ክዋኔ ይቀጥላል። ይህም የሚሆነው ህዝቡ በብዛት አርብቶ አደር በመሆኑ ከእሩቅ አካባቢዎች የሚመጡ በርካታ ሰዎች ስላሉ ነው። ወ/ሮ ሶፋ ዶቢያር እንደሚገልፁት የወጣት፣ የጎልማሳ እና የህፃን ለቅሶ ከሆነ ግን ሁሉም ነገር ቀብሩ ላይ ያልቃል። ከቀብሩ በኋላ በግል እየመጣ ሀዘንተኛ ቤተሰቦችን የሚያፅናና እና ምን እንርዳ፣ ምን እናግዝ የሚል እንጂ ከረፈደ መጥቶ የሚያለቅስ እና ለቅሶ ልድረስ የሚል አይኖርም።

4.4. የቀጠሮ ለቅሶ

በበና ብሔረሰብ ዘንድ ሁለት አይነት የለቅሶ ክዋኔዎች አሉ። መደበኛ ለቅሶ እና የቀጠሮ ለቅሶ። የቀጠሮ ለቅሶ የማይሠጣቸው እና በመደበኛ መልኩ የሚካሄዱት የአዋቂ እና የተለየ ምክንያት ካልተፈጠረ በቀር የባላባት ለቅሶዎች ናቸው። የእነዚህ ሁለት አካላት ለቅሶዎች በማህበረሰቡ እና በአካባቢው ዘንድ ቀድሞ የመሰማት እና የመታወቅ እድል ስላላቸው ሁሌም ሲባል በሚችል ሁኔታ በመደበኛው መንገድ ነው ስርዓቱ የሚፈጸምላቸው። ከዚህም ሌላ ሞታቸው እንደተሰማ ወዲው ስለማይቀበሩ እና ከሁለት ቀናት በላይ መቆየት ስለሚችሉ ለቀጠሮ ለቅሶ የሚሆን እድል የላቸውም። የባላባት ለቅሶ እጅግ አልፎ አልፎ በቀጠሮ የመሆን አጋጣሚ ሊከሰትበት ይችላል። ይህም በስልጣን ሽግግሩ ወቅት እክሎች ከተፈጠሩ እና ባላባት ካልተሾመ ባላባት ስለማይቀበር የሀገር ሽማግሌዎች ችግሩን እስኪፈቱት እና ነገሮችን እስኪያስተካክሉ ድረስ ቀጠሮ ይሠጣሉ።

የቀጠሮ ለቅሶ ብዙውን ጊዜ የሚደረገው በድንገተኛ ሞት ወቅት እና ብዙም ሀብትና ንብረት የሌለው ሰው ከሞተ ነው። አንድ ሰው በድንገተኛ መንገድ ከሞተ ቤተሰቦቹ በተለያየ መንገድ መልዕክቱን ይልካሉ። ጥይት ሰምቶ ወደ ቤቱ ሲገሰግስ ለመጣ ሰው እዚያው ይነገረዋል። አንዳንዱ ወዲያው መጥቶ ሊያለቅስ እና ለቅሶ ሊደርስ ይችላል። የሚች ቤተሰቦች ግን ምንም ዓይነት የመጠጥና የምግብ አገልግሎት አይሰጡትም። ከተወሰነ ቆይታ በኋላ ሰው መጥቶ ሲሰበሰብ ለቅሶውን በዚህ ቀን አድርጌዋለሁ እና በዚያን ቀን መጥታችሁ ድረሱኝ ይላል። የሚወሰነው ቀን ብዙውን ጊዜ ከሐሙስ ዕለት ከአንድ ወይም ከሁለት ቀን በኋላ ነው። ይህ የሚሆነው ሐሙስ የገበያ ቀን በመሆኑ በርካታ ሰዎች ይገናኛሉ። ስለዚህም ሐሙስ የሰሙ ሰዎች በቀጣዮቹ ሁለት ቀናት ተዘጋጅተው እና ለሌሎች ሰዎችም ነግረው እንዲመጡ ይደረጋል። ከቀጠሮው ቀድመው ወደ ቤቱ የሚመጡ ሰዎች እና ቤተሰቦች ይኖራሉ። እነዚህ አካላት ከለቅሶው በፊት የሚመጡት ስራ ለማገዝ፣ ለመገነዝ ወይም ለለቅሶው ማስኬጃ የሚሆን እርዳታ ለመስጠት ነው። ይህ እርዳታ የከብት፣ የመጠጥ ወይም የገንዘብ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ሰዎች ግን ለቅሶ ደረሱ ማለት አይደለም።

የቀጠሮው ቀን ሲደርስ ሁሉም ነገር የተዘጋጀ እና የተጠናቀቀ ስለሆነ ስነ-ስርዓቱ የደመቀ እና የተሳካ ይሆናል። ለቀስተኛው በጠዋት እየመጣ ብዙ ጥይቶችን ይተኩሳል። በተለይ ዕድሜው ገፋ ያለ ወጣት ከሆነ ወዳጅ ዘመዶቹ፣ ጓደኞቹ እና የአካባቢው ሰዎች ሁሉ ተዘጋጅተውበት ከየትም ብለው መሣሪያ ይዘው ይመጣሉ። በቀጠሮ ለቅሶ ወቅት የሚሰማው ተኩስ በጣም ከፍተኛ ነው። በዚህ ጊዜ የአካባቢ ሰው በመጠኑም ቢሆን መስጋቱ አይቀርም። አንዳንድ ጊዜ መሳሪያዎች እየባረቁ እና በመቀት እና በእሳት ብዛት እየተያያዙ የቃጠሎ አደጋ እያደረሱ ጉዳት ያመጣሉ። ለቅሶው ግን የደመቀ እና የተዋጣለት መሆኑ አይቀርም። በዚህ ቀን ለቅሶ ያልደረሰ ሰው ሌላ ጊዜ ቢመጣ የምግብ እና የመጠጥ አገልግሎት አይቀርብለትም። በለቅሶው ቀን ቤተሰቡ ባገኘው እርዳታ እና ለቀስተኛው ሲመጣ ይዞት የሚመጣው እና የተዘጋጀበት ስጦታ ለቅሶውን ደማቅ እና የተሳካ እንዲሆን ያደርገዋል።

የቀጠሮ ለቅሶ በርካታ ፋይዳዎች አሉት። አንደኛ ከኢኮኖሚ አንፃር ያለው ጥቅም ሰፊ ነው። በየጊዜው ለሚመጣ ለቀስተኛ እና ቤተሰብ በየጊዜው ከብት ማረድ እና መጠጥ ማዘጋጀት የኋላ ኑሮውን ይጎዳበታል፤ የቀጠሮ ለቅሶ ከዚህ ያድናል። ሁለተኛ ለለቀስተኛ ማስተናገጃ በየጊዜው በሚደረግ ግብግቦ የተነሳ ከተለያየ ሰው ቤት ብድር መጠየቅ በኢኮኖሚም ሆነ በሥነ-ልቡና ረገድ የሚያስከትለው ተፅዕኖ ከባድ ነው። ሦስተኛ ለቀስተኛ በተለያየ ጊዜ በመጣ ቁጥር አብሮ ማልቀስ እና ማዘን ቋሚን መጉዳት እና በሽተኛ ማድረግ ነው። ከዚህ ሌላም ሀዘንተኛው ቤተሰብ ሊፅናና እና ሀዘኑን ሊረሳ አይችልም። ለቀስተኛ በመጣ ቁጥር እርሱን ማስተናገድም የግል ስራን የሚያስተጓጉል ነው። ስለዚህም በአንድ የቀጠሮ ለቅሶ ቀን መገላገል ጠቃሚ ነው። ሀዘንን ቶሎ ለመርሳት፣ ጉልበትን ለመቆጠብ፣ ከምንም በላይ ደግሞ ወጪን ለመቀነስ ያግዛል። ሕዝቡም ስራውን ከመፍታት እና ከሀዘንተኛ ቤተሰብ ጋር ላለመቀያየም የቀጠሮ ለቅሶ ጠቃሚ ነው። አስቦበት እና ተዘጋጅቶበት ለቅሶው ላይ ለመሳተፍ እድል ያገኛል። የሩቅ አካባቢ ሰውም በጊዜው ለቅሶ በመድረስ ማህበራዊ ግዴታውን ይወጣል። ስለዚህም በሐዘንተኛው ቤተሰብ ወገንም ሆነ ለቅሶ በሚደርሰው ማህበረሰብ ዘንድ የቀጠሮ ለቅሶ ያለው አገልግሎት እና ጥቅም ዘርፈ ብዙ ነው።

5. ማጠቃለያ እና ይሁንታ

5.1. ማጠቃለያ

በዚህ የጥናት ፅሁፍ ውስጥ የበና ብሔረሰብ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ምን እንደሚመስል ተመልክተናል። የበና ብሔረሰብ አንድ ሰው ሲሞት ከአድሜ፣ ከማህበራዊ ደረጃ እና ከማህበራዊ ተሳትፎ አንፃር የተለያየ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ያካሂዳል። የለቅሶ ስነ-ስርዓቱና የቀብር ሁኔታዎች የብሔረሰቡን አመለካከት እና ፍልስፍና፣የሚችን ማንነት እና ምንነት እንደዚሁም የሞትን (ሚችን) እና የሕይወትን (ቀሪን) ትርጉም የመግለፅ አቅማቸው እምን ድረስ እንደሆነ ተገልጿል።

በበና ብሔረሰብ ዘንድ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔ ሞት መምጫውን ከማረጋገጫ ብልሃቶች አንስቶ መልክ ብዙ እና ሰፊ መሆኑን ተመልክተናል። ለዚህ አገልግሎትም በተለይ የአዋቂ ቤት ምክር እና መልዕክት እንደዚሁም የማር ጠጅ ዋና የማረጋገጫ መሳሪያዎች ሆነው ተገኝተዋል። እነዚህ ሁለት መሳሪያዎች እንደደከመው ሰው ማንነት እና ምንነት በየበኩላቸው መጪውን የመጠቆም ብልሃታቸው እንደምን እንደሆነ ተመልክተናል። ኑዛዜ የለቅሶ ስነ-ስርዓቱን ቅርፅ እና ይዘት የመወሰን አቅሙ የት ድረስ እንደሆነ እና ኑዛዜ በቋሙ በብሔረሰቡ ዘንድ ያለው ተቀባይነት እና ስለ ኑዛዜ ብሔረሰቡ ያለው አመለካከት ጠንካራ እና ፍፁም ተተግባሪ መሆኑን አስተውሰናል። በለቅሶው ስነ-ስርዓት ቅድመ ዝግጅት ወቅት ለለቀስተኛ የሚደረጉ የመጠጥ እና የምግብ ዝግጅቶች፣ክዋኔውን በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ የሚደረጉ የቦታ እና የአካባቢ ዝግጅቶች እንደዚሁም የቀብር ስነ-ስርዓቱን ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ሰዎች ምርጫ ይካሄዳል። ጎን ለጎንም የሚች መሸጋገሪያ ቤት በመጀመሪያ ልጁ ልክ እንደሚሰራ አስተውሰናል።

አይቀሬው ሞት ከተከሰተ በኋላ በመጀመሪያ ሰው በምን መልኩ እንደሚጠራ ተጠቁሟል። ሰው ከተሰበሰበ በኋላም የአገናኝ፣የለቀስተኞች ወደ ለቅሶው ቤት አመጣጥ እና አገባብ፣የለቀስተኞች አቀባበል እንደዚሁም የአጨፋፈር እና የማፅናናት ሂደቱ እንደየሚች ማንነት እና ምንነት የተለያየ ነው። ገናዥ እና አገናኝንም የሚች

ማህበራዊ ደረጃ እና ተሳትፎው እንደሚወስነው ተስተውሏል። የሬሳ ካረፈበት ቤት አወጣጥ እና የቀብሩ ጉዞ በምን መልኩ እንደሚካሄድም ተመልክተናል። በተጓዥ ክቡርነት የተነሳ ማንም ከሬሳ ፊት አይቆምም፣አይሄድምም። በቀብሩ ቦታ ላይ ለሚካሄዱ ክዋኔዎች ሁሉ

ግንባር ቀደሙ ተዋናይ የሚች የመጀመሪያ ልጅ ነው። እሳት በመጫር፣ ፍየል በመምረጥ እና በመውጋት፣የአባቱን ሬሳ በማልበስ እና በማስተካከል፣አፈር በማልበስ እና ጥይት በመተኮስ ረገድ የሚቀድመው ሰው የለም። በዚህ ወቅት የሚበላው የምግብ ዓይነት፣አበላሉ እና እነማን ለምን እንደሚበሉት እና እንደማይበሉት ተመልክተናል። የሬሳ አቀባበር ምን ጊዜም በቀኝ በኩል ወደ መጣበት አቅጣጫ መሆን አለበት። ወደመጣበት ይመለስ ዘንድ።

እንደሚቹ ማንነት እና ምንነት ከቀብር ቦታው የሚደረገው አመላለስም የተለያየ ነው። ከዚህ በኋላም በመኖሪያ ቤቱ ለሚደረገው ቀጣይ ክዋኔ ይኸው ጉዳይ ዋና መስፈርት ነው። በበና ብሔረሰብ ዘንድ ሁለት የለቅሶ ስነ-ስርዓት ዓይነቶች እንዳሉ ተመልክተናል። መደበኛ እና የቀጠሮ ለቅሶ። ሁለቱ ለማንና ለምን እንደሚደረጉ እና ጥቅምና አገልግሎታቸው ምን እንደሚመስል ከተለያየ አቅጣጫ ተመልክተናል። በአጠቃላይ በበና ብሔረሰብ ዘንድ የሚደረጉ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ክዋኔዎች እንደሚቹ ማንነትና ምንነት የሚወሰኑ ሲሆን በውስጣቸው ያለውም ሂደት የሚች፣ የቀሪን፣ የሞትን፣የሕይወትን፣የማህበረሰቡን፣የባህሉን እና የአካባቢውን ማንነት፣ እንዴትነት፣ አመለካከትና ትርጉም የመግለፅ አቅማቸው ከፍ ያለ ነው።

በጥናቱ ሂደትና ግኝት ላይ እንደተመለከትነውም እያንዳንዱ የባህል ዘርፍ የራሱ የሆነ ቅርጽ፣ መልእክት እና አገልግሎት አለው። የለቅሶ ስነ-ስርዓትም በውስጡ የሚያካትታቸው የቀብር ስነ-ስርአት እና የአቀባበር ሁኔታ፣ የማስተዛዘኛ እና የሀዘን መግለጫ መንገዶች የራሳቸው ጥቅምና አገልግሎት አላቸው። ስለዚህም በተገቢው ሀኔታ መቃኘት፣ መጠናት፣ መተንተን እና መተርጎም አለባቸው። ከዚህ በኋላም ይህንን ርእሰ ጉዳይ አንስተው የሚያጤኑ ሰዎች በተለይ በእያንዳንዱ ክዋኔ ውስጥ ያለውን መልእክትና ትርጉም በትኩረት ቢያጤኑት መልካም ነው። ከመዘርዘርና ከመግለጽ ወደ መተንተንና መተርጎም ደረጃ ተሸጋግረው ቢጠኑ ጥቅምና አገልግሎታቸው የጎላ መሆኑን ተመልክተናል።

5.2. ይሁንታ

ይህንን የጥናት ፅሁፍ ለማዘጋጀት የመስክ ስራ ማካሄድ አስፈላጊ ነበር። ለዚህም ሲባል ወደ በናፀማይ ወረዳ አካባቢ በመሄድ ከአንድ ወር ላላነሰ ጊዜ ተቀምጫለሁ። በዚህ ጊዜም የተለያዩ መልካምም መልካም ያልሆኑም ሁኔታዎች ገጥመውኛል። በመጀመሪያ ወደ አካባቢው በመሄድ ለፍቃድ የተለያዩ ቢሮዎችን አንኳኩቻለሁ። እንግዳ በመቀበል፣ በማስተናገድ እና ከሰው ጋር በማስተዋወቅ እና በማናኘት ረገድ ሊመሰገኑ ይገባቸዋል። ለዚህም ይመስላል የአካባቢው የጎብኚዎች ብዛት ከዓመት ዓመት እየጨመረ የመጣው። ከዚህም በተጨማሪ የአካባቢው ሰዎችም ሆኑ የመንግስት መስሪያ ቤት አካላቱ ከመደበኛ ስራቸው በተጨማሪ በትርፍ ጊዜያቸውም ቢሆን የምን እናድርግልህ፣ የት ደረስክ፣ እንዴት ሆነልህ እና የበርታ መልዕክታቸው ከመተባበር እና ከማገዝ ጋርም ጭምር አልተለየኝም። በዚህ ረገድ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ በዚሁ እንዲቀጥሉ እና ትግስታቸውን እንዲያከርመት አደራ አላለሁ። ስራ ወዳድነታቸውም የሚያስመሰግናቸው እና ሌሎችንም የሚያበረታታ ነው።

በአንባሩ ከብሔረቡ ተወላጆች እና ተወካዮች ጋር ስገናኝ ጉልህ የሆኑ ችግሮችን ተመልክቻለሁ። አንደኛው በለቅሶ ስነ-ስርዓት ወቅት ደማቅ የሆነ እና ተከታታይነት ያለው ክዋኔ እንዳያካሂዱ በመንግስት አካላት መከልከላቸው ነው። በተለይም ጥይት መተኮስ እየተከለከሉ እንደሆነ ገልፀውልኛል። ይኸውም "የአካባቢውን ሰው ትረብሻላችሁ፣ ሰላም ታደፈርሳላችሁ" በሚል ምክንያት የተኮሰ ሰውለ እንደሚያዝ እና መሳሪያውን እንደሚነጠቅ ይናገራሉ። ይህም "በችግር ጊዜ ሰው እንዳንጠራ እና ሞት በመጣም ጊዜ ድረሱልን ለማለት ተቸግረናል" በማለት ይገልፃሉ። ሌላው "ሞቅ ያለ እና ተከታታይነት ያለው ክዋኔ ማድረግ ጎጅ ባህል ነው እና እንዳታደርጉ" መባላቸውን ይገልፃሉ። በዚህም ሳቢያ ተገቢ ለሆነ ሰው ተገቢ ነው ብለው የሚያስቡትን ክዋኔ ማድረግ እንዳልቻሉ ጠቁመዋል። ይህንንም ጉዳይ የወረዳው የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ቢያጤነው እና ተገቢ የሆነ ክትትል ቢያደርግበት መልካም ነው።

ሁለተኛው ያስተዋልሁት ዓቢይ ችግር በብሔረሰቡ አባላት ዘንድ የተለመደ ጉዳይ ነው። ይኸውም በእያንዳንዱ ድርጊት ላይ የሚጠይቁት ገንዘብ መጠኑን ያለፈ እና አትምን ያሳገናዘበ መሆኑ ነው። ለዚህም እንደ ዓቢይ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰደው በተለይ የውጭ ሀገር ዜጐች ወደ አካባቢው በብዛት ስለሚመጡ እና መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ

ስለሚሰጧቸው ነው። ለሰጡት አገልግሎት ተገቢ የሆነ ክፍያን ማግኘት አለባቸው። ይህም ታዳያ የሰውን አቅም ያገናዘበ መሆን መቻል አለበት። ለዚህም ደግሞ በአካባቢው የሚገኙት የአስጎብኚ ማህበራት እና አገልግሎት ሰጭዎች ለአገልግሎት ሰጪውም ሆነ ፈላጊው አካል ትምህርትና ስልጠና ቢሰጡ መልካም ነው። ይህ ካልሆነ ግን በየአንድ የፎቶ ብልጭታ እና በቪዲዮ ቀረፃው ቆይታ ወቅት የሚጠይቁት ከፍያለ የገንዘብ መጠን የሃገር ውስጥ አጭኒንም ሆነ ጎብኚን አቅም የሚፈታተን በመሆኑ የሚያበረታታ አይሆንም።

ሌላው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ በእነዚሁ የውጭ ሃገራት ጎብኚዎች መብዛት ሳቢያ የአካባቢው ባህልና እሴት እየተቀየረ መምጣቱ ነው። ለዚህ ማሳያ የሚሆነን የስም አወጣጥ ነው። ብዙዎቹ በእድሜ ገፋ ያሉ እና ባህላቸውን የሚጠብቁ ሰዎች የስሙን ጉዳይ አይደራደሩበትም። ይሁን እንጂ አንዳንድ ታዳጊዎች እና ወጣቶች ከእነርሱ ጋር ጥሩ ጊዜ ባሳለፈ፣ ጥሩ ገንዘብ በሰጣቸው እና ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን ባቀረበላቸው የውጭ ሀገር ሰው መጠራትን እየለመዱት መጥተዋል። ከእነዚህም መሀከል "አሌክሳንደር"፤ "ሚኪ"፤ "ጆን" እና "ቶም" የተሰኙ ሰዎችን አግኝቼ ይህንኑን ጉዳይ አረጋግጫለሁ። በዚህ ረገድ የአካባቢው የባህልና ቱሪዝም ቢሮ በዚህ ጉዳይ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ቢሰራ መልካም ነው። የስምን ዋጋ እና ትርጉም ማሳየት እና ማስተማር አስፈላጊ ነው። አለዚያ በስም የተጀመረው የባህል እና እሴት መሸርሸር ነገ ከነገ ወዲያ በነበር ቀርቶ ፀፀትና ቁጭት ውስጥ እንዳይጥለን።

ዋቢ ጽሑፎች

ሐረገወይን ድፋባቸው፤ "የክስታንኛ የለቅሶ ግጥሞች"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፤ ዲማጽ፣ 1974።

ሞገስ ሚካኤል፤ "በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ስነ-ስርዓት፤ በስርዓቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፋከራና ክዋኔው"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፤ የሁዲማጽ፣ 2002።

ቤታና ሆጤሶ፤ *ሲዳማ... ሕዝብና ባሕሉ*፤ አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ 1983።

ተሾመ መሉጌታ፤ "በቤንሻንጉል ጉሙዝ በድባጢ ወረዳ የለቅሶ ስነ-ስርዓት"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፤ ዲማጽ፣ 1998።

አህመድ መሀመድ፤ "በአሪ ብሔረሰብ የቢዩ ባላባታዊ ቤተሰብና የለቅሶ ስርዓት"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፤ ዲማጽ፣ 1989።

አስቴር አንጀሎ፤ "የጋሞ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፤ ዲማጽ፣ 1997።

አየለ መሎሪ፤ "የሀዲያ ህብረተሰብ የለቅሶ ስነ-ስርዓት"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፤ ዲማጽ፣ 1986።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፤ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948።

ወርቁ ማንደፍሮ፤ "በሊቦ ከምከም ወረዳ የለቅሶ ስነ-ስርዓትና የሙሾ ግጥሞች"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፤ ዲማጽ፣ 1987።

ዘላለም ኢዮብ፤ "በጎፋ ብሔረሰብ ባህላዊ ለቅሶ (ዬሆ) ግጥሞች ክዋኔና ስነ-ግጥማዊ ገፅታ"፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፤ ዲማጽ፣ 1995።

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን እና ዩኔስኮ፤ *የኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች የኢንቨንተሪ ማንዋል*፤ አዲስ አበባ፡ ማስተር ማተሚያ ቤት፣ 2002።

የብሔረሰቦች ምክር ቤት በባህል፣ ቋንቋ፣ ታሪክና ቅርስ ጥናት ተቋም፣ *የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ኽሮፋይል*፣ ሐዋሳ፣ ፍቅረሠላም ማተሚያ ቤት፣ 2001።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1972።

በደቡብ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የደቡብ ኦሞዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ፣ *"የዞኑ የስነ-ህዝብና ልማት ሁኔታ ባጭሩ"*/ ጂንካ፣ 2002።

ደስታ ተክለ ወልድ፣ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962።

ፈለገህይወት ዘገየ፣ "በባንጃ ሽኩዳድ ወረዳ የቀብር ስነ-ስርዓትና የለቅሶ ግጥሞች ስብስብ ይዘት ትንተና"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ ዲግሪ፣ 1989።

Abdulla Abdurahman. "Harriri Funeral Customs." *Ethnological Society Bulletin. Ed.* Alula Pankhurst. Vol. 1, No. 1. Addis Ababa, Addis Ababa University Press. 2002. *pp.* 16-24.

Andargachew Tesfaye. "The Funeral Customs of the Kottu of Harar." *Ethnological Society Bulletin. Ed.* Alula Pankhurst. Vol. 1, No. 7. Addis Ababa, Addis Ababa University Press. 2002. *pp.* 216-219.

Authority For Research and Conservation of Cultural Heritage. *An Inventory of the Intangible Cultural Heritage of Sixteen Nations and Nationalities in South Omo Zone of SNNPR.* Addis Ababa: Master Printing Press, 2008.

Barnard, Alan and Jonathan Spencer. (*Eds*) *Encyclopedia of Social and Cultural Anthropology.* London and New York, Taylor and Francis e –Library, 2005.

Danesi, Marcel. *Messages, Signs and Meanings.* 3rd ed. Toronto: Canadian Scholars' Press, 2004.

Fasika Belete. "The Death Customs Among The Amharas of Šäwa." *Ethnological Society Bulletin. Ed.* Alula Pankhurst. Vol. 1, No. 7. Addis Ababa, Addis Ababa Universty Press. 2002. *pp.* 204-211.

Finnegan, Ruth. *Oral Tradition and The Verbal Arts: a Guide to Research Practices.* New York: Thomson Publishing Company, 1992.

Green, Thomas A. *(Ed). Folklore: an Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music and Art.* Santa Barbara. ABC- CLIO, Inc. 1997.

Goldstein, Kenneth S. *A Guide for Field Workers in Folklore.* Pennsylvania: Folklore Associates Inc., 1964.

Hertz, Robert. *Death and the Right Hand. Trans.* Rodney and Needham, Claudia. Aberdeen; Aberdeen University Press. 1960

Martha C. Sims and Martine Stephens. *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Traditions.* Ohio: Utah state University press, 2005.

Nega Tesema. "The Death Customs in The Province of Tigre." *Ethnological Society Bulletin. Ed.* Alula Pankhurst. Vol. 1, No. 5. Addis Ababa, Addis Ababa Universty Press. 2002. *pp.* 108-115.

Rappaport, Roy A. "Ritual." *Folklore, Cultural Performances, and Popular Entertainments. Ed.* Richard Bauman. New York, Oxford University Press, 1992. *pp.* 249-260.

Tamirat Beyene. "The Benaṣ: Historical and Cultural Review Profile." Key Afer: *n.p.* , 2011.

Watts, Linda S. *Ed. Encyclopedia of American Folklore.* New York: InfoBase Publishing, 2007

አባሪዎች

አባሪ አንድ:- የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

ተ.ቁ	የዋና መረጃ አቀባይ ስም	ዕድሜ	ፆታ	ሥራ	ቀበሌ	መረጃ የተሰበሰበበት ቀን	መረጃ የተሰበሰበበት ቦታ
1	አቶ በላቸው ሉማር	68	ወንድ	አርብቶ አደር	ሻባ	አርብ ሚያዚያ 14/2003ዓ.ም	የቀበሌው ጤና ጣቢያ ግቢ ውስጥ
2	አቶ ጋየ ፊዮ	70	ወንድ	አርብቶ አደር	ሻባ	አርብ ሚያዚያ 14/2003ዓ.ም	የቀበሌው ጤና ጣቢያ ግቢ ውስጥ
3	አቶ ሰጎ አዮ	65	ወንድ	አርሶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር	ሻባ	ቅዳሜ ሚያዚያ 15/2003ዓ.ም	የቀበሌው ጤና ጣቢያ ግቢ ውስጥ
4	ወ/ሮ ሶፋ ዶቢያር	50	ሴት	የቤት እመቤት	ሻባ	ቅዳሜ ሚያዚያ 15/2003ዓ.ም	የቀበሌው ጤና ጣቢያ ግቢ ውስጥ
5	ወ/ሮ ወንገላ ሰጎ	48	ሴት	የቤት እመቤት	በሶ	ቅዳሜ ሚያዚያ 15/2003ዓ.ም	መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ
6	አቶ ዶይያ ኪሎ	53	ወንድ	የኦልካኪቦ ቀበሌ የፀጥታ ዘርፍ አስተዳደር ኃላፊ	ኦልካቦ	ማክሰኞ ሚያዚያ 18/2003ዓ.	የመቃብሩ ቦታ ላይ
7	አቶ ፍቃዱ ጋሴ	63	ወንድ	የግል ሙዚየም አስጎብኚ	ጅንካ ጤናዳም ሰፈር	እሁድ ሚያዚያ 23/2003ዓ.ም	በመኖሪያ ቤታቸው ግቢ ውስጥ

					ቁስሉ	መረጃ የተሰበሰበበት ቀን	መረጃ የተሰበሰበበት ቦታ
1	ወ/ሪት ዋዩ ዲመኮ	27	ሴት	የቤት እመቤት	ሻባ	አርብ ሚያዚያ 14/2003ዓ.ም	የቀበሌው ጤና ጣቢያ ግቢ ውስጥ
2	አቶ ቃሮ ቡኔ	60	ወንድ	አርብቶ አደር	ሻባ	አርብ ሚያዚያ 14/2003ዓ.ም	የቀበሌው ጤና ጣቢያ ግቢ ውስጥ
3	አቶ በኒ ኪሎ	62	ወንድ	አርብቶ አደር እና ባላባት	ሻባ	አርብ ሚያዚያ 14/2003ዓ.ም	መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ
4	ወ/ሮ ዋዶ ኢሾ	43	ሴት	የቤት እመቤት	በሶ	ቅዳሜ ሚያዚያ 14/2003ዓ.ም	መኖሪያ በሚገኘው ቤታቸው ውስጥ
5	አቶ መኮንን ጪንጊ	32	ወንድ	አርብቶ አደር	በሶ	ቅዳሜ ሚያዚያ 15/2003	መኖሪያ ቤታቸው አቅራቢያ በሚገኘው ሜዳ ላይ
6	አቶ ቦዶ ኢሾ	55	ወንድ	አርብቶ አደር	በሶ	ቅዳሜ ሚያዚያ 15/2003ዓ.ም	መኖሪያ ቤታቸው አቅራቢያ በሚገኘው ሜዳ ላይ
7	ወ/ሮ ተሚማ ገላን	35	ሴት	የበና ፀማይ ወረዳ የማስታወቂያና ባህል ጽ/ቤት የሕዝብ ግንኙነት ኤክስፐርት	ቀይ አፈር	ማክሰኞ ሚያዚያ 18/2003ዓ.ም	በፅህፈት ቤቱ ቢሮ ውስጥ
8	አቶ ማሌ ኢሾ	49	ወንድ	አርሶ አደርና ከፊል	አልካሊቦ	ማክሰኞ ሚያዚያ 18/2003ዓ.ም	የመቃብሩ

				አርብቶ አደር			ቦታ ላይ
9	አቶ ቢቶ ባና	41	ወንድ	አርሶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር	ኦልካኪቦ	ማክሰኞ ሚያዚያ 18/2003ዓ.ም	የመቃብሩ ቦታ ላይ
10	አቶ ተስፋዬ ኢሾ	42	ወንድ	የሻባ ቀበሌ ጽ/ቤት ዋና ኃላፊ	ሻባ	እሁድ ሚያዚያ 23/2003ዓ.ም	በመኖሪያ ቤታቸው
11	አቶ ዋልታ	33	ወንድ	የበና ፀማይ ወረዳ የማስታወቂያ ባህል ጽ/ቤት የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ	ኦልካኪቦ	እሁድ ሚያዚያ 23/2003ዓ.ም	በመኖሪያ ቤታቸው
12	አቶ ሚኪ ቀላዬ	23	ወንድ	አርብቶ አደር	ኦልካኪቦ	እሁድ ሚያዚያ 23/2003ዓ.ም	በመኖሪያ ቤታቸው
13	አቶ ማሙሸ	27	ወንድ	የአኑ-ምባ አስጎብኚዎች ማህበር አባል እና አስጎብኚ	ቀይ አፈር	እሁድ ሚያዚያ 23/2003ዓ.ም	በመኖሪያ ቤታቸው
14	አቶ ፍራይሁን ፍቃዱ	30	ወንድ	መምህር ርዕስ መምህር ማግሌ ወረዳ ዶዶስ አንደኛ ደረጃ ት-ምህርት ቤት	ጅንካ ጤናዳም ሰፈር	እሁድ ሚያዚያ 23/2003ዓ.ም	በመኖሪያ ቤታቸው ግቢ ውስጥ

አባሪ ሁለት፡- ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ መንደርደሪያ ጥያቄዎች

አባሪ ሁለት፡- ቃለ-መጠይቅ ለተደረገላቸው አካላት የቀረቡ መንደርደሪያ ጥያቄዎች

የበና ብሔረሰብ አመጣጥ ምን ይመስላል?

የበና ብሔረሰብ የማህበራዊ ደረጃ ክፍፍሎች እንዴት ያሉ ናቸው?

የማህበራዊ ደረጃ ክፍፍሎቹ የስራ ድርሻ እና አገልግሎታቸው ምንድን ነው?

ለህፃናት ሞት የሚደረገው የለቅሶ ስነ-ስርዓት ምን ይመስላል?

ለወጣት ሞት የሚደረገው የለቅሶ ስነ-ስርዓት ምን ይመስላል?

ለጎልማሳ ሞት የሚደረገው የለቅሶ ስነ-ስርዓት ምን ይመስላል?

ለአዛውንት ሞት የሚደረገው የለቅሶ ስነ-ስርዓት ምን ይመስላል?

ባላባት ሲሞት የሚደረገው የለቅሶ ስነ-ስርዓት ምን ይመስላል?

መደበኛ ለቅሶ እና የቀጠሮ ለቅሶ ልዩነታቸው ምንድን ነው?

በለቅሶ ስነ-ስርዓት ወቅት የየማህበረሰብ ክፍሉ የስራ ድርሻ ምንድን ነው?

በለቅሶው ስነ-ስርዓት ክዋኔ ወቅት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶች የትኛዎቹ ናቸው?

አገለግለት፡- የዞኑ ወረዳዎች አጠቃላይ መረጃ

የባህል ሴክተር


ቅጽ 11-01 በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ብሔረሰቦች ስብጥርና ቁንቁ የ2000 ዓ.ም

ዞን /ልዩ ወረዳ/ ወረዳ /ክ/አስ ----------


ተ.ቁ	የብሔረሰቡ ስም	የብ/ሰቡ አፍ መፍቻ ቁንቁ ስም	የቁንቁው ተናጋሪ ህዝብ ብዛት	ብሔረሰቡ የተሰበሰራበት ዋና የስራ ዓይነት	ብሔረሰቡ የሰፈረበት የመሬት ስፋት	በብሔረሰቡ ውስጥ የሚገኙ ገሳዎች ብዛት	ምርመራ
1	አሪ	አሪኛ	216921	ግብርና		ከ50 በላይ	አንዲና አሸንዳ መስራች ገሳዎች
2	ማሌ	ማለኛ	69355	ጥምር ግብርና		30	
3	በና	በኒኛ	29696	//		20	ጋታና ጋላቦ መስራች ገሳዎች
4	ፀማይ	ፀማይኛ	8897	አርብቶ አደር		6	
5	ብራይሌ	ኦንገታ	109	ግብርና		3	
6	ኤርቦሬ	ኤርቦርኛ	5831	አርብቶ አደር		16	
7	ሐመር	ሐመርኛ	41013	//		20	
8	ካሮ	ካሮኛ	2973	//		10	ጋታና ጋላቦ መስራች ገሳዎች
9	ዳሰነች	አፍ ዳሰነች	44399	//		8	
10	ካንጋቴን	አፍ ኛንጋተም	16241	//		7	
11	ሙርሌ	አፍ //	3491	//		1	
12	ኑዌን	ኑዌንኛ	606	ጥምር ግብርና		3	
13	ቦዲ	ቦዲኛ	6500	አርብቶ አደር		14	
14	ሙርሲ	ሙርሲኛ	8034	//		12	
15	ዲሜ	ዲሜኛ	8090	ግብርና		17	
16	ሃሚ/ባጫ	አሪኛ ዲሜኛ ቦዲኛ		ጥምር ግብርና		[illegible]	
		ድምር	462216				
		+	38158				
			500374				

Weredas in South Omo Zone

አላቢ አሬት፡-
የወረዳዎች እና የቀለሌዎች
ካርታዎች



WEREDAS AND KEBELES IN SOUTH OMO ZONE



ማረጋገጫ

ይህ የጥናት ጽሑፍ የእኔ የግል ስራ መሆኑንና በዕሁፉ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ተዛማጅ ጽሑፎችንና መረጃዎችን በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ።

ስም፡ ዘላለም ፋንቱ

ፊርማ

የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

መስከረም 2004ዓ.ም

አዲስ አበባ